# “መንግሥት ያለ አይመስልም ነበር”

## የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ በተከሰተው የፀጥታ መደፍረስ ምክንያት የተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ምርመራ ሪፖርት

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
(ኢሰመኮ)

2013 ዓ.ም.

# “መንግሥት ያለ አይመስልም ነበር”

## የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ በተከሰተው የፀጥታ መደፍረስ ምክንያት የተፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ምርመራ ሪፖርት

2013 ዓ.ም.

# ማውጫ


አንኳር እና ምክረ ሃሳቦች ........ 1

አንኳር ........ 1

ምክረ ሃሳቦች ........ 6

መግቢያ ........ 8

1. አገራዊ እና ክልላዊ አውድ ........ 10

2. ምርመራው በተከናወነባቸው ስፍራዎች ስለነበሩ ክስተቶች ሂደት ........ 11

*2.1. አምቦ ከተማ እና አካባቢው* ........ 11

*2.2. ጭሮ ከተማ* ........ 13

*2.3. መተሃራ ከተማ* ........ 15

*2.4. ሀሮማያ ከተማ* ........ 15

*2.5. አወዳይ ከተማ* ........ 17

*2.6. ፍቼ ከተማ* ........ 18

*2.7. ወሊሶ ከተማ* ........ 19

*2.8. አዳማ ከተማ* ........ 23

*2.9. ዴራ ከተማ* ........ 24

*2.10. አዳባ ከተማ* ........ 26

*2.11. ባሌ ዞን አጋርፋ ወረዳ* ........ 27

*2.12. ኮፈሌ ከተማ* ........ 29

*2.13. ጉና ወረዳ ነገሌ ከተማ* ........ 30

*2.14. ዶዶላ ከተማ* ........ 32

*2.15. ቡራዩ ከተማ* ........ 32

*2.16. አርሲ ነጌሌ ከተማ* ........ 34

*2.17. ባቱ ከተማ* ........ 35

*2.18. ሻሸመኔ ከተማ* ........ 36

*2.19. ጅማ ዞን (ጅማ፣ የቡ እና ሰቃ ከተማዎችን ያጠቃልላል)* ........ 38

*2.20. አሰሳ ከተማ* ........ 39

*2.21. ጎባ ከተማ* ........ 40

*2.22. ኢተያ ከተማ* ........ 40

*2.23. ጀጁ ወረዳ አርቦዬ ከተማ* ........ 41

*2.24. አርሲ ሮቤ ከተማ* ........ 41

*2.25. መርቲ ወረዳ (አቦምሳ እና በሌ ከተሞች)* ........ 42

2.26. ጊንጪ ከተማ ..... 42
2.27. ሱሉልታ ከተማ ..... 42
2.28. ገርበ ጉራቻ (ኩዩ ወረዳ) ..... 43
2.29. ሀሳሳ ..... 43
2.30. ነጌሌ ስጋሎ ..... 43
2.31. በቆጂ ..... 43
2.32. ቢሾፍቱ ..... 43
2.33. ሞጆ ..... 44
2.34. መቂ ..... 44
2.35. ዱከም ..... 44
2.36. ለገጣፎ ለገዳዲ ..... 44
2.37. ገላን ከተማ ..... 44
2.38. ሲሬ ከተማ ..... 44
3. በምርመራው የተለዩ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ..... 45
3.1. ግድያ እና አካላዊና ሥነ-ልቦናዊ ጉዳት ..... 45
3.2. በንብረት ላይ የደረሰ ጉዳትና የዜጎች መፈናቀል ..... 50
3.3. የሕክምና አገልግሎት ክልከላ ..... 50
3.4. የፀጥታ አካላት የኃይል አጠቃቀም ..... 51
3.5. ጠቅላላ ድርጊቱና ውጤቱ በሰብአዊነት ላይ የተፈጸመ (crime against humanity) የግፍና ጭካኔ ወንጀል (atrocity crime) ስለመሆኑ ..... 52

# አንኳር እና ምክረ ሃሳቦች

## አንኳር

አርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. በድንገት መገደሉን ተከትሎ በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በተከሰተው የፀጥታ መደፍረስ የሰዎች ሕይወት በአሰቃቂ መንገድ ጠፍቷል፣ የአካልና የሥነ-ልቦና ጉዳት ደርሷል፣ ንብረት ወድሟል፣ ሰዎች ከቤታቸው እና ከኑሮዋቸው በመፈናቀል ለከፍተኛ እንግልት ተዳርገዋል።

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) ከዚሁ ክስተት ጋር በተያያዘ በተለያዩ ስፍራዎች ተከስቶ የነበረውን የሰብአዊ መብቶች ጥሰት መርምሯል። የምርመራው የጊዜ ወሰን የአርቲስት ሃጫሉ ግድያ ከተከሰተበት ከሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. ምሽት ጀምሮ የነበሩት 3 ተከታታይ ቀናት ናቸው።

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ምርመራ ባደረገባቸው 40 የኦሮሚያ አካባቢዎች ባሰባሰበው መረጃ መሰረት የአርቲስቱን ሞት ተከትሎ በነበሩት 3 ተከታታይ ቀናት በተከሰተው የፀጥታ መደፍረስ በአጠቃላይ የ123 ሰዎች ሕይወት አልፏል፣ ቢያንስ በ500 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ከመኖሪያቸው ተፈናቅለዋል፣ በግለሰቦች፥ በንግድ ድርጅቶችና የመንግስት ንብረት ላይ ከፍተኛ ውድመትና ዘረፋ ተፈፅሟል። ሕይወታቸው ካለፈው ሰዎች ውስጥ 35ቱ በሁከቱ በተሳተፉ ግለሰቦችና ቡድኖች የተገደሉ ሲሆን፣ እነዚሁ አካላት 306 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት አድርሰዋል። በመንግስት የፀጥታ ኃይሎች በተወሰደ እርምጃ ቢያንስ 76 ሰዎች ሲገደሉ፣ ከ190 በላይ ሰዎች የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። በሌላ በኩል በፀጥታ መደፍረሱ ወቅት በተከሰተ ፍንዳታ፣ ቃጠሎ እና መሰል አደጋዎች 12 ሰዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል።

በዚህ መጠነ ሰፊ ጥቃት የተሳተፉት ብዙ ቁጥር ያላቸው ከቦታ ቦታ በቡድን ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ሰዎች ሲሆኑ፤ በጩቤ፣ በድንጋይ፣ በእሳት፣ በኤሌክትሪክ ገመድ፣ በዱላ፣ በዶማ፣ በገጀራ እና በመጥረቢያ ተጠቅመው ሰዎችን ደብድበዋል፣ የአካል ጉዳት አድርሰዋል፣ ፍጹም ግፍና ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ በማሰቃየት ወይም በማረድ ጭምር ሰዎችን ገድለዋል። አጥቂዎቹ ሰዎችና ቡድኖች የነዋሪዎችን ቤት በመስበርና በመግባት ከፊሎቹን በየቤታቸው፤ ከፊሎቹን ከቤታቸው አስገድዶ መንገድ ላይ በማስወጣት ገድለዋል፣ ሬሳቸውን መሬት ላይ በመጎተትና በጎዳና ላይ በመጣል አስከሬናቸው ለሰዓታት ሳይነሳ እንዲቆይ አድርገዋል።

የአካል ጉዳት ከደረሰባቸው ሰዎች ውስጥ መላው አካላቸው በመሰባበሩ ስቃይ በተሞላበት ሁኔታ በሕክምና ላይ ያሉ ሰዎች ነበሩ። ከፍተኛ ድብደባ ደርሶባቸው ከሞት የተረፉት አብዛኞቹ ሰዎች አጥቂዎቹ ገለናቸዋል ብለው ጥለዋቸው የሄዱ ሰዎች ናቸው። አጥቂዎቹ ከፈጸሙት ድብደባ፣ ግድያና ንብረት ማውደም በተጨማሪ ተጎጂዎችንና የተጎጂ ቤተሰቦችን ብሔርን መሰረት ያደረጉ ስድቦች ሲሳደቡ፣ ሲያንቋሽሹ፣ ሲያስፈራሩና ሲዝቱባቸው እንደነበርና ይህም ሰላማዊ ነዋሪዎች በብሔር ወይም በኃይማኖታቸው ምክንያት ለጥቃት የመጋለጥ ከፍተኛ ስጋትና የሥነ-ልቦና ጭንቀት እንደፈጠረባቸው ኢሰመኮ ተገንዝቧል።

በሰው ሕይወት እና አካል ላይ ከደረሰው ጉዳት በተጨማሪ 6468 ሰዎች በቤት እና ንብረታቸው ላይ በተፈጸመ ጥቃት ወይም ለደኅንነታቸው በመስጋት ከመኖሪያቸው ተፈናቅለው በቤተ-ክርስትያን እና በመንግስት ጊዜያዊ መጠለያ ጣቢያዎች ይገኙ ነበር። በንብረት ላይ ከፍተኛ ውድመት የደረሰ ሲሆን፥ መኖሪያ ቤቶችን፣ ንግድ ቤቶችን፣ የግል

እና የመንግስት ተሽከርካሪዎችን ጨምሮ ከ900 በላይ በሚሆኑ ንብረቶች ላይ ቃጠሎ፣ ዝርፊያ እና ውድመት ተፈጽሟል።[1]

ኮሚሽኑ በምርመራው የሰበሰበውን መረጃ ከሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች አንፃር በመተንተን የሚከተሉትን ግኝቶች ለይቷል።

## *በሰብአዊነት ላይ የተፈጸመ ወንጀል (crime against humanity)*

ኮሚሽኑ ባደረገው ምርመራ መሰረት የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ በኦሮሚያ ክልል ልዩ ልዩ አካባቢዎች በጥቃቱ በተሳተፉ ሰዎችና ቡድኖች በሲቪል ሰዎች ላይ የተፈጸሙት ጥቃቶች በሰብአዊነት ላይ የተፈጸመ ወንጀል ባሕርያትን የሚያሟሉ ናቸው፡ ፡

በተለይም፥

- በአብዛኛው በቡድን የተደራጁ ሰዎች ከቦታ ቦታ እየተንቀሳቀሱ ብዙ ሲቪል ሰዎችን በአሰቃቂ ሁኔታ መግደላቸው፣ የአካል እና የሥነ-ልቦና ጉዳት ማድረሳቸው፣ ንብረት ማውደማቸው እና ነዋሪዎችን ማፈናቀላቸው፤

- ድርጊቱ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. ሌሊት ጀምሮ እስከ ሰኔ 24 ቀን 2012 ዓ.ም. ድረስ የቀጠለ መሆኑ እና ቢያንስ በ40 የተለያዩ ቦታዎች ተስፋፍቶ የተፈጸመ ጥቃት መሆኑ፤

- ጥቃቱ ያነጣጠረው በከፊል በብሔር እና ኃይማኖታቸው ተለይተው የተመረጡ ሰዎችን ከየቤታቸው ለይቶ በማሳደድ እና በማጥቃት፣ በከፊል ብሔርና ሃይማኖት ሳይለይ ሰላማዊ ነዋሪዎችን ወይም ሲቪል ሰዎችን ሆነ ብሎ በማጥቃት የተፈጸመ የወንጀል ድርጊት መሆኑ፤ እንዲሁም

- በወቅቱ በማኅበራዊ ሚዲያ እና በተወሰኑ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ይተላለፍ ከነበሩት መልዕክቶች እና በወንጀል ድርጊቱ ይሳተፉ የነበሩ ሰዎች እና ቡድኖች ያሰሟቸው ከነበሩት መፈክሮች አንጻር፤

በወንጀል ድርጊቱ ሲሳተፉ የነበሩት ሰዎች፤ ተግባራቸው ስልታዊ እና የተቀናጀ ወይም የሰፊ ጥቃት አካል መሆኑን በማወቅ የተሳተፉበት እንደነበር ያሳያል። በአጠቃላይ በዚህ ሪፖርት በዝርዝር እንደተመለከተው በጥቃቱ በተሳተፉት ሰዎች በቡድን በመሆን የተፈፀሙት ጥቃቶች እንደ ተራ ወንጀል ብቻ የሚቆጠር ሳይሆን ጠቅላላ ድርጊቱና ውጤቱ በሰብአዊነት ላይ የተፈጸመ (crime against humanity) የግፍና ጭካኔ ወንጀል (atrocity crime) ስለመሆኑ የሚያሳዩ ናቸው።

[1] በክልሉ ሌሎች አካባቢዎች የደረሰውን ጉዳት የሚመለከት ዝርዝር መረጃ እና በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ኮሚሽኑ ከኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መረጃ የጠየቀ ቢሆንም ይህ ሪፖርት ይፋ እስከተደረገበት ጊዜ ድረስ ምላሽ አላገኘም።

## ግድያ፣ አካላዊ ጥቃት፣ የንብረት ውድመት እና የዜጎች መፈናቀል

ኮሚሽኑ ምርመራ ባደረገባቸው 40 የኦሮሚያ አካባቢዎች የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ መገደል ከተሰማበት ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. ምሽት ጀምሮ ሰዎች በሰልፍ መልክ እና በቡድን ወደ ጎዳና በመውጣት፣ ጎማ በማቃጠል እና ድንጋይ ደርድሮ መንገድ በመዝጋት እንቅስቃሴዎች ከጀመሩ በኋላ፣ ሰዎችን ማጥቃት እና ንብረት ማውደም የጀመሩ ሲሆን በማግስቱ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. ሁኔታው ተባብሶ ቀጥሏል።

ወደ አደባባይ/ጎዳና የወጡ ሰልፈኞች ከፍተኛ ሁከት እና ጥቃት ባሥነሱባቸው አካባቢዎች በሰላም የሚኖሩ ሲቪል ሰዎች ሁከት በአሥነሱ ሰዎችና ቡድኖች በየቤታቸው እና በየጎዳናው በግፍና በጭካኔ በዱላ፣ በጩቤ፣ በመጥረቢያ፣ በስለት ብረት፣ በድንጋይ እና በኤሌክትሪክ ገመድ ተደብድበው ተገድለዋል፣ የአካል እና የሥነ-ልቦና ጉዳት ደርሶባቸዋል፣ ቤት እና ንብረታቸው ሆነ ተብሎ በእሳት ተቃጥሎ ወድሟል፣ በከፊልም ተዘርፏል። በዚህም የተነሳ ሰዎች ከመኖሪያቸው ተፈናቅለዋል፣ በግል ድርጅቶች፥ በመንግስት እና በፖለቲካ ፓርቲዎች ንብረት ላይም ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል።




የጥቃቱ ባሕሪ እና መጠን እንደ የአካባቢው ሁኔታ የሚለያይ ቢሆንም በአመዛኙ የክርስቲያን እምነት ተከታዮች በብዛት በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ጥቃቱ በአማራ ብሔር ተወላጆች ላይ ያነጣጠረ ሲሆን፤ የእስልምና እምነት ተከታዮች በብዛት በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ደግሞ በኦሮቶዶክስ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች ላይ ያነጣጠረ ነበር።

በሰዎች እና በንብረት ላይ ጥቃት ከመድረሱ አስቀድሞ ለመከላከል እና ጥቃቱን ለማስቆም የፀጥታ አካላት የነበራቸው ሚና ከቦታ ቦታ የተለያየ ሲሆን፤ በተወሰኑ አካባቢዎች የፀጥታ ኃይሉ ቅድመ ዝግጅት በማድረጉ ጉዳቱን ለመከላከል፣

ለማስቆም ወይም ለመቀነስ ተችሏል። በአንጻሩ የፀጥታ አካሉ የወንጀል መከላከል ወይም የማስቆም አቅምና ዝግጁነት ዝቅተኛ በነበረባቸው አካባቢዎች፣ በተለይም በባቱ፣ በሻሸመኔ፣ በጭሮ፣ በሀሮማያ፣ በወሊሶ፣ በአዳማ፣ በጎባ፣ በአርሲ ነጌሌ እና በአርሲ ሮቤ፣ እንዲሁም በዴራ፣ በአዳባ፣ በአጋርፋ፣ በኮፈሌ፣ በጀጁ፣ እና በኢተያ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል።

በእነዚህ ከፍተኛ ጉዳት በደረሰባቸው አካባቢዎች ጥቃት በሚፈጸምበት ወቅት የአካባቢው ሕዝብና ተጎጂዎች ለየአካባቢው አስተዳደር እና ለፀጥታ አካላት በተደጋጋሚ እርዳታ ቢጠይቁም አዎንታዊ ምላሽ አለማግኘታቸውን፣ ይልቁንም "በበላይ አካል አልታዘዝንም፣ የግለሰብ ንብረት ጠብቁ አልተባልንም፣ የምንጠብቀው የመንግስትን የልማት ተቋማትን፣ ባንኮችን እና የኃይማኖት ተቋማትን ነው" የሚል ምላሽ ሲሰጣቸው እንደነበር ለኮሚሽኑ ገልጸዋል። በተወሰኑ ቦታዎች ፖሊስ ጥቃቱን እያየ በዝምታ ማለፉን ጥቃቱ የደረሰባቸው ነዋሪዎች እና ምስክሮች በከፍተኛ ቅሬታ ለኮሚሽኑ ገልጸዋል። አንድ ተጎጂ ሁኔታውን ለኮሚሽኑ በምሬት ሲገልጹ "መንግስት ያለ አይመስልም ነበር" ብለዋል።

ስለጉዳዩ ለኮሚሽኑ ማብራሪያ የሰጡት የየአካባቢው የፀጥታ አካላትና የመንግስት ኃላፊዎች ጥቃቱ ድንገተኛ፣ በብዙ ስፍራዎች ብዙ ቁጥር ያላቸው ሰዎች የተሳተፉበት ስለነበር በሚፈለገው መጠንና ፍጥነት ለማስቆም ፈታኝ እንደነበረ ገልጸዋል። ይሁንና በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች ነዋሪዎችን ከዚህ አይነት ጥቃት አስቀድሞ ለመከላከል በክልሉ መንግስት የተደረገ በቂ የጥንቃቄ ዝግጅት አለመኖሩ፣ በተለይ ከዚህ ቀደም ይህን መሰል ብሔርን እና ኃይማኖትን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች በተፈጸሙባቸው ቦታዎች ጭምር አንዳችም ዝግጁነት አለመኖሩ ዜጎችን በአሳዛኝ ሁኔታ ለተደጋጋሚ ጥቃት እና በደል አጋልጧል።

## የህክምና አገልግሎት መስተጓጎል

ኮሚሽኑ ምርመራ ባካሄደባቸው የተወሰኑ ስፍራዎች ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች የጤና አገልግሎት እንዳያገኙ የመከላከል እና የማሰናከል ድርጊቶች እንደነበሩ ኢሰመኮ ከምስክሮች አረጋግጧል። በጉና ወረዳ ነገሌ ከተማ፣ በአርሲ ነጌሌ እና በዶዶላ የመንግስት የፀጥታ ኃይሎች የህክምና ተቋማት ውስጥ በመግባት የሰብአዊ መብት መርኆዎችን እና ግዴታዎችን በጣሰ መልኩ ተጎጂዎች ሕክምና እንዳያገኙ አንገላተዋል፣ የህክምና ባለሙያዎችን አስፈራርተዋል። በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ የህክምና ባለሙያዎች (ለምሳሌ በወሊሶ ከተማ) የህክምና አገልግሎት በሚሰጡበት ቦታ የሰብአዊ መብት ግዴታዎችን ብቻ ሳይሆን የሙያ እና የሞራል ግዴታቸውን በሚጥስ ሁኔታ ብሔርን መሰረት አድርገው አድልዎ እና ማግለል ያደርጉ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል።

## የፀጥታ አካላት ኃይል አጠቃቀም

ምንም እንኳን የፀጥታ ኃይሉን በየቦታው የገጠመው መጠነ ሰፊ የፀጥታ መደፍረስ ችግር እና የፀጥታ አባሎቹም የሕይወት መስዋእትነት በሚጠይቅ ሁኔታ በመሰማራታቸው ኃላፊነታቸው እጅግ ፈታኝ የነበረ መሆኑን መገንዘብ ቢቻልም፣ በተወሰኑ ቦታዎች የነበረው የኃይል አጠቃቀም ተመጣጣኝነት ከፍተኛ ጥያቄ የሚያሥነሳ ነው።

ኢሰመኮ ምርመራ ካደረገባቸው አካባቢዎች መካከል በጉና ወረዳ ነገሌ ከተማ፣ በአዳማ፣ በዶዶላ፣ በነጌሌ ስጋሎ፣ በአወዳይ፣ በቡራዩ እና በአምቦ ከተሞች በመንግስት የፀጥታ አካላት ጭንቅላታቸው፣ ግንባራቸው፣ ደረታቸው እና ጀርባቸው ላይ በጥይት ተመትተው የተገደሉ ሰዎች ይገኙበታል። ከተጎጂዎች መካከል ሰልፍ ውስጥ ያልነበሩ፣ በመንገድ ወይም በቤታቸው በር ላይ የተገደሉ፣ በወጣቶች እና በፖሊሶች መካከል የተፈጠረን አለመግባባት ለማሸማገል ጣልቃ የገቡ የአገር ሽማግሌዎችን ጨምሮ የአዕምሮ ህመምተኛ እና ሕፃናት ይገኙበታል።




በተወሰኑ አካባቢዎች (ለምሳሌ በአምቦ እና በጊንጪ ከተሞች) በተፈጠረው ሁከት ከሰልፈኞች እና በቡድን ተደራጅተው ከቦታ ቦታ ይንቀሳቀሱ ከነበሩ ሰዎች መካከል መሳሪያ የያዙ፣ ጥይት የተኮሱ፣ ቦምብ የወረወሩ እና የፀጥታ ኃይል አባላቱን ጭምር ያቆሰሉ እንዲሁም የገደሉ ነበሩ። ይህም በመሆኑ የፀጥታ ኃይል አባላት የጦር መሳሪያ እንዲጠቀሙ ያስገደደ ሁኔታ እንደነበር መገመት ይቻላል። ሆኖም ግን በአብዛኛው አካባቢዎች የፀጥታ ኃይል አባላት መለስተኛ ጉዳት በሚያስከትሉ መሳሪያዎች (less-lethal weapons) ሳይሆን ሕይወት ሊያጠፉ በሚችል መሳሪያዎች (lethal weapons) መጠቀማቸው ለሰልፈኞቹ፣ በአካባቢው ለነበሩ ሰዎች እና ለየፀጥታ ኃይል አባላቱ ጭምር የሕይወት እና የአካል ደኅንነት ተጋላጭነት ፈጥሯል።

ኢሰመኮ ይህን ምርመራ ባደረገባቸው እና የፀጥታ ኃይሎች በወሰዱት እርምጃ የሰው ሕይወት በጠፋባቸው በየትኛውም አካባቢ በፌዴራል ወይም በክልል መንግስት አካል የደረሰውን የሕይወት መጥፋት ምርመራ በማድረግ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የተጀመረ ስራ መኖሩን ለማረጋገጥ አልቻለም።

## ምክረ ሃሳቦች

### *ለፌደራል መንግስት እና ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት*

- የአርቲስት ሃጫሉ ግድያን ተከትሎ በኦሮሚያ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች በተለያዩ ቡድኖች በሰብአዊነት ላይ የተፈጸመ ወንጀል ስለመፈጸሙ ኮሚሽኑ ያገኛቸውን አመላካች ማስረጃዎችን መሰረት በማድረግ፣ የወንጀል ምርመራ ተደርጎ በሰብአዊ መብቶች ጥሰት የተጠረጠሩ ሰዎች ተለይተው ለፍትሐዊ የዳኝነት ሂደት እንዲያቀርቡና ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ፤
- በኦሮሚያ ክልልም ሆነ በሌሎችም የአገሪቱ አካባቢዎች የግፍ እና ጭካኔ ወንጀል (atrocity crimes) ሊከሰት የሚችል መሆኑን በመገንዘብ፣ እነዚህ አሰቃቂ ወንጀሎች እንዳይፈጸሙ የስጋት ምንጮቸን እና አመላካቾችን በመለየት መከላከል የሚያስችል ጠንካራ እና የተቀናጀ የቅድመ ማስጠንቀቂያ እና የመከላከያ ሥርዓት እንዲዘረጋ፤
- በዚህ ሪፖርት እንደተመለከተው በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸም ወንጀል (crime against humanity) በመከሰቱና ከሌሎች የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር ተዳምሮ ሲታይ፤ የዘር ማጥፋት ወንጀልን (Genocide) ጨምሮ የዚህ አይነት የግፍና ጭካኔ ወንጀሎች (atrocity crimes) ስጋት መኖሩን የሚያመላክት ስለሆነ፤ የአጥፊዎችን ተጠያቂነት ከማረጋገጥና የተጎዱ ሰዎችን መልሶ ከማቋቋም በተጨማሪ፤ መንግስት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር፤ የተሟላ የግፍና ጭካኔ ወንጀል መከላከያ ስትራቴጂ (Comprehensive Strategy for the Prevention of Atrocity Crimes) ተነድፎ በአፋጣኝ በስራ ላይ እንዲውል፤
- በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች መሰረት በሕይወት የመኖር መብት ላይ ያንዣበቡ ተጨባጭ ስጋቶችን ለማስወገድ ተገቢ እና ተጨባጭ እርምጃዎችን እንዲወሰዱ፤ በተለይም ብሔር እና ኃይማኖትን መሰረት በማድረግ ለሚፈጸም ጥቃት ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የበለጠ ጥበቃ እንዲደረግ፤
- በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ ቡድኖች የተፈጸሙ ጥቃቶችን ለመከላከል እና ለማስቆም የፀጥታ አካሉ የነበረውን ሚና እና ከጤና አገልግሎት አሰጣጥ መስተጓጎል ጋር የነበሩ ሁኔታዎችን በሚመለከት ነጻ እና ገለልተኛ ምርመራ በማድረግ ተገቢውን እርምጃዎች መውሰድ እና አጥፊዎች ለፍትሕ እንዲቀርቡ ማድረግ፤
- በመንግስት የፀጥታ ኃይል አባላት ተመጣጣኝ ያልሆነ የኃይል አጠቃቀም የነበረባቸውን አካባቢዎች ጨምሮ፤ በመንግስት የፀጥታ አካላት በተወሰደ እርምጃ ሕይወታቸው ያለፈ እና የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን በሚመለከት የእርምጃውን ሕጋዊነት እና ተመጣጣኝነት በሰብአዊ መብቶች መርኖዎች መሰረት በሚመለከታቸው ገለልተኛ አካላት ምርመራ እንዲደረግ እና አጥፊዎችን በመለየት ለፍርድ እንዲቀርቡ ማድረግ፤
- በተለያዩ ቡድኖች በደረሱ ጥቃቶች እና በመንግስት የፀጥታ ኃይል ባልደረቦች በተወሰዱ እርምጃዎች ለሞቱ ሰዎች ቤተሰቦች፣ የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን እና ንብረታቸው የወደመባቸውን ተጎጂዎች ለመካስ እና መልሶ ለማቋቋም የሚደረገው ድጋፍ መንግስት ያለበትን ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶችን የማስከበር ግዴታ መሰረት በማድረግ በይፋ ተገልጾ እንዲተገበር፤ እንዲሁም

- በቁጥጥር ስር የሚውሉ ሰዎች አያያዛቸው ሰብአዊ መብቶቻቸውን ያከበረ እንዲሆን፤ በተጠርጣሪዎች ላይ የአካል ጉዳት ያደረሱ የፖሊስ አባላት ላይ ተገቢውን ምርመራ በማድረግ ተጠያቂነት እንዲረጋገጥ፤ ኮሚሽኑ ምክረ ሃሳብ ያቀርባል።

## ለፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እና ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ

- የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ በተፈጠረው መጠነ ሰፊ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት የተሳተፉ ሰዎችን በመለየት ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ የአጥፊዎችን ተጠያቂነት ማረጋገጥና በየጊዜው ሂደቱን ለሕዝብ ይፋ ማድረግ።

## ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለጨፌ ኦሮሚያ

- በዚህ ምርመራ የተለዩትን የሰብአዊ መብቶች ጥሰት መሰረት በማድረግ የተሰጡትን ምክረ ሃሳቦች መፈፀማቸውን እንዲከታተሉ፤
- የፌደራልም ሆነ የክልሉ የፀጥታ አካላት ተግባራቶቻቸውን በሚወጡበት ጊዜ ሰብአዊ መብቶችን ባከበረ መልኩ መሆኑን ለማረጋገጥ ቁጥጥር እንዲያደርጉ፤
- በኦሮሚያ ክልልም ሆነ በሌሎች የአገራችን አካባቢዎች እየጨመረ የመጣውንና ሕዳጣን (minority) የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚፈጸሙ አድልዎ እና ጥቃቶችን የሚከታተል፣ ለኢሰብአዊ ጥቃቶች ያለውን ስጋት የሚተነትን እና የመከላከያና የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ የሚያደርግ ተቋማዊና ዘላቂ መፍትሄ የሚፈለግበት መንገድ እንዲመቻች፤
- የሰብአዊ መብቶች ጥሰት የሚደርስባቸው ሰዎችን ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች በሚያስቀምጡት ግዴታ መሰረት ወጥ እና በቂ በሆነ መልኩ መልሶ ለማቋቋም እና ለመካስ የሚያስችል የተጎጂዎች ፈንድ እንዲቋቋም እንዲደረግ ኮሚሽኑ ምክረ ሃሳብ ያቀርባል።

## ለሚዲያዎች እና ማኅበረሰብ አንቂዎች (activists)

- በኢትዮጵያ ያለውን ውስብስብ የብሔር፣ የኃይማኖት እና የፖለቲካ አውድ በጥልቀት በመረዳት እና ለግፍ እና ጭካኔ ወንጀል (atrocity crimes) ያለውን እየጨመረ የመጣ ተጋላጭነት በመገንዘብ፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አድሏዊ አመለካከት፣ ጥርጣሬን፣ መቃቃር እና ጥላቻ የሚፈጥሩና ጥቃት እንዲፈጸም ሊያነሳሱ የሚችሉ መልዕክቶችን እና ዝግጅቶችን ከማቅረብ እንዲቆጠቡ እና በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት እንዲሰሩ ኢሰመኮ ምክረ-ሃሳብ ያቀርባል።

# መግቢያ

አርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. በድንገት መገደሉን ተከትሎ በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በተከሰተው የፀጥታ መደፍረስ የሰዎች ሕይወት በአሰቃቂ መንገድ ጠፍቷል፣ የአካልና የሥነ-ልቦና ጉዳት ደርሷል፣ ንብረት ወድሟል፣ ሰዎች ከቤታቸው እና ከኑሮዋቸው በመፈናቀል ለከፍተኛ እንግልት ተዳርገዋል።

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን በተለያዩ ስፍራዎች ተከስቶ የነበረውን የሰብአዊ መብቶች ጥሰት መርምሯል። የምርመራው የጊዜ ወሰን የአርቲስት ሃጫሉ ግድያ ከተከሰተበት ከሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. ምሽት ጀምሮ ለ ሶስት ተከታታይ ቀናት የነበሩትን ክስተቶች ይሸፍናል። ምርመራው የተካሄደባቸው ቦታዎች የተመረጡት ኮሚሽኑ ባደረገው የቅድመ ምርመራ ክትትል ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት እንደተፈጸመባቸው የለያቸው አካባቢዎች ላይ ትኩረት በማድረግ ነው። በተቻለ መጠን ምርመራው ሁሉንም የመብት ጥሰት አይነቶችን፣ ተጎጂዎችን እና ሚዛናዊ የአከባቢ ስብጥርን በጠበቀ መልኩ ተከናውኗል።

## የምርመራው ዘዴ

ምርመራው ከተለያዩ ምንጮች መረጃዎችን በቃለ-መጠይቅ በመሰብሰብ እና በማጣራት፣ በአካላዊ ምልከታ፣ የሰነድ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ እና ከሰብአዊ መብቶች መርኖዎች አንፃር በመተንተን ተከናውኗል።

በዚሁ መሰረት፣ እያንዳንዳቸው 3 አባላት ያሏቸው 10 የምርመራ ቡድኖችን በማዋቀር ከሐምሌ 14 እስከ ሐምሌ 30 ቀን 2012 ዓ.ም. ድረስ በኦሮሚያ ክልል ልዩ ልዩ አካባቢዎች በአጠቃላይ በ40 ቦታዎች የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ምርመራ ስራው ተከናዉኗል። የምርመራ ቡድኑ አባሎች ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች እና ቤተሰቦቻቸውን፣ የአይን ምስክሮችን፣ የጤና ተቋማት ባለሙያዎችንና ሠራተኞችን እንዲሁም የሚመለከታቸውን የመንግስት አስተዳደር መስሪያ ቤቶች እና የፀጥታ አካላትን አነጋግረዋል።

ጉዳት ከደረሰባቸው ሰዎች እና ቤተሰቦቻቸው 148 ሰዎች፣ በሰዎች ላይ ጥቃት ሲፈጸም በስፍራው ከነበሩ የአይን ምስክሮች እና የጤና ተቋም ባለሙያዎች እና ሰራተኞች ውስጥ 101 ሰዎች፣ እንዲሁም 79 በተለያየ የአስተዳደር እርከን ደረጃ ከሚገኙ የመንግስት ሰራተኞች፣ ኃላፊዎች እና የፀጥታ ኃይል አባሎች፤ በአጠቃላይ ለ328 ሰዎች ቃለ-መጠይቅ ተደርጓል።

በተጨማሪም፣ ሁኔታውን በሚመለከት በመንግስት አካላት የተዘጋጁ ሪፖርቶች እና ሌሎች ሰነዶች፣ ከሆስፒታሎች እና ሌሎች የጤና ተቋማት የተገኙ ሰነዶች፣ ከተጎጂዎች እና ከምስክሮች የተሰበሰቡ የፎቶ፣ የቪዲዮ እና የድምጽ ማስረጃዎች እንዲሁም በተጎጂዎች ለኮሚሽኑ የቀረቡ የአቤቱታ ሰነዶችን በመረጃነት ተጠቅሟል።

ምርመራው በርካታ አካባቢዎችን የሸፈነ በመሆኑና ፈጣን የምርመራ ስልትን የተጠቀመ በመሆኑ፤ በሁሉም ስፍራዎች የሚገኙ ሁሉንም ተጎጂዎች ለማነጋገር አልተቻለም። ስለሆነም በተወሰኑ ስፍራዎች የሰው ሕይወት ከጠፋባቸው ቤተሰቦች፣ የአካል ጉዳት ከደረሰባቸው እና ንብረት ከወደመባቸው ተጎጂዎች በማሰባጠር እና አጠቃለይ ገጽታውን ሊያሳይ በሚችል መንገድ መረጃዎች እና ማስረጃዎች ተሰብስበዋል።

የግለሰቦችን እና የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን ደኅንነት ለመጠበቅ፤ እንዲሁም በልዩ ልዩ ማኅበረሰቦች መካከል ሊኖር ስለሚገባው ሰላማዊ ግንኙነት ሲባል፤ የግድ አስፈላጊ ሆኖ ሊጠቀሱ ከተገባቸው ኩነቶች በስተቀር፤ የግለሰቦች ስም እና የተወሰኑ አካባቢዎች ስሞች ወይም ልዩ መጠሪያዎች በዚህ ሪፖርት አልተገለጹም።

## በምርመራ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች፡-

- የተወሰኑ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል መንግስት የአስተዳደር እና የፀጥታ ተቋማት የስራ ኃላፊዎች የኮሚሽኑን ተግባር እና ዓላማ በአግባቡ አለመረዳት እና ለስራው ተገቢውን ድጋፍ እና እገዛ አለማድረግ፤
- ለኮሚሽኑ በአዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን በሚጻረር መልኩ በተወሰኑ ቦታዎች ከክልል መንግስት ወይም የፀጥታ ቢሮ የጽሁፍ ፍቃድ ካላመጣችሁ በሚል የኮሚሽኑን መርማሪዎች ስራ ማሰናከል እና መረጃ መከልከል፤ እንዲሁም
- በአጋርፋ የኮሚሽኑ መርማሪዎች በአካባቢው አስተዳደር ለ2 ሰዓታት ያህል መታገታቸው እና ማስረጃቸውን ለማጥፋት ሙከራ መደረጉ ናቸው።

## 1. አገራዊ እና ክልላዊ አውድ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዓብይ አህመድ ወደ ሥልጣን ከመጡበት 2010 ዓ.ም. አጋማሽ ጀምሮ በኢትዮጵያ ያለው የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ሁኔታ እንዲሻሻል ማድረግ የመንግስታቸው ዋና አጀንዳ መሆኑን በተደጋጋሚ ሲገልጹ ቆይተዋል። በእርግጥም በእሳቸው የሚመራው አዲሱ መንግስት በወቅቱ በሺዎች የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ አድርጓል፣ በትጥቅ ትግል ላይ የነበሩ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን ጨምሮ በፖለቲካ አመለካከታቸው ምክንያት ብቻ በውጪ አገር ለመኖር የተገደዱ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ወደ አገራቸው እንዲመለሱ አድርጓል፣ እንዲሁም ለሰብአዊ መብቶች ጥሰት ምክንያት የነበሩ ጨቋኝ ሕጎችን በማሻሻል እና የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽንን ጨምሮ ልዩ ልዩ የመብት እና የዴሞክራሲ ተቋማትን ለማጠናከር አበረታች ተግባራት ተከናውነዋል።

ይሁንና በአዲሱ የፖለቲካ ምኅዳር ውስጥ በተከሰተው የፖለቲካ እና የብሔር ጽንፈኝነት ምክንያት በተከሰቱ ግጭቶች እና ሕግ ለማስከበር መንግስት የነበረው አቅም ውስንነት የተነሳ፤ መደበኛ ባልሆነ መንገድ በተደራጁ ቡድኖች በሚቀሰቀሱ ግጭቶች የሰው ሕይወት ጠፍቷል፣ የአካል ጉዳት ደርሷል፣ ንብረት ወድሟል እንዲሁም ሰዎች ከመኖሪያቸው ተፈናቅለዋል። የፖለቲካ ለውጡ የፈጠረውን የፖለቲካ ምኅዳር መስፋት እና የሚዲያ ነፃነት አላግባብ የተጠቀሙበት ጽንፈኛ የብሔር እና የሃይማኖት አጀንዳ የሚያራምዱ ቡድኖች እና በመንግስት ኃላፊነት ቦታ ያሉ ግለሰቦችን ጨምሮ ግጭት ቀስቃሽ ንግግር እና ተግባር ለሰብአዊ መብቶች ጥሰት መስፋፋት አይነተኛ ምክንያት ሆኗል። ለምሳሌ፡ -

- ከሚያዚያ እስከ ነሃሴ 2010 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልል ምእራብ ጉጂ ዞን እና በደቡብ ክልል ጌዲዮ ዞን የተከሰተው ብሔርን መሰረት ያደረገ የማኅበረሰብ ግጭት ተከስቷል፤
- በቤኒሻንጉል/ጉሙዝ ክልል በተለያዩ ጊዜያት በከፊል የብሔር ማንነትን መሰረት ያደረገ፥ በአጠቃላይ ግን ሲቪል ሰዎች ላይ ያነጣጠሩ ጥቃቶች ተፈጽመዋል፤
- ጥቅምት 7 ቀን 2011 ዓ.ም. በቡራዩ ከተማ በሚኖሩ ሲቪል ሰዎች ላይ ጥቃት ተፈጽሟል፤
- በሚያዚያ ወር 2011 ዓ.ም. በአማራ ክልል ጃዊ ወረዳ በሲቪል ሰዎች ላይ በታጣቂዎች ጥቃት ተፈጽሟል፤
- ጥቅምት 12 ቀን 2012 ዓ.ም. የፌዴራል ፖሊስ ለአቶ ጃዋር መሐመድ ደህንነት ጥበቃ ተመድበው የነበሩ የፖሊስ አባላትን ማንሳቱን ተከትሎና አቶ ጃዋርም “በመንግስት የፀጥታ ኃይሎች ተከብቤያለሁ” የሚል መልዕክት በማኅበራዊ ሚዲያ በማስተላለፋቸው ሁከት ተከስቷል፤
- በጥቅምት ወር 2012 ዓ.ም. በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን በአጣዬ ከተማ እና አካባቢው ባሉ ሌሎች ከተሞች ብሔርን መሰረት ያደረገ ጥቃት ተፈጽሟል።

በእነዚህ ክስተቶች ብዙ ሰዎች ተገድለዋል፣ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፣ ንብረት ወድሟል እንዲሁም ሰዎች ከመኖሪያቸው እና ከንብረታቸው ተፈናቅለዋል።

በተለይ በኦሮሚያ ክልል የታጠቁ ቡድኖች በሚንቀሳቀሱባቸው አካባቢዎች የመንግስት ሲቪል ሰራተኞችን ጨምሮ በርካታ ሰዎች በታጣቂዎች ተገድለዋል፤ ሲቪል ሰዎች በኃይል ታግተዋል፣ ተሰውረዋል፣ ንብረታቸውን ተዘርፈዋል።

የፌዴራል እና የክልል ሕግ አስከባሪ ኃይሎችም ሰላም እና መረጋጋት ለማስፈን በሚወስዱት እርምጃ በአንዳንድ ቦታዎች ተመጣጣኝ ያልሆነ ኃይል በመጠቀማቸው ሕይወት ጠፍቷል። በሌላ በኩል የፀጥታ ኃይል አባሎችም በሕግ ማስከበር ሥራ ላይ በተሰማሩበት የሕይወት መስዋእትነት ከፍለዋል፤ ብዙዎችም የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። በዚህ አገራዊ እና ክልላዊ አውድ ውስጥ አሳዛኙ የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ድንገተኛ ግድያ ለተጨማሪ መጠነ-ሰፊ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት መነሻ ምክንያት ሆኗል።

# 2. ምርመራው በተከናወነባቸው ስፍራዎች ስለነበሩ ክስተቶች ሂደት

## *2.1. አምቦ ከተማ እና አካባቢው*

ሰኔ 24 ቀን 2012 ዓ.ም. የአርቲስት ሃጫሉ ቀብር ሥነ-ሥርዓት ላይ ለመገኘት እና ሐዘናቸውን ለመግለጽ አስከሬኑ በተቀመጠበት በአምቦ ከተማ የወላጆቹ መኖሪያ ቤት ብዙ ሰዎች ተገኝተው ነበር። በዚሁ ስፍራ የተወሰኑ ወጣቶች "አስከሬኑ ይሰጠን፤ ፊንፊኔ ነው የምንቀብረው በማለት" ጥያቄ ያነሡ ሲሆን የሟች ዘመዶች ጥያቄውን በመቃወማቸው ረብሻ ተፈጥሮ እንደነበር ምስክሮች ገልጸዋል። በወቅቱ በስፍራው የነበሩ ምስክሮች ለኮሚሽኑ መርማሪ ቡድን አባላት እንደገለጹት በአካባቢው ነዋሪነት የማይታወቁ በርከት ያሉ ወጣቶቹ "ሀጫሉ እዚህ አይቀበርም፤ በቀለ ገርባን እና ጃዋር መሐመድን መንግስት በሄሊኮፕተር አምጥቶ ካላሳየን ሬሳው ከቤት አይወጣም፤ ሃጫሉ መቀበር ያለበት አምቦ ሳይሆን ፊንፊኔ ነው፤ ከዚህ በኋላ በቀለ ገርባን እና ጃዋር መሐመድን እንጂ አብይን አናውቅም" የሚሉ መፈክሮች ያሰሙ እንደነበር አስረድተዋል።

ከዚሁ ተከትሎ አንዲት ወጣት "አስከሬኑን ሊወስዱት ነው" ብላ በመጮኋ ወጣቶቹ ወደ የፀጥታ ኃይሎቹ ድንጋይ መወራወር እና መሳደብ መጀመራቸውን፥ የሽጉጥ ድምጽም እንደተሰማ እና ቀጥሎም በማይታወቅ ሰው ቦምብ ተወርውሮ መፈንዳቱን በስፍራው የነበሩ ምስክሮች ገልጸዋል። በቦምቡ መፈንዳት በተደናገጡት የኦሮምያ ልዩ ኃይል አባሎች ተኩስ መከፈቱን እና በሃዘኑ ቤት ወደ ተሰበሰበው ሕዝብ ጭምር በመተኮሳቸው ሰዎች በጥይት ተመተው እንደሞቱ እና ከሞቱት ውስጥም ጋቢ ለብሰው ወጣቶቹን ድንጋይ አትወራወሩ እያሉ ሲከላከሉ የነበሩ የአርቲስት ሃጫሉ አጎት ልጅ አቶ አሰፋ ገብረ መድሕን እንደሚገኙበት እና ከቆሰሉት ሰዎች ውስጥም ለሃዘኑ የመጡ ሴቶችም እንደነበሩበት ምስክሮች ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

እንዲሁም በሁከቱ ወቅት ከሕዝቡ መሃል ሆነው ሽጉጥ በመተኮስ የአፀፋ መልስ ሲሰጡ የነበሩ ሰዎች እንደነበሩ እና አብዛኛው ሰው የተጎዳው በዚህ የተኩስ ልውውጥ መሆኑን ተጎጂዎች እና ምስክሮች ለኮሚሽኑ ገልጸዋል። በዚያው እለት ከቀኑ 9 ሰዓት አካባቢ በለቅሶ ቤቱ የነበረው ሁከት ከተረጋጋ በኋላ ሰዎች ወደ ቤታቸው ሲሄዱ በመንገድ ላይ ቅኝት ሲያደርጉ ከነበሩ የአገር መከላከያ ኃይል አባላት ውስጥ አንዱ በጥይት መመታቱን ምስክሮች ገልጸዋል።

የአምቦ ከተማ ፖሊስ እና የመንግስት ኃላፊዎች በሰጡት ምስክርነት ደግሞ ሰኔ 24 ቀን 2012 ዓ.ም. ከጠዋቱ 4 ሰዓት ጀምሮ የአርቲስት ሃጫሉ አስከሬን በተቀመጠበት የወላጆቹ መኖሪያ ቤት አካባቢ የነበረውን ሕዝብ በተዛባ መረጃ የሚያደናግሩ እና አስከሬኑን እንውሰድ የሚሉ ሰዎች ችግር ፈጥረዋል የሚል መረጃ በመገኘቱ የፀጥታ ኃይል አባላት ወደ ቦታው ሲሄዱ በሃዘን ቤቱ የነበሩ ታዳሚዎች ደግሞ በተዛባ መረጃ ፖሊሶች አስከሬኑን ሊወስዱ መጡ የሚል ግርግር መፈጠሩን ገልጸዋል። ሁከቱ ሆነ ተብሎ ሕገ-ወጥ ተልእኮ በነበራቸው ቡድኖች የተቀሰቀሰ መሆኑን እና በስራ ላይ በነበሩ ፖሊሶች ላይ ቦምብ በመወርወር እና ተኩስ በመክፈት ሰው መግደላቸውን እና ማቁሰላቸውን ገልጸዋል። በዚሁ እለት በሃዘን ቤቱ ከተፈጠረው ሁከት ትንሽ አስቀድሞም በከተማው ውስጥ መንግስትን የሚቃወሙ መፈክሮችን በማሰማት ሰልፍ መካሄዱን፣ ሰልፈኞቹም ወደ ፖሊስ ጣቢያ በመሄድ እስረኛ ይለቀቅ በማለት መፈክር ያሰሙ እንደነበረም ጨምረው ገልጸዋል።

የመንግስት ኃላፊዎች ለኮሚሽኑ እንደገለጹት በእነዚህ ቀናት በምእራብ ሸዋ ዞን ሌሎች አካባቢዎች ሁከት በፈጠሩት ግለሰቦች 11 ፖሊሶች በጥይት ተመተው የሞት እና የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፣ ሶስት ሲቪል ሰዎች ተገድለዋል፣ አራት ቆስለዋል፣ አንድ የፖሊስ መኪና እና አምቡላንሶች ተሰባብረዋል፣ አንድ መኪና ተቃጥሏል፣ የግለሰብ ንብረት

የሆነ ወርቅ እና 14000 ብር ተዘርፏል። እንዲሁም በደንዲ ወረዳ የመንግስት ንብረት የሆነ ሁለት ክላሽ እና ኤስ. ኬ. ኤስ. የተባሉ የጦር መሳሪያዎች ተዘርፈዋል።

ሰኔ 25 ቀን 2012 ዓ.ም. የአርቲስት ሃጫሉ የቀብር ፕሮግራም በአምቦ ከተማ እንደሚፈጸም በቴሌቪዥን በተላለፈው መረጃ መሰረት በቀብሩ ላይ ለመገኘት በአምቦ ከተማ አቅራቢያ ከምትገኘው ጉደር ከተማ ወደ አምቦ ከተማ መጥተው የነበሩ የተወሰኑ ተጎጂዎች እና የዓይን ምስክሮች ለኢሰመኮ እንደገለጹት፤ አምቦ ከተማ መሃል ሲደርሱ የአገር መከላከያ ሰራዊት ወታደሮች ካስቆሟቸው በኋላ ለምን መጣችሁ ሲሏቸው ለቀብር ነው የመጣነው ብለው ቢመልሱም ከወታደሮቹ ውስጥ "ሃጫሉ ወደ ሄደበት ቦታ መሄድ ካልፈለጋችሁ በስተቀር ቀብር መሄድ አትችሉም" ቢሏቸውም "እንመለስም" ብለው ቁጭ በማለታቸው ተኩስ እንደከፈቱባቸው፤ ከፊት ከነበሩት ሰዎች ውስጥ በጥይት ተመተው የሞቱ እና የቆሰሉ መሆኑን ገልጸዋል። ተኩሱ የቆመው ሕዝቡ ሲሸሽ እንደነበረ ገልጸዋል። በሌላ በኩል በዚሁ ዕለት ከቀኑ 5 ሰዓት አካባቢ ከአምቦ ከተማ ወደ አዲስ አበባ መውጫ በኩል የቀብር ሥነ-ሥርዓትቱ ላይ ለመገኘት ሁሉቃ ወንዝ ጋር ተሰብስበው መፈክር ሲያሰሙ የነበሩ ሰዎችን ወደ ከተማው ማለፍ አትችሉም በሚል ከመከላከያ ሰራዊት እና የፖሊስ አባላት ጋር ክርክር እና ግርግር ተፈጥሮ በመጀመሪያ በአስለቃሽ ጭስ ለመበተን ተሞክሮ እንደነበር፤ በኋላ ግን የጥይት ተኩስ በመከፈቱ የሞቱ እና የተጎዱ ሰዎች እንደነበሩ የአይን ምስክሮች ለኢሰመኮ አስረድተዋል።

በአምቦ ከተማ ከሰኔ 24 እስከ ሰኔ 25 ቀን 2012 ዓ.ም. በተከሰተው የፀጥታ መደፍረስ ችግር 12 ሰዎች በጥይት ተመትተው መሞታቸው እና 42 ሰዎች የአካል ጉዳት የደረሰባችው መሆኑን ከአምቦ ዩኒቨርሲቲ ሪፈራል ሆስፒታል እና ከአምቦ አጠቃላይ ሆስፒታል የተገኘው የህክምና ማስረጃ ያመለክታል። ከነዚህም ውስጥ የመከላከያ ሰራዊት እና የኦሮሚያ ክልል ልዩ ኃይል አባላት በወሰዱት እርምጃ የሞቱ እና የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች አሉ።

ከአምቦ ከተማ ፖሊስ እና ከከተማው መስተዳድር የስራ ኃላፊዎች በተገኘው መረጃ መሰረት ሰኔ 24 ቀን 2012 ዓ.ም. አራት ሲቪሎች እና አንድ የፀጥታ ኃይል ባልደረባ ሲገደሉ በ14 ሰለማዊ ሰዎች እና በአራት የፀጥታ ኃይል አባላት ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል። ከዚህ በተጨማሪም በአጠቃላይ በአምቦ ከተማ አንድ የቀበሌ ጽ/ቤት፣ የከተማው የመንገድ ትራንስፖረት ጽ/ቤት ተሽከርካሪ፣ አንድ የግለሰብ ሆቴል፣ አንድ መኖሪያ ቤት፣ እና አንድ የጀሶ ፋብሪካ ላይ ጉዳት መድረሱን ገልጸዋል።

የአምቦ አካባቢ አስተዳደር አካላት ለኢሰመኮ እንደገለጹት የአርቲስት ሃጫሉ ሞት እንደተሰማ የሰላም መደፍረስ ችግር እንደሚነሳ ገምተው እንደነበር እና በተለይም በቀብሩ እለት ለፀጥታ ጥበቃ በቂ ዝግጅት በማድረጋቸው በለቅሶ ቤቱ የተፈጠረውን ረብሻ የፌደራሉ እና የክልሉ የፀጥታ ኃይሎች ፈጥነው ባይቆጣጠሩት ጉዳቱ የከፋ ሊሆን ይችል ነበር ብለዋል። ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. ምሽት ላይ የክልሉ መንግስት ከፌደራል መከላከያ ሰራዊት ድጋፍ ጠይቆ ወዲያውኑ ከምሽቱ 2 ሰዓት ጀምሮ የፌደራል መከላከያ ሰራዊት አባላት ወደ አምቦ ከተማ እና አካባቢው በመግባት ቁልፍ ቦታዎች ላይ ጥበቃ ማድረግ ባይጀምሩ ኖሮ የቀብር ሥነ-ስርአቱን በሰላም ለመፈጸም አስቸጋሪ ሊሆን ይችል እንደነበር ለኢሰመኮ ገልጸዋል።

እንደ አምቦ ከተማ ፖሊስ እና የአካባቢው አስተዳደር ኃላፊዎች አስተያት፤ ለሰላም መደፍረሱ እና በሰው እና በንብረት ላይ ለደረሰው ጉዳት ዋነኛው ምክንያት ኦነግ ሸኔ የተባለው ቡድን ከተወሰኑ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮንግረስ (ኦፌኮ) ፓርቲ አባላት ጋር በመቀናጀት የፈጠሩት ረብሻ እና ጥቃት ነው። በተጨማሪም ከዚህ በፊትም የኦነግ ሸኔ አባላት በተለያዩ ጊዜያት 39 ሰዎችን መግደላቸውን፤ ንብረት መዝረፍ እና ማቃጠላቸውን፤ በተያዙት አባሎቻቸው

የባንክ ሂሳብ ውስጥ ከፍተኛ የገንዘብ መጠን መገኘቱን፤ እንዲሁም ቀውሱ በተከሰተባቸው ሁለት ቀናት የኦነግ ሸኔ ቡድን አባላት በመንግስት መስሪያ ቤቶች ላይ ጉዳት ለማድረስ ሲሞክሩ በአገር መከላከያ ሰራዊት አባላት ከነሙሉ ትጥቃቸው በቁጥጥር ስር መዋላቸውንም ጨምረው ገልጸዋል። በአንጻሩ በተለይ ኦፌኮ እና ኦነግ መንግስት አባሎቻችንን እና ደጋፊዎቻችንን አለአግባብ እያሳደደ፣ እያሰረ እና እያጉላላ ነው ሲሉ ለኮሚሽኑ አቤቱታ አቅርበዋል።

በአምቦ ከተማ በግለሰቦች ንብረት ላይ የደረሰውን ጥቃት እና ጉዳት በተመለከተ ተጎጂዎች ለኮሚሽኑ ሲገልጹ፤ በጥቃቱ የተሳተፉት ሰዎች እና ቡድኖች "ነፍጠኛ" እያሉ መፈክር በማሰማት ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ ስለነበር፤ የተፈፀመው ጥቃት የብሔር ማንነትን መሰረት ያደረገ ነበር ብለዋል።

የኦሮሚያ ክልል ኃላፊዎች በበኩላቸው በግድያ፣ አካል ጉዳት በማድረስ፣ ንብረት በማውደም እና በአጠቃላይ በብጥብጡ ተሳትፈዋል ተብለው የተጠረጠሩ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን፣ ከነዚህ መካከልም ይህ ሪፖርት በሚዘጋጅበት ወቅት በተወሰኑት ላይ ክስ መቅረቡን፣ ከፊሎቹ በምክር እና በነጻ ተለቀዋል። በሌላ በኩል በወቅቱ ገና በቁጥጥር ስር ያልሆኑ ተጠርጣሪዎች መኖራቸውን ኃላፊዎቹ ለኮሚሽኑ ገልጸዋል።

ለተጎጂዎች የሚደረግ ድጋፍ በሚመለከት፥ የንብረት ጉዳት ደርሶብናል ብለው አቤቱታ ላቀረቡ ግለሰቦች ጥያቄያቸው ለዚሁ ጉዳይ በተቋቋመ የምርመራ ቡድን እየተጣራ እንደሚገኝ በመንግስት አካላት የተገለጸ ሲሆን፤ ተጎጂዎች በበኩላቸው ከነጻ ህክምና ውጪ ለሟች ቤተሰቦችም ሆነ ንብረታቸው ለወደመባቸው ሰዎች የተደረገ ድጋፍ አለመኖሩን ገልጸዋል።

## 2.2. ጭሮ ከተማ

በጭሮ ከተማ ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. ምሽት የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያ ከተሰማ ጀምሮ በከተማዋ ከባድ የሃዘን ድባብ ነበር። እስከ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. ከጠዋቱ 4 ሰዓት ድረስ የከተማዋ አጠቃላይ ሁኔታ ሰላማዊ የነበረ ቢሆንም፤ ከጠዋቱ 4 ሰዓት በኋላ በተነሳው ሁከት የሰዎች ሞት እና የአካል እና የንብረት ጉዳት ደርሷል።

> "ሰኔ 23 ቀን 2013 ዓ.ም. ሰው ሞቶብን ከቀብር ወደ ቤት ስንመለስ በግምት ከ150 እስከ 300 የሚሆኑ ሰልፈኞች 'ሆ!' ብለው በመጮህ ድንጋይ መወርወር ጀመሩ፤ እኛም ወደ ቤት ገባን። ሰልፈኞቹ ዱላ፣ ሜንጫ እና ድንጋይ ይዘው ነበር። ከዚያም ሟች ከራሱ ግቢ ወጥቶ ወደ ሌላ ግቢ ሲገባ ተከትለውት ሄደው እዚያው ገደሉት። የሟች ቤትና ንብረትንም ሙሉ በሙሉ አውድመዋል። ሟች ሰልፈኞቹ ሲያሳድዱት ለሚያውቃቸው ፖሊሶች ስልክ እየደወለ ነበር፤ የደረሰለት ግን የለም።"
>
> *አንድ ተጎጅ የተናገሩት*

ከአይን ምስክሮች፣ ከአካባቢው አስተዳደር ኃላፊዎች እና ከጭሮ ጠቅላላ ሆስፒታል በተገኘ መረጃ መሰረት በጭሮ ከተማ ከተከሰተው ሁከት ጋር በተያያዘ ሶስት ሰዎች ሞተዋል። ከሟቾቹ ውስጥ አንዱ በሁከት ፈጣሪዎች በደረሰበት ጥቃት የተገደለ ሲሆን፤ ሁለቱ ደግሞ በፀጥታ ኃይሎች መገደላቸውን ለማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም በ44 ሰዎች ላይ (5 ሴት እና 39 ወንድ) የአካል ጉዳት እንዲሁም የ70 ሰዎች ንብረት ላይ ጉዳት ደርሷል።

በሁከት አድራጊዎች የተገደሉት ግለሰብ ቤተሰቦች ለኢሰመኮ እንደገለጹት "ሰኔ 23 ቀን 2013 ዓ.ም. ሰው ሞቶብን ከቀብር ወደ ቤት ስንመለስ በግምት ከ150 እስከ 300 የሚሆኑ ሰልፈኞች 'ሆ!' ብለው በመጮህ ድንጋይ መወርወር ጀመሩ፤ እኛም ወደ ቤት ገባን። ሰልፈኞቹ ዱላ፣

ሜንጫ እና ድንጋይ ይዘው ነበር። ከዚያም ሟች ከራሱ ግቢ ወጥቶ ወደ ሌላ ግቢ ሲገባ ተከትለውት ሄደው እዚያው ገደሉት። የሟች ቤት ንብረትንም ሙሉ በሙሉ አውድመዋል። ሟች ሰልፈኞቹ ሲያሳድዱት ለሚያውቃቸው ፖሊሶች ስልክ እየደወለ ነበር፤ የደረሰለት ግን የለም።”

በወቅቱ በጭሮ ከተማ የነበሩ ሌሎች ምስክሮች እና ተጎጂዎችም ለኢሰመኮ እንደገለጹት ሰልፈኞቹ የፀጥታ አስከባሪዎች ላይ ድንጋይ ይወራወሩ እንደነበር እና በዚህም ምክንያት በፀጥታ ኃይል አባሎቹ ላይ ጉዳት መድረሱን፤ የፀጥታ ኃይሉ ሁኔታውን ለማረጋጋት በሚመስል መልኩ ተኩስ መጀመሩን እና በፀጥታ ኃይል አባላት በተተኮሰ ጥይት ሰዎች መሞታቸውን እና መቁሰላቸውን አስረድተዋል። የሰልፈኞቹን እንቅስቃሴ እና ድርጊት በተመለከተም በመጀመሪያ ንብረት ይዘርፉ እንደነበር እና ቀጥሎም ወደ ንብረት ማውደም በመሸጋገር በመንገድ ዳር ቆሞ ከነበረ የነዳጅ ማመላለሻ ቦቴ መኪና ላይ ነዳጅ እየቀዱ ቤቶችን እና በመንገድ ላይ ቆሞ የነበረ መኪና እንዳቃጠሉ ገልጸዋል። በተጨማሪም በሁከቱ ሲሳተፉ የነበሩት ሰዎች የጭሮ ከተማ ነዋሪዎች ብቻ ሳይሆኑ፤ ከአጎራባች የገጠር ቀበሌዎች የመጡ እና በአካባቢው ነዋሪነት በማያውቋቸው ሰዎች ጭምር መሆናቸውን አስረድተዋል።

> “ መከላከያዎች ሲመጡ ባንክ ለመጠበቅ ተብለን ነው የመጣነው አሉ፤ ፖሊሶችም ምንም ጥበቃ አላደረጉልንም፤ በሁከቱ የሚሳተፉትን ለመበተን እንኳ ጥይት ወደ ሰማይ አልተኮሱም። ከጠዋቱ 2 ሰዓት እስከ ቀኑ 6 ሰዓት ድረስ ድብደባ ነበር፤ ነገር ግን አንድም የሕግ አስከባሪ አካል አልደረሰልንም፤ ሁከት ፈጣሪዎቹ አጥፍተው ሲበቃቸው ነው የሄዱት። ፖሊስ ከአቅሙ በላይ ነበር፤ መከላከያ ሰራዊት የመጣው ጉዳት ከደረሰ በኋላ ነው። ”
>
> *አንድ ተጎጅ የተናገሩት*

ንብረታቸው ከጥቃት የተረፈላቸው የከተማው ነዋሪዎች ንብረታቸው እና ሕይወታቸው የተረፈው በፀጥታ ሃይሎች ጥበቃ ስለተደረገላቸው መሆኑን እና ከተማው በቅፅበት ድብልቅልቁ በመውጣቱ የፀጥታ ሃይሉ በአንድ ጊዜ ሁሉም ቦታ መድረስ አለመቻሉን ገልጸዋል። በሁከቱ ንብረታቸው የወደመባቸው የከተማው ነዋሪዎች በበኩላቸው፤ ቀደም ሲልም የጥቃት ስጋቶች ይታዩ እንደነበር እና መንግስት አፋጣኝ የእርምት እርምጃ ባለመውሰዱ የተከሰተ የከፋ ችግር ነው በማለት ቅሬታቸውን ገልጸዋል። ንብረታቸው የወደመባቸው አንድ ግለሰብ ለኮሚሽኑ ሲገልጹ “መከላከያዎች ሲመጡ ባንክ ለመጠበቅ ተብለን ነው የመጣነው አሉ፤ ፖሊሶችም ምንም ጥበቃ አላደረጉልንም፤ በሁከቱ የሚሳተፉትን ለመበተን እንኳ ጥይት ወደ ሰማይ አልተኮሱም። ከጠዋቱ 2 ሰዓት እስከ ቀኑ 6 ሰዓት ድረስ ድብደባ ነበር፤ ነገር ግን አንድም የሕግ አስከባሪ አካል አልደረሰልንም፤ ሁከት ፈጣሪዎቹ አጥፍተው ሲበቃቸው ነው የሄዱት። ፖሊስ ከአቅሙ በላይ ነበር፤ መከላከያ ሰራዊት የመጣው ጉዳት ከደረሰ በኋላ ነው።” ብለዋል

በጭሮ ከተማ ጥቃት የደረሰባቸው ብዙ ሰዎች እና ቤተሰቦች ጥቃቱ ብሔርን እና ሃይማኖትን መሰረት ያደረገ ስለመሆኑ ይስማማሉ። ለዚህ በማሳያነት የሚጠቅሱትም ጥቃት ፈጻሚዎቹ “ይህ የኦሮሞ ነው አትንካ፥ እሷ/እሱ አማራ ወይም ክርስቲያን ስለሆኑ ንብረቱን አጥፉ” ሲሉ እንደነበር ገልጸዋል። በተጨማሪም ሁከት ፈጣሪዎቹ “ነፍጠኛ!” እያሉ እየጮሁ ድንጋይ መወርወራቸውን፤ በተለይ ክርስቲያን ብቻ እየተለየ መደብደቡን እና ንብረት መውደሙን፤ በአባ ኮራን ሰፈር ያሉ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ የክርስቲያን ቤቶች እየተለዩ መቃጠላቸውን፤ እንዲሁም አንዷትን ሴት “አንቺ ትግሬ ነሽ ... መቀሌ ሂጂ” ሲሉ እንደነበር አስረድተዋል።

የጭሮ ከተማ ፖሊስ ለኮሚሽኑ እንደገለጸው ይህ ሪፖርት በሚዘጋጅበት ወቅት ጥቃት በመፈጸም የተጠረጠሩ 119 ሰዎች በቁጥጥር ስር ውለዋል።

ተጎጂዎች ለኮሚሽኑ እንደገለጹት የአካባቢው ሕዝብ የዕለት ምግብ በማቅረብ ደግፏቸዋል። የመንግስት አካላት መጥተው የጎበኟቸው ቢሆንም ኢሰመኮ ለምርመራ ስራው መረጃ እስከሰበሰበበት ቀን ድረስ ምንም ድጋፍ እንዳላደረጉላቸው አስረድተዋል። የአካባቢው አስተዳደር አካላት በበኩላቸው በየቀበሌው ኮሚቴ አዋቅረው ከህብረተሰቡ እርዳታ እየተሰበሰበ እንደሆነ ገልጸዋል።

## 2.3. መተሃራ ከተማ

በመተሃራ ከተማ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. የአርቲስት ሃጫሉ ሞት ከተሰማ በኋላ የተወሰኑ ወጣቶች ሐዘናቸውን ለመግለጽ በሚመስል መልኩ ወደ ጎዳና መውጣት ጀመሩ። ሆኖም ከጠዋቱ 4 ሰዓት ጀምሮ ሁኔታው ወደ ሁከት እና ጥቃት ማድረስ ተቀይሯል።

በተፈጠረው ሁከት 1 ሰው ሲገደል፤ ሁከት ፈጣሪዎች በሰነዘሩት ጥቃት ደግሞ 2 ሴቶች የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። በ48 ሰዎች ንብረት ላይ ጉዳት ደርሷል። ተጎጂዎች እና ምስክሮች ለኢሰመኮ እንዳስረዱት፥ ወጣቶቹ 'ሆ…!' ብለው በመጮህ መምጣታቸውን እና በሆቴሎች እና መኪናዎች ላይ ድንጋይ በመወርወር ጉዳት አድርሰዋል፤ ሰዎችንም ይደበድቡ ነበር።

ኢሰመኮ ያነጋገራቸው ተጎጂዎች እንዳስረዱት ጥቃቱ የተፈጸመባቸው አንዳንድ ቦታዎች ላይ የፀጥታ ኃይል ባልደረቦች ቢኖሩም ለመከላከል አልቻሉም፤ በሌሎች ቦታዎች ደግሞ የፀጥታ አካላት ስልክ ቢደወልላቸውም ምላሽ አልሰጡም። ረብሸኞቹ በሁለት ዙር ተመላልሰው ጥቃቱን ሲፈጽሙ የፀጥታ አካላት ለመከላከል ያደረጉት ጥረት ደካማ ነበር።

የጥቃቱን አጠቃላይ ባህሪ በተመለከተ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ለኮሚሽኑ እንዳስረዱት ጥቃቱ ብሔርን መሰረት ያደረገ መሆኑን እንደሚያምኑ እና ለዚህም ማሳያው በከተማው ውስጥ ካሉት ሆቴሎች ውስጥ በተለይ ተመርጠው ጉዳት የደረሰባቸው የትግራይ ተወላጆች ንብረት መሆኑን ገልጸዋል።

ለተጎጂዎች የተደረገ ድጋፍን በሚመለከት የመንግስት አካላት ወደ ከተማው መጥተው ጉዳት የደረሰበትን ንብረት መዝግበው ከመሄድ ውጪ ኢሰመኮ ማስረጃ እስካሰባሰበበት ቀን ድረስ የተደረገላቸው ድጋፍ እንደሌለ ተጎጂዎች ለኮሚሽኑ ገልጸዋል።

## 2.4. ሀሮማያ ከተማ

በሀሮማያ ከተማ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. የአርቲስት ሃጫሉ ሞት ከተሰማ በኋላ የተወሰኑ ወጣቶች ሐዘናቸውን ለመግለጽ በሚመስል መልክ ወደ አደባባይ/ጎዳና የወጡ ሲሆን፤ ሁኔታው ወዲያው ወደ ሁከት እና ጥቃት መፈፀም እንደተቀየረ ከተጎጂዎች፣ በስፍራው ከነበሩ ምስክሮች እና ከአካባቢው የአስተዳደር አካላት ተወካዮች ከተገኙ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል።

ስለ ሁኔታው የሀሮማያ ከተማ ከንቲባ ለኮሚሽኑ ሲያስረዱ "በእለቱ ጥቂት ሰዎች መጥተው ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ፈቃድ ጠየቁ፤ እኛም እስከ ጠዋቱ 4 ሰዓት ሰልፉን እንዲጨርሱ ፈቀድን። ሆኖም ከጠዋቱ 4 ሰዓት በኋላ ሰልፉ ወደ ሁከት ተቀየረ። ከነበረን ልምድ በረብሻ ጊዜ ጉዳት የሚደርሰው በሃይማኖት እና መንግስት ተቋማት፥ እንዲሁም በባንኮች ላይ ስለነበር ለእነርሱ ጥበቃ አድርገናል። በግለሰቦች ላይ ከዚህ በፊት ይህን የመሰለ ጥቃት ተፈጽሞ አይታወቅም። 36 ቤቶች ተቃጥለዋል፤ በአጠቃላይ 46 ቤቶች ላይ ጉዳት ደርሷል። ይህ ሁሉ ጉዳት የደረሰው በአንድ ሰዓት ውስጥ ስለነበር በየቦታው መድረስ እና መከላከል አልቻልንም" ብለዋል።

ቤታቸው ሙሉ በሙሉ የተቃጠለባቸው አንዲት ሴት ሁኔታውን ለኮሚሽኑ ሲገልጹ፤ "ብዙ ወጣቶች በድንገት ድንጋይ መወርወር ጀመሩ። ከዚያም ልጆቼን ይዤ ወደ ጓሮ ኮሽም ዛፍ ስር ገብተን ተደበቅን። ወዲያውኑ ቤቱን ማቃጠል ጀመሩ። ቤቱ እውስጡ ከነበረው ዕቃ ጋር ሙሉ በሙሉተቃጥሏል። ጉዳቱ ሲደርስ ምንም የፀጥታ ኃይል በቦታው አልነበረም።" ብለዋል።

> "ከጠዋቱ ወደ 4 ሰዓት አካባቢ ሁከት ፈጣሪዎቹ በመጀመሪያ እየጨፈሩ መጥተው አማራን እናጠፋለን በማለት ዝተው ከሄዱ በኋላ፤ ከቀኑ 6 ሰዓት ላይ ተመልሰው መጥተው ድንጋይ አከታትለው ቤቴ ላይ መወርወር ጀመሩ። በመቀጠልም ንብረቱን እና እራሱን ከአደጋ ለመከላከል ፍቃድ ያለው መሳሪያዬን ተጠቅሜ ሁከት ፈጣሪዎቹን ለማባረር ወደ ሰማይ ጥይት ስተኩስ ሸሹ፤ ነገር ግን ፖሊሶች ለምን ጥይት ተኮስክ ብለው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ወሰዱኝ። ፖሊሶች ከወሰዱኝ ሁከት ፈጣሪዎቹ ተመልሰው ቤቱን አቃጠሉት፤ ቤቱን ሲያቀጣጥሉት ውስጥ የነበረችው አማቴ ከቃጠሎው ለማምለጥ ወደ ውጪ ወጥታ ስትሮጥ ተከትለዋት አስፋልት መንገድ ላይ ገድለዋታል፤ ድርጊቱ ሲፈጸምም ፖሊሶች ቆመው ሲመለከቱ ነበር።"
>
> *አንድ ተጎጅ የተናገሩት*

ንብረቱ የተቃጠለበት እና ራሱን እና ንብረቱን ለመከላከል ሞክሮ የነበረ አንድ ተጎጂ ሁኔታውን ለኮሚሽኑ ሲያስረዳ፤ "ከጠዋቱ ወደ 4 ሰዓት አካባቢ ሁከት ፈጣሪዎቹ በመጀመሪያ እየጨፈሩ መጥተው አማራን እናጠፋለን በማለት ዝተው ከሄዱ በኋላ፤ ከቀኑ 6 ሰዓት ላይ ተመልሰው መጥተው ድንጋይ አከታትለው ቤቴ ላይ መወርወር ጀመሩ" በማለት ገልጿል። በመቀጠልም ንብረቱን እና እራሱን ከአደጋ ለመከላከል ፍቃድ ያለው መሳሪያውን ተጠቅሞ ሁከት ፈጣሪዎቹን ለማባረር ወደ ሰማይ ጥይት ሲተኩስ እንደሸሹ፤ ነገር ግን ፖሊሶች ለምን ጥይት ተኮስክ ብለው ወደ ፖሊስ ጣቢያ እንደወሰዱት እና ፖሊሶች እሱን ከወሰዱት በኋላ ሁከት ፈጣሪዎቹ ተመልሰው ቤቱን እንዳቃጠሉበት፤ ቤቱ ሲቃጠል ውስጥ የነበረችው አማቱ ከቃጠሎው ለማምለጥ ወደ ውጪ ወጥታ ስትሮጥ ተከትለዋት አስፋልት መንገድ ላይ የገደሏት መሆኑን እና ድርጊቱ ሲፈጸምም ፖሊሶች ቆመው ሲመለከቱ ነበር በማለት አስረድቷል። በስፍራው የነበሩ የአገር ሽማግሌዎችም ለኮሚሽኑ መርማሪዎች ስለሁኔታው ሲገልጹ ተጎጂውን ፖሊሶች ይዘውት እንደሄዱ መስክረዋል።

ሌሎች ምስክሮችም ለኢሰመኮ እንደገለጹት ሁከት ፈጣሪ ወጣቶች ተሰብስበው ሰዎችን ሲደበድቡ እንደነበር እና ከተደበደቡት ሰዎች ውስጥ አዛውንቶች ጭምር እንደሚገኙበት፤ አንድ ማየት የተሳናቸው ጡረተኛን ከቤት አስወጥተው ቤታቸውን ማቃጠላቸውን እና ጥቃቱን ያደረሱት የከተማው ነዋሪ የሆኑ እና ከአጎራባች የገጠር ቀበሌዎችም የመጡ ወጣቶች መሆናቸውን አስረድተዋል።

ኢሰመኮ ያነጋገራቸው ተጎጂዎች እና ምስክሮች ጥቃቱ ብሔርን መሰረት ያደረገ እንደነበር እና በተለይ በአማራ ብሔር ተወላጆች ላይ ማነጣጠሩን ገልጸዋል። የአካባቢው አስተዳደር ኃላፊዎችም ሰለሁኔታው ለኮሚሽኑ ሲያስረዱ፤ አንዳንድ ቡድኖች "ነፍጠኛ ላይ እርምጃ ውሰዱ" የሚል ተገቢ ያልሆነ ፕሮፓጋንዳ ያናፍሱ ስለነበር የተሳሳቱ ግለሰቦች ይህንን መሰረት አድርገው ያደረሱት ጥቃት እንደሆነ ገልጸዋል።

ከተጎጂዎች አንዱ ስለደረሰባቸው ጥቃት ለኢሰመኮ ሲገልጹ፤ "የተወሰኑ የአካባቢው ተወላጆች ብዙ ጊዜ መንዜ እያሉ ይጠሩኛል፤ አሁንም ከሚኒሊክ ጋር እያገናኙ ነው ጥቃት ያደረሱብኝ። ቀደም ብሎም ብዙ ጊዜ ትልቁም ትንሹም ቤቴ ላይ ድንጋይ ይወረውሩብኝ ነበር። የአሁኑ አደጋ በደረሰበት ዕለት ቤቴን ከማቃጠላቸው በፊት ቤቱን የተከራዩኝ የኦሮሞ ብሔርተወላጆች ስለነበሩ እቃቸውን እንዲያወጡ ካደረጉ በኋላ ነው ቤቱን ያቃጠሉት።" ብለዋል። በተጨማሪም ከዚህ በፊት ይደርስባቸው ስለነበረው ዛቻ እና ማስፈራሪያ ለአካባቢው አስተዳደር አካላት እያሳወቁ ጥበቃ እንዲደረግላቸው ጠይቀዋቸው እንደነበር አስረድተዋል።

የንብረት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን ለመርዳት ሁለት ኮሚቴዎች ተቋቁመው ሙሉ በሙሉ የወደሙትን እና ሊጠገኑ የሚችሉ ቤቶችን የመለየት ስራ እየሰሩ ነው። ሀሮማያ ዩኒቨርሲቲም መልሶ ለማቋቋሙ ስራ የሚያግዝ 1.7 ሚሊዮን ብር ለግሷል። ከመኖሪያቸው ሸሽተው በኃይማኖት ተቋማት ተጠልለው የነበሩትን ሰዎችም በአገር ሽማግሌዎች እና በኃይማኖት አባቶች አማካኝነት ወደቤታቸው መመለሳቸውን የአካባቢው አስተዳደር አካላት ተወካዮች ገልጸዋል።

## 2.5. አወዳይ ከተማ

በአወዳይ ከተማ ከሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. ለሊት ጀምሮ ወጣቶች በአርቲስት ሃጫሉ ሞት የተሰማቸውን ሃዘን ለመግለጽ ወደ አደባባይ መውጣት እንደጀመሩ እና በኋላ ሁኔታው ወደ ሁከት እና ጥቃት ማድረስ እንደተቀየረ የአካባቢው አስተዳደር አካላት ተወካዮች ገልጸዋል።

የኢሰመኮ መርማሪዎች ከተለያዩ ምንጮች በደረሳቸው መረጃ መሰረት እስከ ሰኔ 29 ቀን 2012 ዓ.ም. ድረስ በቀጠለው ሁከት በከተማው በአጠቃላይ አምስት ሰዎች በፀጥታ ሃይሎች በተተኮሰ ጥይት ተገድለዋል።

የኮሚሽኑ መርማሪዎች ያነጋገሩት አንድ ምስክር ሰኔ 24 ቀን 2012 ዓ.ም. ሁከት ፈጣሪዎችን ለመበተን የፀጥታ ኃይሎች በተኮሱት ጥይት አንድ ወጣት ጭንቅላቱ ላይ ተመትቶ መሞቱን ገልጿል። እንዲት እናት ለኢሰመኮ እንደገለጹት ሰኔ 29 ቀን 2012 ዓ.ም. ከለሊቱ 10፡00 ሰዓት ልጃቸውን ጓደኞቹ ጠርተውት ሄዶ ሰልፉ ላይ በፀጥታ ኃይሎች በጥይት ተመትቶ ሞቷል።

የአወዳይ ከተማ የፀጥታ ዘርፍ ኃላፊዎች እንዳስረዱት ወጣቶች ከሰኔ 22 ለሊት ጀምረው መንገድ ሲዘጉና "አብይ ይውረድ" የሚል መፈክር ሲያሰሙ እንደነበር ገልፀው፤ የፀጥታ ኃይሉ ግን ጥበቃ በማድረጉ በንብረት ላይ የደረሰ ጉዳት ባይኖርም ሰኔ 23 እና ሰኔ 25 ቀን 2012 ዓ.ም. ሁኔታውን ለመቆጣጠር በፀጥታ ኃይሎች በተወሰደ እርምጃ በጥይት ተመትተው የሞቱ ሰዎች አሉ።

## *2.6. ፍቼ ከተማ*

በፍቼ ከተማ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. የአርቲስት ሃጫሉ ሞት ከተሰማ በኋላ ከጠዋት ጀምሮ ወጣቶች ሃዘናቸውን ለመግለጽ ወደ አደባባይ መውጣት እንደጀመሩ እና በኋላም ሁኔታው ወደ ሁከት እና ጉዳት ማድረስ እንደተቀየረ ከተጎጂዎች፣ በስፍራው ከነበሩ ምስክሮች እና ከአካባቢው አስተዳደር አካላት ተወካዮች የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ።

በፍቼ ከተማ በተከሰተው ሁከት በ9 ቤቶች ላይ ጉዳት ሲደርስ፤ በሁከት ፈጣሪዎች እና በፖሊስ አባላት መካከል በተፈጠረ ፍጥጫ ሶስት ሲቪል ሰዎች እግራቸው እና ታፋቸው ላይ በጥይት ተመትተዋል። የከተማው ፖሊስ በበኩሉ ተጎጂዎቹ "ከሰልፈኞቹ መካከል በተተኮሰ ሽጉጥ የቆሰሉ ናቸው" ብሏል።

> "ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. ጠዋት ወጣቶች እየጮሁ መጡ፤ በራችንን ዘግተን በተቀመጥንበት 5፡00 ሰዓት አካባቢ 'ነፍጠኛ!' ብለው በመጮህ ፀያፍ ስድብ ጭምር በመሳደብ ግቢውን ወረሩት። ከዚያም ራሴን እና ቤተሰቤን ከጥቃት ለመከላከል ስል ሁለት የተመዘገቡ ክላሽንኮቭ መሳሪያዎች ተጠቀምኩ። በአካባቢው የፖሊስ አባላት የነበሩ ቢሆንም ከጥቃት እንዲታደጉን ስጠይቃቸው 'ከአቅማችን በላይ ስለሆነ እንዴት እንርዳህ' አሉኝ። አብዛኛው የፍቼ ከተማ ሕዝብ ጥቃቱን ሊከላከልልኝ ሞክሯል። ሆኖም ግን ሆቴሌ የሚገኘው ከዋናው መንገድ ዳር ስለነበር ከፍተኛ ውድመት ደርሶበታል። እኔና ባለቤቴም የመደብደብ አደጋ ደርሶብናል።"
>
> *አንድ ተጎጅ የተናገሩት*

በሌላ በኩል ተጎጂዎች እና ተጎጂዎችን ወደ ሆስፒታል የወሰዱ ሰዎች በወቅቱ ሰልፈኞቹ ወደ ፖሊስ ጽ/ቤቱ ድንጋይ መወርወር ሲጀምሩ እና የታሰሩ ሰዎች ይለቀቁልን ብለው መፈክር እያሰሙ ወደ ጽ/ቤቱ ሲጠጉ አንድ የፖሊስ አባል በደረቱ ተኝቶ ወደ ሰልፈኞቹ ይተኩስ እንደነበር ለኮሚሽኑ ገልጸዋል።

ሰኔ 23 ቀን ጠዋት ከ7000-8000 የሚደርስ የተደበላለቀ ስሜት የነበረው ሕዝብ ሰልፍ ወጥቶ እንደነበር፤ የፍቼ ከተማ ነዋሪ ዝምተኛ ስለሆነ ይህን ቦታ ማነቃቃት አለብን ብለው የሚያስቡ የፖለቲካ አጀንዳ ያነገቡ ቡድኖች ችግር መፍጠራቸውን፤ በመጀመሪያ ኮማንዶ በሚባል ሰፈር ተሰባስበው "ነፍጠኛ አገር ለቆ ይውጣልን" እየሉ መፈክር ያሰሙ እንደነበረ እና ከዚያም በጣም ብዙ ቁጥር ያለው ሰው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ሄዶ "እስረኞችን ልቀቁልን" በማለቱ ፍጥጫ መፈጠሩን እና ጉዳት መድረሱን የፍቼ ከተማ እና በኦሮሚያ ክልል የሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር የሥራ ኃላፊዎች ገልጸዋል።

በሆቴላቸው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው አንድ ተጎጂ በእለቱ የነበረውን ሁኔታ ሲገልጹ "ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. ጠዋት ወጣቶች እየጮሁ መጡ፤ በራችንን ዘግተን በተቀመጥንበት 5፡00 ሰዓት አካባቢ 'ነፍጠኛ!' ብለው በመጮህ ፀያፍ ስድብ ጭምር በመሳደብ ግቢውን ወረሩት። ከዚያም ራሴን እና ቤተሰቤን ከጥቃት ለመከላከል ስል ሁለት የተመዘገቡ ክላሽንኮቭ መሳሪያዎች ተጠቀምኩ። በአካባቢው የፖሊስ አባላት የነበሩ ቢሆንም ከጥቃት እንዲታደጉን ስጠይቃቸው 'ከአቅማችን በላይ ስለሆነ እንዴት እንርዳህ' አሉኝ። አብዛኛው የፍቼ ከተማ ሕዝብ ጥቃቱን ሊከላከልልኝ ሞክሯል። ሆኖም ግን ሆቴሌ የሚገኘው ከዋናው መንገድ ዳር ስለነበር ከፍተኛ ውድመት ደርሶበታል። እኔና ባለቤቴም

የመደብደብ አደጋ ደርሶብናል።” ብለዋል። ሌሎች ተጎጂዎችም ጥቃት በተፈጸመባቸው ወቅት በአካባቢው የፖሊስ አባላት የነበሩ ቢሆንም “ከአቅማችን በላይ ነው” በማለት ከጥቃት እንዳልተከላከሉላቸው ገልጸዋል።

የፀጥታ መደፍረስ እንዳጋጠመ ሕዝቡን የማረጋጋት ስራ መሰራቱን፤ በማኅበር የተደራጁ የአካባቢው ሰዎችን፣ ተጽእኖ ፈጣሪ ግለሰቦችን (የአገር ሽማግሌዎች እና ታዋቂ ሰዎችን) እና በከተማው ያሉ የቀበሌ ታጣቂዎች በመጠቀም ሁከቱን ለመቆጣጠር መሞከራቸውን የአካባቢው የአስተዳደር ኃላፊዎች አስረድተዋል።

ተጎጂዎች ጥቃቱ ማንነትን መሰረት ያደረገ እንደነበረ ለኮሚሽኑ ያስረዱ ሲሆን አንድ ተጎጂ “አንተ አማራ ነህ” እያሉ ጥቃት እንደፈጸሙባቸው አስረድተዋል። የአካባቢው አስተዳደር አካላትም ወጣቶቹ “ነፍጠኛ አገር ለቆ ይውጣልን” እያሉ መፈክር ያሰሙ እንደነበር እና ሃጫሉን የገደለው የአማራ ተወላጅ ነው ብለው ባሰቡ ወጣቶች ብሔርን መሰረት ያደረገ ጥቃት እንደተፈፀመ ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

በከተማው ጥቃቱን በመፈጸም የተጠረጠሩ 8 ሰዎች በቁጥጥር ስር ውለው የነበረ ቢሆንም ኮሚሽኑ ለምርመራ በስፍራው በነበረበት ወቅት ሁሉም በምክር መለቀቃቸውን፤ ሕዝቡንና ባለሃብቶችን በማስተባበር ተጎጂዎችን ለመርዳት ኮሚቴዎች ተቋቁመው 9 ቤቶችን መልሶ ለማሰራት አስፈላጊ የግንባታ ግብዓቶች ተለይተው የወጭ ግምት ስራ መሰራቱን የከተማው አስተዳደር የስራ ኃላፊዎች አስረድተዋል።

## *2.7. ወሊሶ ከተማ*

በወሊሶ ከተማ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. ከጠዋት ጀምሮ ሐዘናቸውን ለመግለጽ ሰዎች ወደ አደባባይ እንደወጡና በኋላም ሁኔታው ወደ ሁከት እና ጥቃት ማድረስ እንደተቀየረ ተጎጂዎች፣ ምስክሮች እና የአካባቢው አስተዳደር አካላት አስረድተዋል።

> *“ ከሟች ወንድማማቾች አንደኛውን በር ዘግቶ ከቤተሰቡ ጋር በተቀመጠበት ጥቃት ፈጻሚዎቹ የግቢውን በር ነቅለው በመግባት ‘በ24 ሰዓት ውስጥ ሰፈራችንን ለቃችሁ ውጡ’ ብለው በማስፈራራት ሟችን በዱላ ጭንቅላቱን እና አንገቱን መተውታል። ጥቃት ፈጻሚዎቹ በድጋሚ 8፡00 ሰዓት አካባቢ ተመልሰው ሲመጡ ሽጉጥ ይዞ በሕግ አምላክ እያለ ወደላይ እየተኮሰ ሲወጣ ከግቢ ውጪ መንገዱ ላይ ተኝተው በሚተኩሱ የፀጥታ ኃይል ባለደረቦች ተመትቶ ወደቀ። ስልክ ተደውሎለት የመጣው ታላቅ ወንድሙም ከግቢ ውጪ አጥር ስር በተደበቁ የታጠቁ የፀጥታ አካላት በጥይት ተመትቶ እንዲሞት ተደርጓል። ”*
>
> *ምስክሮች የተናገሩት*

ከከተማው አስተዳደር ኃላፊዎች፣ ከሆስፒታል፣ ከተጎጂዎች እና ምስክሮች በተሰበሰበ መረጃ መሰረት በእለቱ 2 ወንድማማቾችን ጨምሮ 3 ሰዎች ተገድለዋል። ከነዚህ ውስጥ አንደኛው በጨቤ፣ በገጀራ፣ በመጥረቢያ እና በፌሮ ተደብድቦ፤ ሁለተኛው ደግሞ በፀጥታ ኃይሎች በጥይት ተመትቶ ሞተዋል። ሦስተኛ ሟችን በተመለከተ የሟች ዘመዶች ሟች የሞተው በመንግስት የፀጥታ ኃይሎች በጥይት ተመትቶ እንደሆነ የገለጹ ሲሆን ኢሰመኮ ከሆስፒታል ያገኘው መረጃ ደግሞ ግለሰቡ ሕይወቱ ያለፈው ከፍተኛ ድብደባ እና ጭንቅላቱ ላይ ጉዳት ደርሶበት እንደሆነ ያሳያል።

ወንድማማቾች የሞቱበትን ሁኔታ በሚመለከት ቤተሰቦቻቸው እና ምስክሮች በሰጡት ቃል መሰረት በእለቱ ጠዋት 4፡00 ሰዓት ገደማ ከሟች ወንድማማቾች አንደኛውን በር ዘግቶ ከቤተሰቡ ጋር በተቀመጠበት ጥቃት ፈጻሚዎቹ የግቢውን በር ነቅለው በመግባት "በ24 ሰዓት ውስጥ ሰፈራችንን ለቃችሁ ውጡ" ብለው በማስፈራራት ሟችን በዱላ ጭንቅላቱን እና አንገቱን መተውታል። ምስክሮቹ እንዳስረዱት "ጥቃት ፈጻሚዎቹ በድጋሚ 8፡00 ሰዓት አካባቢ ተመልሰው ሲመጡ ሽጉጥ ይዞ በሕግ አምላክ እያለ ወደላይ እየተኮሰ ሲወጣ ከግቢ ውጪ መንገዱ ላይ ተኝተው በሚተኩሱ የፀጥታ ኃይል ባለደረቦች ተመትቶ ወደቀ። ስልክ ተደውሎለት የመጣው ታላቅ ወንድሙም ከግቢ ውጪ አጥር ስር በተደበቁ የታጠቁ የፀጥታ አካላት በጥይት ተመትቶ እንዲሞት ተደርጓል"።

> " ጥቃት ፈፃሚ ወጣቶች ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን ወደ ህክምና የሚዎስዱ አምቡላንሶችን በማስቆም ቁስለኞችን በማውረድ አምቡላንሶችን ሲያባርሩ እንደነበር እና ህይወታቸው ያለፉው ሰዎች አምቡላንሱ ባይከለከል ኖሮ ምናልባትም በህይወት ሊተርፉ ይችሉ ነበር። "
>
> *ተጎጅዎች እና ምስክሮች የተናገሩት*

በከተማው በርካታ ሰዎች በጩቤ፣ በዱማ፣ በገጀራና በመጥረቢያ ተደብድበው ከባድና ቀላል ጉዳት እንደደረሰባቸው ተጎጂዎች እና በአካባቢው የነበሩ ምስክሮች አስረድተዋል። ከከተማው ሆስፒታል በተገኘው መረጃ መሰረት 57 ሰዎች የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። አብዛኞቹ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ጥቃት ከተፈፀመባቸው በኋላ ሞተዋል ተብለው በአጥቂዎቹ የተተው ናቸው። ከተደበደቡት ውስጥ ካህናትና ሴቶች ይገኙበታል። ከተጎጂዎች በተገኘው ዝርዝር መሰረት 150 ቤተሰቦች የንብረት ወድሞባቸዋል። ሶስት የግለሰብ ቤቶች ሙሉ ለሙሉ ተቃጥለዋል፤ ሌሎች ተጎጂዎች ላይ ደግሞ የቤት እቃ የማውደም፣ አጥር የማፍረስ፣ በኪስ እና በቤት ውስጥ የተቀመጠ ጥሬ ገንዘብ እና ሌሎች ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን የመዝረፍ፣ ባጃጆችን የማቃጠልና የመሰባበር፣ የተከማቸ እህል የማቃጠልና የመዝረፍ ጥቃቶች ተፈፅሟል።

ጥቃት የደረሰባቸውና ጥቃት ይደርስብናል ብለው የሰጉ 200 አባዎራዎች ከቤታቸው ተፈናቅለው በአቅራቢያው በሚገኝ ቤተክርስቲያን ተጠልለው ነበር። ሁኔታው ሲረጋጋ ወደ ቤታቸው ቢመለሱም የተወሰኑት አባወራዎች ግን ቤት ንብረታቸውን ጥለው ወደ አማራ ክልል መሰደዳቸውን ተጎጂዎች ለኮሚሽኑ ገልጸዋል።

በወሊሶ ከተማ የሚገኘው ቅዱስ ሉቃስ ሆስፒታል አስተዳዳሪዎች እንደተናገሩት በሆስፒታሉ የሚሰሩ የህክምና ባለሙያዎች የህክምና አገልግሎት ለመስጠት ፍቃደኛ አልነበሩም። በዚህም ምክንያት ተጎጂዎች የቀዶ ጥገና ህክምና አገልግሎት ለማግኘት ተቸግረው ነበር። በሆስፒታሉ ሚሰሩ የጤና ባለሙያዎች "በክልሉ ሃዘን ታውጇል" በሚል አንታዘዝም ብለው እንደነበረ እና አንድ "ሚኒሊክ" የሚባል በሽተኛ አናክምም በማለታቸው አንዲት ነርስ ስሙን ቀይራ ህክምና እንዲያገኝ ማድረጓን ተገልጿል። በተጨማሪም ጥቃት ፈፃሚ ወጣቶች ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን ወደ ህክምና የሚዎስዱ አምቡላንሶችን በማስቆም ቁስለኞችን በማውረድ አምቡላንሶችን ሲያባርሩ እንደነበር እና ህይወታቸው ያለፉው ሰዎች አምቡላንሱ ባይከለከል ኖሮ ምናልባትም በህይወት ሊተርፉ ይችሉ እንደነበር የተጎጂ ቤተሰቦች እና ምስክሮች አስረድተዋል።

> " ሲመጡብኝ ፈርቼ መሮጥ ብጀምርም ስለወደቅሁ ደርሰው-ብኝ እግሬን በዱማ ቀጠቀጡት። ሞቷል ብለው ጥለውኝ ሲሄዱ እንደ እባብ ወደ ሌላ ቦታ ተስቤ በመሰወር ሕይወቴን አተረፍኩ። "
>
> *አንድ ተጎጂ የተናገሩት*

ተጎጂዎች እና ቤተሰቦቻቸው እንደገለፁት ግድያውን፣ ድብደባውን እና የንብረት ማውደሙን የፈጸሙት መፈክር ሲያሰሙ የነበሩ ወጣቶች ናቸው። አንድ ተጎጂ የነበረውን ሁኔታና የደረሰደበትን "ሲመጡብኝ ፈርቼ መሮጥ ብጀምርም ስለወደቅሁ ደርሰውብኝ እግሬን በዶማ ቀጠቀጡት። ሞቷል ብለው ጥለውኝ ሲሄዱ እንደ እባብ ወደ ሌላ ቦታ ተስቤ በመሰወር ሕይወቴን አተረፍኩ" በማለት አስረድቷል።

በአጠቃላይ በዕለቱ ጥቃት ፈጻሚዎቹ በተደራጀ መልኩ እስከ ቀኑ 11፡00 ሰዓት ድረስ በአራት ዙር እየተመላለሱ ጥቃት ሲያደርሱ ነበር። በመጀመሪያ ዙር ዘረፋ ነበር። ከዚያም ቤት ማቃጠሉና ድብደባው ቀጠለ። ጥቃት ፈጻሚዎቹ በቀጥታ ሰፈር ውስጥ በመግባት የመኖሪያ እና የንግድ ቤት በሮችን መንቀል እና በድንጋይ መሰባበር መጀመራቸውን፤ ግለሰቦች ቤት በመግባት የጦር መሳሪያ በሃይል እንዲያስረክቡ በመጠየቅ ነዋሪዎች የጦር መሳሪያ እንደሌለ በመናገር እንዲፈትሹ ቢነግሯቸውም በዱላ ጭንቅላትና አንገትን ጨምሮ መላ ሰውነታቸውን መደብደብ፣ ሰውና እንስሳ መግደል፣ ንብረት መዘረፍ፣ የማውደምና እና የማቃጠል ተግባራትን ሲፈጽሙ ነበር።

የአካባቢው አስተዳደር እና የፀጥታ አካላት ጥቃቱን ቀድመው ለመከላከል እና ጥበቃ ለማድረግ አልሞከሩም፤ እንዲያውም በወቅቱ የአካባቢው ሰው ለየፀጥታ አካላት ቢደውሉም ምላሽ የሰጣቸው አልነበረም።

አንዳንድ ተጎጂዎች ግን የፀጥታ ኃይል ባልደረቦች ለጥቃት አድራሾቹ ደጀን ሆነው ጥበቃ ያደርጉላቸው እንደነበር ገልጸዋል። ሌሎች ተጎጂዎች በሰጡት ምስክርነትም "ፖሊስ እያየ እንዳስጠቃቸው፤ ጥቃቱ በሚፈጸምበት ወቅት ሰው ሲደበደብ እና ንብረት ሲቃጠል በአቅራቢያው የነበሩ የፀጥታ ሃይሎች ምንም እርምጃ አለመውሰዳቸውን" ገልጸዋል። አንድ ተጎጂ በሰጡት ምስክርነት "በግምት 1000 አካባቢ የሚሆኑ ወጣቶች ጥይት ስንተኩስ ተበትነው ነበር። ወዲያውኑ ልዩ ሃይል መጣ። ከዚያም ወጣቶቹ ወዲያው ተመልሰው መጥተው ቤቱን አቃጠሉት። መፈክር ሲያሰሙ የኦሮሚያ ልዩ ኃይልም ያን ተከትሎ ያሰማ ነበር" ብለዋል። ሌሎች ሁለት ተጎጂዎች ደግሞ "ልዩ ኃይሎች በሁለት የቅኝት ተሽከርካሪዎች እየዞሩ አጥቂዎቹን ሲደግፉ እንደነበረ እና የልዩ ኃይልና የከተማ ፖሊስ አባላት ጥቃት ካደረሱት ሰልፈኞች ኋላ ነበሩ" በማለት ገልጸዋል። ኮሚሽኑ ይህን ከገለልተኛ ምንጮች ለማረጋገጥ አልቻለም።

> " ጥቃት አድራሾቹ ተሰብስበው ድንጋይ መወራወርና አጥር ማፍረስ ሲጀምሩ ፍቃድ ባለው መሳሪያችን ወደ ሰማይ በመተኮስ መከላከል ችለን የነበር። ነገር ግን ተኩሱን የሰማው የፀጥታ ኃይል መሳሪያቸውን ነጥቆ በቁጥጥር ስር አድርጎ በመኪና ይዞን ሲሄድ ወጣቶቹ ተመልሰው ቤታችን ገብተው ንብረት የመዝረፍ፣ የማውደም እና የማቃጠል ድርጊት ፈፅመዋል። "
>
> *ሁለት ተጎጂዎች የተናገሩት*

ሁለት ቤታቸው የወደመባቸው እና የተከማቸ እህል የተዘረፈባቸው ተጎጂዎች በበኩላቸው ጥቃት አድራሾቹ ተሰብስበው ድንጋይ መወራወርና አጥር ማፍረስ ሲጀምሩ "ፍቃድ አለው" ባሉት መሳሪያቸው ወደ ሰማይ በመተኮስ መከላከል ችለው የነበረ ቢሆንም ተኩሱን የሰማው የፀጥታ ኃይል መሳሪያቸውን ነጥቆ እነሱን በቁጥጥር ስር በማዋል በመኪና ይዟቸው እንደሄደ እና ከዚያም በኋላ ወጣቶቹ ቤታቸው ገብተው ንብረት የመዝረፍ፣ የማውደም እና የማቃጠል ድርጊት መፈጸማቸውን አስረድተዋል።

የአካባቢው አስተዳደር አካላት አንዳንድ ተጎጂዎች መሳሪያቸውን ተነጥቀው በፀጥታ አካላት ከቤታቸው መወሰዳቸውን አምነው፤ ይህንን ያደረጉት ከጥፋት አድራጊዎቹ ጋር በነበረው መፋጠጥ መሳሪያው ሕጋዊ ቢሆንም የበለጠ ጉዳት

እንዳይደርስ እና የሰዎቹን እና የቤተሰባቸውን ህይወት ለማዳን እንደሆነ አስረድተዋል። አክለውም፥ ለንብረቱ ጥበቃ እና ከለላ ማድረግ ይገባ እንደነበር መገምገማቸውን፤ ነገር ግን የፀጥታ ኃይሉ ቁጥር አነስተኛ ስለነበር እና ችግሩ ብዙ ቦታ የሸፈነ በመሆኑ ይህንን ማድረግ እንዳልቻሉ ገልጸዋል።

አንዳንድ ተጎጂዎች ከጥቃቱ ኦሮሞ የሆኑ ጎረቤቶታቸው እንዳዳኗቸው ሲገልፁ አንዳንዶች ግን እየጠቆሙ እንዳስጠቋቸው ገልጸዋል። ተጎጂዎቹ እንደገለጹት ከሆነ ከቀኑ11 ሰዓት ላይ ጥቃቱ የቆመው በከተማው የሚገኘውን የአምቦ ዩኒቨርሲቲ ካምፓስ የሚጠብቁ የፌደራል ፖሊሶች በመድረሳቸው እና ዝናብ በመዝነቡ ነው።

የአካባቢው አስተዳደር ኃላፊዎች በእለቱ ለስብሰባ አዳማ እንደነበሩ፤ ጥቃቱን ቶሎ ለማስቆም ያልተቻለው መጀመሪያ ዋና ዋና የግል ተቋማት እና የመንግስት መስሪያ ቤቶች ላይ ጥቃት ይደርሳል በሚል ጥርጣሬ የነበረው ጥበቃ እዚያ ላይ ትኩረት በመደረጉ ከ4፡00 ሰዓት በኋላ ሁኔታው ወደ ብሔር እና ሃይማኖት ጥቃት ሲቀየር እና ጥቃቱ ድንገተኛ በመሆኑ እንዲሁም ችግሩ በአንድ ጊዜ ብዙ ቦታ ላይ በመፈጠሩ የፀጥታ ኃይሉ በመወጠሩ ነው።

ኃላፊዎቹ አክለው እንደገለጹት ዩኒቨርሲቲ ሲጠብቅ የነበረው የፌደራል ፖሊስ የፀጥታ መደፍረሱን ለመቆጣጠር ድጋፍ አድርጓል፤ ተጨማሪ የፀጥታ ኃይል በሂሊኮፕተር ጭምር እንዲገባ ድጋፍ ጠይቀው አመያ በተባለ ስፍራ የነበረ ልዩ ኃይል አመሻሽ ላይ ከተማው ገብቷል። በመሃከል መንገድ ተዘግቶ የነበረ በመሆኑ ተጨማሪ ኃይሉ በቶሎ እንዳይደርስ ችግር ፈጥሮ ነበር። ተጨማሪ ኃይል ከደረሰ በኋላ ቢያንስ በቀጣዩ ቀን ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስ ለማድረግ ተችሏል።

የወሊሶ ከተማ አስተዳደር ኃላፊዎች ጥቃቱ የበለጠ እንዳይባባስ የተወሰደው እርምጃ ተመጣጣኝ መሆኑን ገልፀው፤ የፀጥታ ኃይሉ ወደላይ በመተኮሱ ሊደርስ ይችል የነበረውን ጉዳት ለመቀነስ ተችሏል ብለዋል። በተለይ በቀጣይ ቀናት ምንም እንዳይከሰት ለማድረግ ከምዕራብ ሸዋ ዞን አስተዳደር ጋር ኮማንድ ፖስት በማቋቋም ችግሩ እንዳይሰፋ እና ህይወት እንዳይጠፋ ከገጠር የሚመጡት እንዳይገቡ በማድረግ፤ ገሊላ በሚባለው የከተማው አካባቢ የሚኖሩ የአማራ ተወላጆች እና በቤተክርስትያን ለተጠለሉ ሰዎች ጥበቃ ማድረጋቸውን ገልጸዋል።

ተጎጂዎች እና ምስክሮች ጥቃቱ ብሔርን መሰረት አድርጎ እንደተፈፀመ ለኮሚሽኑ አስረድተዋል። የጥቃቱ ምክንያት የአርቲስት ሃጫሉ መገደል ይሁን እንጂ አስቀድሞ በተዘጋጀ የስም ዝርዝር መሰረት የአማራ ብሔር ተወላጆች እየተመረጡ መጠቃታቸው፤ በተለምዶ ገሊላ የሚባለው ሰፈር በአብዛኛው የአማራ ብሔር ተወላጆች የሚኖሩበት መሆኑ ስለታወቀ አጥቂዎቹ በቀጥታ እዚያ መምጣታቸውን ጥቃቱ ብሔርን መሰረት ያደረገ መሆኑን እንደሚያመለክት ገልጸዋል። ጥቃቱ የተፈፀመባቸው ተጎጂዎች የጥቃቱ አላማ የአማራ ብሔርተወላጆችን ማፈናቀል ነው ብለው እንደሚያምኑ የገለፁ ሲሆን አንድ ተጎጂ "ጥቃት ፈጻሚዎቹ ቤት ተከራይ የሆኑ የአማራ ብሔር ተወላጆችን ንብረት አውጥተው አውድመዋል። የእናንተን ገንዘብ አንፈልግም በማለት ቀድደዋል፣ ከእናንት ጋር መኖር አንፈልግም ብለዋል። አብን አስታጥቋቸዋል በሚል ግምት እያንዳንዱ የአማራ ብሔር ተወላጅ ቤት የጦር መሳሪያ ይገኛል ሲሉ ነበር። ሆኖም ግን ከዚህ ቀደም በ2011 ዓ.ም. የአማራ ብሔር ተወላጆች መሳሪያ አላቸው ተብሎ መንግስት ሁሉም ቤት ላይ ፍተሻ አድርጎ ከአንድ ሰው ውጪ መሳሪያ አልተገኘባቸውም" በማለት አስረድተዋል። ሌላ ተጎጂ "ሃጫሉን የገደለው ነፍጠኛ ስለሆነ ከአገራችን ውጡ እያሉ ያደረሱት ጥቃት በመሆኑ ጥቃቱ ማንነትን መሰረት ያደረገ ነበር፤ የሰዎች ስም ዝርዝር ይዘው ነበር፤ መሳሪያ ስለመኖሩ ተጠቁመን ነው የመጣነው። ይሉ ነበር" ብለዋል። በተጨማሪም ከተጎጂዎቹ መካከል አንዱ "ከ2008 ዓ.ም. ጀምሮ አልፎ አልፎ የአማራ ብሔር ተወላጆች ንብረት ወድሟል፤

በየጊዜው ቆምጬ እና ስደተኛ እየተባልን ስንሰደብ እና ስንሸማቀቅ ኖረናል፤ ስጋት ያደረባቸው ቤት ሸጠው ለመውጣት ሲሞክሩ ማን ውጡ አላችሁ ይሉናል፤ ለመንግስት አካላት ጥቃት አድራሾቹን በስም እየጠራን እንኳን ስንነግራቸው ዱርዬዎች እና ቦዘኔዎች ናቸው አትስሟቸው ይሉን ነበር” ብለዋል።

የከተማው አስተዳደር አካላት ለኮሚሽኑ እንደገለፁት መረጃው በሚሰበሰብበት ወቅት ጥቃቱን በመፈጸም የተጠረጠሩ 83 ሰዎች በቁጥጥር ስር ውለው እንደነበር እና ኮሚሽኑ ምርመራ ባደረገበት ጊዜ 48 ተጠርጣሪዎች በእስር ላይ እንደሚገኙ ገልጸዋል። ተጎጂዎቹ በበኩላቸው ወንጀለኞቹ አለመያዛቸውንና የተያዙትም እየተለቀቁ መሆናቸው እንዳሰጋቸው ገልጸዋል።

ጉዳቱ ከደረሰ በኋላ ለአንዳንድ ተጎጂዎች ከነጻ የሆስፒታል ህክምናና፣ ቤታቸው ሙሉ ለሙሉ ለተቃጠለባቸው 4 ቤተሰቦች ከተሰጡት ጊዜያዊ የቀበሌ ቤቶች እንዲሁም የከተማዋ ከንቲባ የቤተሰብ አባል ለተገደሉባቸው ቤተሰቦች የማስተዛዘኛ የሚሆን ዱቄት፣ ዘይትና መኮረኒ መሰጠቱን ገልጸዋል። ይሁንና ድጋፉ በቂ አለመሆኑን ተጎጂዎች ገልጸዋል። በተጨማሪም እርዳታው ለሁሉም ተጎጂዎች ባይደርስም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፣ በኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር እና በበጎ ፍቃደኞች ድጋፍ ተደርጓል።

ተጎጂዎቹ የተደረገልን ድጋፍ በቂ ስላልሆነና አብዛኞቻችንም ሙሉ ንብረታችን ስለተቃጠለ በረሃብና በእርዛት እየተሰቃየን ነው ብለዋል። በመሆኑም ብዙዎቹ ንብረቶቻቸውን በመሸጥ የአማራ ክልል መንግስት ተረክቦ ወደ አገራችን ይመልሰን የሚል አቋም ይዘዋል። ሆኖም ንብረት ሸጦ መሄድ ለሚፈልጉ ሰዎች አስተዳደሩ መልቀቂያ ስለማይሰጣቸው መሰናክል እንደሆነባቸው ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

## 2.8. አዳማ ከተማ

ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. ከጠዋት ጀምሮ በአርቲስት ሃጫሉ ሞት ሐዘናቸውን ለመግለጽ ወጣቶች ወደ አደባባይ መውጣት እንደጀመሩና በኋላም ሁኔታው ወደ ሁከት እና ጉዳት ማድረስ እንደተቀየረ ተጎጂዎች፣ በስፍራው የነበሩ ምስክሮች እና የአካባቢው አስተዳደር አካላት አስረድተዋል።

ኮሚሽኑ ባደረገው ማጣራት መሰረት በከተማው በአጠቃላይ የ10 ሰዎች ሕይወት አልፏል። ከእነዚህም መካከል የፀጥታ ኃይሉ ሁከቱን ለመቆጣጠር በወሰደው እርምጃ 8 ሰዎች ሲገደሉ፤ 2 ሰዎች ደግሞ በሁከት ፈጣሪዎቹ በገጀራ፣ በዱላ እና በድንጋይ በፈፀሙት ድብደባ ሕይወታቸው አልፏል። ከእነዚህም ውስጥ ባለቤታቸው በተባራሪ ጥይት በመመታታቸው ወደ ሆስፒታል ሄደው ሲመለሱ በወጣቶች ተደብድበው ህይወታቸው ያለፈ ግለሰብ ይገኙበታል። በአጠቃላይ በከተማው በ72 ሰዎች ላይ ቀላል እና ከባድ የአካል ጉዳት ደርሷል። ከእነዚህ ውስጥ 22ቱ የፀጥታ ኃይሉ ባልደረቦች ናቸው። በተጨማሪም ኮሚሽኑ የጉዳቱን አይነትና መጠን ለመለየት በከተማዋ ከሚገኙት አዳማ ሆስፒታል፣ አዳማ ጀነራል ሆስፒታል እና ሪፍት ቫሊ ሆስፒታል መረጃ ሰብስቧል። በተገኘው መረጃ መሰረትም ቢያንስ 48 ሰዎች በተፈጸመባቸው ጥቃት ምክንያት ቀላልና ከባድ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል።

በከተማዋ በ15 የመንግስት ተቋማት እና 7 የመንግሰት መኪናዎች ላይ ቃጠሎ ሲደርስ በ19 የግለሰብ የንግድ ተቋማት ንብረት ላይ መሰባበር እና ውድመት ተፈፅሟል።

ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው ድብደባ የተፈፀመባቸው እና ንብረታቸው የወደመባቸው ተጎጂዎች እና ምስክሮች እንደገለጹት የመንግስት አካላት ጉዳቱ እንዳይደርስ ቀድሞ ለመከላከልም ሆነ በፍጥነት ደርሰው ጥቃቱን ለመቆጣጠር እና ጥበቃ ለማድረግ ያደረጉት ጥረት አነስተኛ ነበር። በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ የፀጥታ አካላት በቦታው ቢደርሱም የከንቲባ ፅ/ቤት መቃጠሉን ሲሰሙ ጥለው ወደ ቦታው መሄዳቸውን ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

የከተማው የአስተዳደር አካላት ስለሁኔታው በሰጡት ምላሽ የፀጥታ አካሉ ዋና ዋና የጥቃት ትኩረቶች ይሆናሉ ተብለው የተለዩ ስፍራዎችን ለመጠበቅ ቢሞክርም ጉዳቱን ለማድረስ የወጣው ኃይል እና በቦታው የነበረው የፀጥታ ኃይል ሊመጣጠን ባለመቻሉ ጉዳቱ መከሰቱን አስረድተዋል። ሁኔታው ከአቅም በላይ ሲሆን የፌደራል ፖሊስ እና የአገር መከላከያ ሰራዊት እንዲገባ ተጠይቆ የተጠየቀው ድጋፍ ጠዋት 3፡00 ሰዓት ላይ መድረሱን ገልጸዋል።

የአስተዳደር አካላት በከተማዋ የደረሰው አብዛኛው ጥቃት ብሔርን ወይም ሃይማኖትን ማዕከል ያደረገ ሳይሆን መንግስትን የመቃወም እና ሰነዶችን የማጥፋት ይዘት እንደነበረው የገለፁ ቢሆንም አንዳንድ ተጎጂዎች የደረሰባቸው ጥቃት ብሔርን መሰረት ያደረገ ነው የሚል እምነት እንዳላቸው ለኮሚሽኑ አስረድተዋል። አንድ ተጎጂ ወጣቶች ቤቱን ሲሰባብሩ “የትግሬ ቤት ነው አይደል” እያሉ እንደነበረ እና አለመሆኑን ቢናገሩም ሊተውት እንዳልቻሉ ተናግረዋል።

በመንግስት የፀጥታ አካላት በተወሰደው እርምጃ የጠፋውን ሕይወት እና የደረሰውን የአካል ጉዳት በሚመለከት የከተማው አስተዳደር አካላት ጥቃቱ የመንግስት ተቋማት (የኦሮሚያ ብሮድካስት ኔትወርክ ቢሮ)፣ ነዳጅ ማደያዎች እና ትልልቅ ሆቴሎች ላይ ያተኮረ ስለነበረ እነሱን ለመጠበቅ እና ለመከላከል በተወሰደ እርምጃ መሆኑን ገልጸዋል።

የከተማው አስተዳደር አካላት ለኮሚሽኑ እንደገለፁት መረጃው በሚሰበሰብበት ወቅት ጥቃት በመፈጸም የተጠረጠሩ 372 ሰዎች በቁጥጥር ስር ውለዋል። በመንግስት የፀጥታ አካላት እርምጃ የደረሰውን ጉዳት ለማጣራት የተጀመረ ስራ ስለመኖሩ ግን አልተገለጸም።

የንብረት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች የጉዳቱን መጠን ሰርተው ለመንግስት ቢያቀርቡም ኮሚሽኑ ለዚህ ሪፖርት መረጃ በሰበሰበበት ወቅት የተደረገላቸው ድጋፍ አለመኖሩን ተጎጂዎች ገልጸዋል። የከተማዋ የአስተዳደር አካላት በበኩላቸው ንብረታቸው የወደመባቸው ሰዎችን ለመርዳት ኮሚቴ ተዋቅሮ የማጣራት ስራ እየተሰራ እንደነበር ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

## 2.9. ዴራ ከተማ

አርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ በተገደለበት ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. ለሊት 8፡00 ሰዓት ላይ በዴራ ከተማ ጩኸት መሰማት እንደጀመረ፤ ይህንንም ተከትሎ ወጣቶች ከሌሊቱ 10፡00 ሰዓት ጀምሮ ጎማ ማቃጠል፣ መንገድ መዝጋት እና ቤቶችን ማቃጠል የጀመሩ ሲሆን ይህ ሁኔታ እስከ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. ድረስ እንደቀጠለ በስፍራው የነበሩ ምስክሮች እና የአካባቢው የአስተዳደር አካላት ገልጸዋል።

በከተማው በተፈጠረው የሰላም መደፍረስ በአጠቃላይ 15 ሰዎች ሲሞቱ ከእነዚህ መካከል1 የፖሊስ አባል፣ ጥቃት በተፈጸመበት አንድ ሆቴል ውስጥ ሲሊንደር በመፈንዳቱ በደረሰ አደጋ የሞቱ 7 ሰልፈኞች እና ሌሎች 7 ሰዎች ደግሞ በተፈጸመባቸው ድብደባ የሞቱ ናቸው።

በተፈጸመባቸው ድብደባ ከሞቱት መካከል የጥቃቱ ፈፃሚዎች ቤታቸው ድረስ በመምጣት እና ሰብረው በመግባት ሌሎች የቤተሰቡ አባላት ሲያመልጡ አንድ የቤተሰቡ አባል በመያዛቸው ደብድበው ገለውታል። ሬሳው መሬት ላይ እንደተጎተተና "የጠላት እሬሳ አይነሳም" በማለት እስከ ቀኑ 10፡00 ሰዓት ድረስ ሬሳው ሳይነሳ መቆየቱን የተጎጂ ቤተሰቦች እና ምስክሮች ለኮሚሽኑ አስረድተዋል። በተመሳሳይ ጥቃት ፈጻሚዎቹ የሌላ አንድ ግለሰብ ቤት ሰብረው በመግባት የጦር መሳሪያ አምጡ በማለት ልጆችን በመደብደብ ጉዳት ካደረሱ በኋላ ሟችን ከቤት አውጥተው ደብድበው መግደላቸውን ቤተሰቦቹ ለኢሰመኮ ገልጸዋል። ሌሎች ሁለት ሰዎች የተገደሉት ደግሞ በከተማው በሚገኘው ምእራፍ ሁቴል ውስጥ ነው። ጥቃት ፈጻሚዎቹ "የነፍጠኛ ሆቴል ውስጥ ተኝቷል" በሚል አንድ ሰው ከተኛበት ክፍል አውጥተው ቀጥቅጠው እንደገደሉት እንዲሁም የዚያው ሆቴል የጥበቃ ሰራተኛ የነበረ አንድ ግለሰብ ደግሞ ተደብድቦ ተገድሎ አስክሬኑ ተጥሎ መገኘቱን ምስክሮች ገልጸዋል።

ከሞት በተጨማሪ በከተማው በ15 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል። እንዲሁም 33 መኖሪያ ቤቶች፣ 7 ሆቴሎች፣ 31 ሱቆች፣ 4 መኪናዎች፣ 2 ትራክተሮች፣ 2 ብስክሌቶች፣ አራት ሞተር ብስክሌቶች፣ 1 ወፍጮ ቤት፣ 1 እንጨት ቤት ከነማሽኑ፣ 4 ባለ ሶስት እግር ተሽከረካሪዎች፣ 6 ጋሪዎች፣ 1 ዳቦ ቤት እና 1 የዱቄት ፋብሪካ ተቃጥለዋል። ኢሰመኮ መረጃ በሰበሰበበት ወቅት በደረሰባቸው ጉዳት ምክንያት ወይም ተመሳሳይ ጥቃት እንዳይፈፀምባቸው በመስጋት ከቤታቸው ተፈናቅለው ቤተ ክርስቲያን ተጠልለው የሚገኙ ሰዎች ነበሩ።

የመንግስት አካላት ቀድሞ ለመከላከልም ሆነ ደርሰው ለመቆጣጠር እና ጥበቃ ለማድረግ ያደረጉት ጥረት አነስተኛ እንደነበረ፤ ጥቃቱ ከለሊት ጀምሮ እስከ ቀኑ 7፡00 ሰዓት ቢቀጥልም አስተዳደሩም ሆነ የፀጥታ አካላት እንዳልደረሱላቸው እና ጉዳቱ ከደረሰ በኋላ አስክሬን ለማንሳት መምጣታቸውን ጥቃት የደረሰባቸው ተጎጂዎች እና ምስክሮች ገልጸዋል። አንድ ተጎጂ ከዚህ ቀደምም ወጣቶች ሲያስፈራሩን ለወረዳው የፀጥታ አካል ብናሳውቅም እዚያው እራሳችሁ ተከላከሉ መባላቸውን እንዲሁም በቤቱ በደረሰበት ጥቃት ህይወቱ ያለፈው ሌላ ሟች ለፖሊስ ደውሎ ቢያሳውቅም ትእዛዝ አልተሰጠንም የሚል ምላሽ እንደተሰጠው አብረውት የነበሩት ባለቤቱ ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

> "[በቤቱ በደረሰበት ጥቃት ህይወቱ ያለፈ አንድ ሰው] ማጥቃት ሲጀምሩት ለፖሊስ ደውሎ ቢያሳውቅም ትእዛዝ አልተሰጠንም የሚል ምላሽ ተሰጥቶታል።"
>
> *የሟች ቤተሰብ አባላት የተናገሩት*

የአካባቢው የአስተዳደር አካላት ለዚህ ቅሬታ እንደ ምክንያት የጠቀሱት ጥቃቱ ከአቅማቸው በላይ ስለነበረ ከለሊት 8፡00 ሰዓት ጀምሮ ልዩ ፖሊስ እንዲገባ ቢጠይቁም "ትእዛዝ አልደረሰንም" በማለት እስከ ቀኑ 7፡00 ሰዓት ልዩ ኃይሉ ባለመድረሱ የነበራቸውን መደበኛ ፖሊስ ቢያሰማሩም ጥቃቱ ተደራጅቶ መሳሪያ ታጥቆ በመጣ ኃይል፣ ከፖሊስ መሳሪያ ለመንጠቅ እና ፖሊስ ጣቢያ ለመግባት ሙከራ በማድረግ ጭምር የተፈጸመ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ መከላከል እንዳልተቻለ ገልጸዋል።

ተጎጂዎች እና ምስክሮች ጥቃቱ ሃይማኖትን እና ብሔርን መሰረት ያደረገ እንደነበር ገልጸዋል። ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ጥቃት ፈጻሚዎቹ "እናንተ የሚኒሊክ ርዝራዦች ከዚህ ትወጣላችሁ" ይሉ እንደነበረ እና የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ መሆናቸውን ቢገልፁላቸውም ክርስቲያን በመሆናቸው ንብረታቸውን እንዳቃጠሉባቸው ለኢሰመኮ ገልጸዋል።

የአካባቢው አስተዳደር አካላት የደረሰው ጥቃት የኃይማኖት እና የብሔርግጭት ለመፍጠርና በተለይም የብልጽግና ፓርቲን የሚደግፉ ባለሃብቶችን የማሸማቀቅ አላማ ያለው መሆኑን ገልጸዋል። ጥቃት ፈጻሚዎቹ በቀለ ገርባ እና ጃዋር መሐመድ ወደ ከተማዋ መጥተው በነበረበት ጊዜ በዋናነት ዝግጅቱን ያስተባበሩት በመሆናቸው የፖለቲካ አንድምታ ያለው እንደነበር ግምታቸውን ገልጸዋል።

የከተማው አስተዳደር አካላት ለኮሚሽኑ እንደገለፁት መረጃው በሚሰበሰብበት ወቅት በጥቃቱ በመሳተፍ የተጠረጠሩ 160 ሰዎች በፀጥታ አካላት ቁጥጥር ስር ውለዋል። ተጎጂዎች በበኩላቸው ከጥቃት ፈጻሚዎቹ ያልተያዙ እና አሁንም በስልክ የሚያስፈራሩ ሰዎች እንዳሉ፤ በዚህም ምክንያት ምስክርነት ለመስጠት ፍራቻ እንዳለባቸው ለኮሚሽኑ ገልጸዋል።

ከጥቃቱ አስራ አምስት ቀን በኋላ በመንግስት ለተጎጅዎች የስንዴ ድጋፍ ተደርጓል እንዲሁም መሬት ላላቸው ተጎጂዎች ዘር እና ማዳበሪያ ተሰጥቷቸዋል። ነገር ግን ተጎጂዎቹ ወደ ቤታቸው ለመመለስም ሆነ ጉዳቱን ለመካስ የተደረገው ጥረት ከደረሰው ጉዳት አንፃር በቂ አለመሆኑን ተናግረዋል።

## 2.10. አዳባ ከተማ

በአዳባ ከተማ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ሞት ከተሰማ በኋላ በግምት ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት ጀምሮ ሐዘናቸውን ለመግለጽ ብዙ ወጣቶች (ህፃናትን ጨምሮ) ወደ አደባባይ መውጣት የጀመሩ ሲሆን ቀስ በቀስ ሁኔታው ወደ ሁከት ተቀይሯል።

በተከሰተው ሁከት በከተማዋ እና አጎራባች ቀበሌዎች በአጠቃላይ 6 ሰዎች ሞተዋል። የከተማው አስተዳደር አካላት እንደገለፁት በከተማው ውስጥ ብቻ 3 ሰዎች ሲሞቱ ከእነዚህም መካከል ሁለቱ በድብደባ እና አንድ ሰው "በማን እንደተተኮሰ ባልታወቀ ጥይት" ተመትቶ ሞቷል።

ከሟቾች መካከል አንዱን ጥቃት ፈጻሚዎቹ ከቤቱ አስወጥተው መንገድ ላይ ሲደበድቡት እሱን ለማዳን የመጣውን የልጃቸውን ባል ጨምረው እንደገደሏቸው የተጎጂ ቤተሰቦች እና ምስክሮች ለኮሚሽኑ ገልጸዋል።

በከተማው በደረሰው ጥቃት በአጠቃላይ ከ70 በላይ ሰዎች የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። የግል፣ የንግድ እና የመንግስት ንብረት ላይ ጉዳት የደረሰ ሲሆን በአጠቃላይ ከ30 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት ንብረት መውደሙን የአካባቢው አስተዳደር አካላት ገልጸዋል። ቤታቸው በመቃጠሉ ተፈናቅለው ቀስተ ዳመና 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተጠልለው የሚገኙ ተጎጂዎች ነበሩ። ተጎጂዎቹ በመጀመሪያ ወደ ቤተክርስቲያን ከሄዱ በኋላ የመንግስት አካላት ወደ ትምህርት ቤት እንዳመጧቸው ለኢሰመኮ አስረድተዋል።

> "መንግስት ያለ አይመስልም ነበር።"
>
> *አንድ ተጎጂ ስለተከሰተው ነገር የተናገሩት*

የመንግስት አካላት ጥቃቱን ቀድሞ ለመከላከልም ሆነ ደርሰው ለመቆጣጠር እና ጥበቃ ለማድረግ ያደረጉት ጥረት አነስተኛ እንደነበረ እና በአንዳንድ ቦታዎች ፖሊሶች ጥቃቱ ሲፈፀም ዝም ብለው ያዩ እንደነበረ ተጎጅዎች ለኮሚሽኑ ገልጸዋል። የፀጥታ ኃይሉ ጥፋቱ ከተፈፀመ በኋላ በግምት ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ላይ በጣም ዘግይቶ እንደመጣ ተናግረዋል። አንድ ተጎጂ ሁኔታውን "መንግስት ያለ አይመስልም ነበር" በማለት ገልጾታል።

የአካባቢው አስተዳደር አካላት ጥቃቱ ድንገት መድረሱን፤ ሆኖም ግን በግምት ከረፋዱ 5፡00 ሰዓት አካባቢ የፀጥታ ኃይል እንዳሰማሩና መጀመሪያ ባንክ እና የመንግስት ተቋማት ላይ ትኩረት አድርጎ ጥበቃ የተደረገ መሆኑን፤ በኋላ ጥቃቱ ወደ ግለሰብ ንብረት ሲዞር ኃይሉን በማከፋፈል የግለሰቦችን ንብረት ለማዳን ጥረት ቢደረግም ጥቃቱ ሰፊ ቦታ ስለሸፈነ ጉዳት እንደደረሰ አስረድተዋል።

ተጎጂዎች እና ምስክሮች ጥቃቱ ኃይማኖትን እና ብሔርን መሰረት ያደረገ እንደነበር ገልጸዋል። ለዚህም ማሳያ የሚሆነው ጥቃት ፈጻሚዎቹ “አማራ ውጣ”፣ “ነፍጠኛ ውጣ”፣ “ክርስቲያን ውጣ”፣ “መንዜ ውጣ” እያሉ ቤት ንብረታቸውን ማቃጠላቸውን ተጎጂዎች እና ምስክሮች ገልጸዋል። ለምሳሌ አንድ ኮሚሽኑ ያነጋገረው ተጎጂ ጥቃት ፈጻሚዎቹ የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ መሆኑን ቢያውቁም ድብደባ እና ማቃጠል እንደፈፀሙበትና ይህም ኃይማኖቱን መሠረት አድርገው የፈፀሙት መሆኑን እንደሚያምን አስረድቷል። በሌላ በኩል ሙስሊም የሆኑ ጎረቤቶች ደብቀው ህይወታቸውን እንዳተረፉላቸው እና ደርሰው ከጥቃት እንዳዳኗቸው የገለጹ ተጎጂዎችም አሉ። የአካባቢው አስተዳደር አካላት ጥቃቱ መጀመሪያ የፖለቲካ አስተሳሰብን መሰረት አድርጎ የመንግስት ተቋማትን በማጥቃት መጀመሩን እና በኋላ ኃይማኖት እና ብሔርን መሰረት ወደ አደረገ ጥቃት መቀየሩን አስረድተዋል።

ከለይ ከተጠቀሰው ሁኔታ በተለየ መልኩ አንድ ተጎጂ ደግሞ ኦሮሞ ቢሆንም የግል ጸብ የነበረው ሰው በቂም በቀል አራት ወጣቶችን አስተባብሮ የቤተሰባቸውን አባል እንደገደለባቸው ለኢሰመኮ አስረድተዋል። ጥቃቱን የፈፀመው ሰው አስቀድሞም በጠላትነት ይመለከታቸው እና “አገሩን ለቃችሁ ውጡ” በማለት ይዝት እንደነበረና ይህንንም ለፖሊስ አመልክተው እንደነበር ገልጸዋል።

የከተማው አስተዳደር አካላት ለኮሚሽኑ እንደገለፁት መረጃው በሚሰበሰብበት ወቅት ጥቃት በመፈጸም የተጠረጠሩ 164 ሰዎች በቁጥጥር ስር ውለዋል። በተጎጂዎች በኩል ግን ያልተያዙ ሰዎች እንዳሉ፤ አሁንም ጥቃት ይደርስብናል የሚል ስጋት እንዳላቸው እና በቂ ጥበቃ ሊደረግ እንደሚገባ ገልጸዋል። በተጨማሪም ተጎጂዎችን ለመርዳት የተቋቋመ ኮሚቴ አባላቱ በማይታወቅ ምክንያት መታሰራቸው እንዳሳሰባቸውም ተጎጅዎች ለኮሚሽኑ ገልጸዋል።

ተጎጂዎች የመንግስት ድጋፍ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን እና ሕዝበ ክርስቲያኑ ሰብአዊ ድጋፍ እያደረገላቸው መሆኑን ገልጸዋል። የአካባቢው መስተዳድር የምግብ እና የቁሳቁስ እርዳታ (በቆሎ፣ ብርድልብስ፣ ፍራሽ፣ አንሶላ፣ ምንጣፍ እና የከብት ሳር) ማድረጉን እና ሙሉ በሙሉ የወደሙ ቤቶችን በብሎኬት እያሰራ መሆኑን ኮሚሽኑ ተረድቷል።

## 2.11. ባሌ ዞን አጋርፋ ወረዳ

በአጋርፋ ወረዳ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. በተለይም በአምቤንቱ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ሰዎች “ከተለያዩ ቀበሌዎች በመኪና ጭምር ተጭነው ድምጽ እያሰሙ በመምጣት” በግምት ከጠዋቱ 2፡30 ሰዓት ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ በየሰፈሩ በመዞር ጥቃት አድርሰዋል።

ኮሚሽኑ ያነጋገራቸው ተጎጂዎች እና ምስክሮች እንደገለጹት እንዲሁም ተጎጅዎች በተወካዮቻቸው አማካኝነት ለኮሚሽኑ በዝርዝር ባቀረቡት አቤቱታ እንዳመለከቱት በጥቃቱ 3 ሰዎች በመታረድ እና 2 ሰዎች በመደብደብ ህይወታቸው ማለፉን ገልጸዋል። በተጨማሪም የተጎጂዎቹ ተወካዮች ለኢሰመኮ ባቀረቡት አቤቱታ 64 መኖርያ ቤቶች ከነሙሉ እቃቸው መውደማቸውን እንዲሁም 144 ቤቶች ላይ ዝርፊያ መፈጸሙን አሳውቀውዋል። በከተማዋ በመንግስት ተቋማት ላይም ሰፊ የንብረት ጉዳት ደርሷል። ሆኖም ግን የአከባቢው የአስተዳደር አካላት ለኮሚሽኑ

*መርማሪዎች አስተያይት ለመስጠት ፍቃደኛ ባለመሆናቸው በመንግስት ተቋማት ላይ የደረሰውን ጉዳት ዝርዝር በዚህ ሪፖርት ማካተት አልተቻለም።*

*የኮሚሽኑ የምርመራ ቡድን በስፍራው በነበረበት ጊዜ በጥቃቱ ምክንያት ከቤታቸው የተፈናቀሉ ሕጻናት እና አቅመ ደካሞችን ጨምሮ ከ1,500 በላይ ሰዎች አጋርፋ ግብርና ኮሌጅ ውስጥ ተጠልለው ነበር። ተጎጂዎቹ ከ1998 ጀምሮ በክርስቲያኖች ላይ ጫና ይደረግ እንደነበርና በተለያየ ጊዜ ጉዳት ሲደርስባቸው መቆየቱን፤ ይህንንም ለመንግስት አካላት ቢያሳውቁም ችግሩን ለመቅረፍ ምንም አለመደረጉን ገልጸዋል። ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. የጀመረው ጥቃት እስከ ሰኔ 24 ቀን 2012 ዓ.ም. የቀጠለ ቢሆንም ጥቃቱን ያስቆመ የመንግስት አካል አለመኖሩን፤ የፀጥታ አካላትም ጥቃቱ እየደረሰ ስለመሆኑ ቢሰሙም አለመድረሳቸውን ተጎጂዎቹ በምሬት አስረድተዋል። ተጎጂዎች ከፍተኛ ስጋት ላይ መሆናቸውንና በመንግስት አካላት ጥበቃ በሌለበት ሁኔታ ወደ ቤታችሁ ተመለሱ እየተባሉ መሆኑ እንዳሳሰባቸው በወቅቱ ለኮሚሽኑ ገልጸዋል።*

> *“[ተጎጂዎች] ከፍተኛ ስጋት ላይ በመሆናችንና በመንግስት አካላት ጥበቃ በሌለበት ሁኔታ ወደ ቤታችሁ ተመለሱ መባላችን አሳስቦናል።”*
>
> *በጥቃቱ የተፈናቀሉ ሰዎች ለኢሰመኮ የተናገሩት*

*ጥቃቱ ኃይማኖትና ብሔርን መሰረት ያደረገ እንደነበር እና ጥቃት የደረሰባቸውም በዋነኛነት የአማራ ብሔር ተወላጅና እና ክርስቲያኖች መሆናቸውን ተጎጅዎች ተናግረዋል። ጥቃት ፍፃሚዎቹም ጥቃቱን በሚፈጽሙበት ጊዜ “ጎንደሬ ውጣ፤ እዚሁ ነው የልጃችንን ደም የምንበቀለው” ይሉ እንደነበር ተጎጂዎቹ ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።*

*ጥቃቱን በማድረስ ተጠርጥረው እንዳንድ ሰዎች መታሰራቸውን መስማታቸውን፤ ነገር ግን ዋና አደራጆች ተይዘዋል ብለው እንደማያምኑ የኮሚሽኑ መርማሪዎች ያነጋገሯቸው ተጎጂዎች ገልጸዋል። የአካባቢው የአስተዳደር አካላት በዚህ ጉዳይ ላይ ኢሰመኮን ለማነጋገር ፍቃደኛ አልሆኑም።*



ለተፈናቀሉ ወገኖች የአጋርፋ ግብርና ኮሌጅ የእለት ምግብ፣ ፍራሽ እና ማደሪያ ቦታ ማቅረቡን ኢሰመኮ ተመልክቷል። ተጎጂዎች በበኩላቸው በመንግስት የተደረገላቸው ድጋፍ ዝቅተኛ መሆኑን እና የሚዘሩት ዘር እና የአፈር ማዳበሪያ የሌላቸው በመሆኑ መሬታቸው ዘር ሳይዘራ ሊቀር መሆኑን እና ረሃብ እንደሚያሰጋቸው ለኮሚሽኑ ገልጸዋል። የአስተዳደር አካላት የወደሙ ቤቶችን ለመስራት ቃል የገቡ ቢሆንም ኢሰመኮ መረጃ በሰበሰበበት ጊዜ የተጀመረ ነገር አልነበረም።

የኮሚሽኑ መርማሪዎች የአጋርፋ ወረዳ የመንግስት የአስተዳደር አካላትን ለማናገር ያደረጉት ሙከራ ኃላፊዎቹ ፍቃደኛ ባለመሆናቸው አልተሳካም። ዕንዲያውም የወረዳው አስተዳዳሪዎች የኮሚሽኑን የምርመራ ቡድን አባላት ለሁለት ሰዓታት ያህል በቁጥጥር ስር በማዋል አንገላተዋቸዋል፤ የእጅ ስልኮቻቸውን በመቀበል ጭምር መረጃ ለማጥፋት ሙከራ አድርገዋል።

## 2.12. ኮፈሌ ከተማ

በኮፈሌ ከተማ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. ቄጥራቸው በርከት ያለ ወጣቶች ከሌሊቱ 9፡00 ሰዓት ጀምረው በመሰባሰብ መፈክር ሲያሰሙ እንደነበረና ከቀኑ 6፡00 ሰዓት ጀምሮ ሰዎችን የማጥቃት እና ንብረት የማቃጠል ድርጊት ይፈፅሙ እንደነበር ተጎጂዎች፣ በስፍራው የነበሩ ምስክሮች እና የአካባቢው አስተዳደር አካላት አስረድተዋል።

በወረዳው የሞት አደጋ ባይደርስም 1 የአገር ሽማግሌ ላይ የአካል ጉዳት መድረሱን፣ 47 ሱቆችና 22 መኖርያ ቤቶች በድንጋይ መሰባበራቸውን፣ 5 የመኖሪያና የንግድ ቤቶች መቃጠላቸውን ለማወቅ ተችሏል። በስፍራው የተፈናቀሉ ሰዎች ባይኖሩም ቤታቸው የተቃጠለባቸው (የተሰባበረባቸው) ሰዎች ሸሽተው ወደ ሃዋሳና ሻሸመኔ ሄደዋል።

> "ጥቃቱ የቆመው የሃይማኖት አባቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች እና አባገዳዎች ባደረጉት ጥረት ነው። የአካባቢው ህብረተሰብ ንብረት እንዳይቃጠል በመከላከል፣ ለተጎጂዎች ከለላ በመስጠት እና ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን በቤቱ በማስቀመጥ ጭምር ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። የከተማው የቄሮ እና የፎሌ አባላት ከብቶችን ዘርፈው ሲሄዱ ከነበሩ ጥቃት ፈፃሚዎች አስመልሰውልናል።"
>
> *ጥቃት የደረሰባቸው ሰዎች ለኢሰመኮ የተናገሩት*

የአካባቢው አስተዳደር አካላት እንደገለጹት ጥቃቱን የፈፀሙ ሰዎች ብዛት እንደነበራቸው፤ ጥቃቱን ለመከላከል ቢሞክሩም በአካባቢው ከሚገኙ ሌሎች የገጠር ቀበሌዎች ጭምር ሰዎች በመምጣታቸው እስከ ቀኑ 9፡00 ሰዓት ድረስ ከአቅም በላይ እንደሆነባቸው አስረድተዋል። ተጎጂዎች እና ምስክሮችም ጥቃቱ የቆመው የሃይማኖት አባቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች እና አባገዳዎች ባደረጉት ጥረት እንደሆነ ገልጸዋል። አክለውም የአካባቢው ህብረተሰብ ንብረት እንዳይቃጠል በመከላከል፣ ለተጎጂዎች ከለላ በመስጠት እና ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን በቤቱ በማስቀመጥ ጭምር ከፍተኛ ሚና እንደተጫወተ አስረድተዋል። በተጨማሪም የከተማው የቄሮ እና የፎሌ አባላት ከብቶችን ዘርፈው ሲሄዱ ከነበሩ ጥቃት ፈፃሚዎች ማስመለሳቸውን ገልጸዋል።

ጥቃት ፈጻሚዎቹ "ነፍጠኛ ይውጣ" የሚል መፈክር ያሰሙ እንጂ ጥቃቱ የኦሮሞ ብሔር ተወላጆችም ላይ መድረሱን እና በዋነኝነት የዝርፊያ እና የስርቆት ባህሪ እንደነበረው ተጎጂዎች እና የአስተዳደር አካላት ለኢሰመኮ የምርመራ ቡድን አብራርተዋል። ኢሰመኮ መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት ፀጥታውን በማስጠበቅ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ አልተወጡም የተተባሉ የመንግስት ሰራተኞች እና የፖሊስ አባላትን ጨምሮ ከጥቃቱ ጋር በተያያዘ የተጠረጠሩ 70 ሰዎችን በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የከተማው አስተዳደር አካላት ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

የከተማው አስተዳደር ጉዳት የደረሰባቸው ቤቶችን ተጎጂዎች በራሳቸው ወጪ አድሰው ያወጡት ወጪ በከተማው አስተዳደር ይሸፈንላቸዋል የሚል ውሳኔ በመወሰኑ ንብረቶቻቸውን የመጠገን ስራ በራሳቸው የጀመሩ ተጎጂዎች ነበሩ። ህብረተሰቡም ጉዳት የደረሰባቸው ንብረቶችን በመጠገን ላይ እየተሳተፈ መሆኑን እና ይህ መረጃ እስከተሰበሰበበት ቀን ድረስ በተደረገ እንቅስቃሴ በተለይም በከፊል የተጎዱ ሱቆች በአዲስ ቆርቆሮ ተጠግነው ስራ መጀመራቸውን የኮሚሽኑ መርማሪዎች ተመልክተዋል።

> *"ጥቃት ፈጻሚዎቹ 'ነፍጠኛ ይውጣ' የሚል መፈክር ያሰሙ እንጂ ጥቃቱ የኦሮሞ ብሔር ተወላጆችም ላይም የደረሰ ሲሆን በዋነኝነት የዝርፊያ እና የስርቆት ባህሪ ነበረው።"*
>
> *ተጎጅዎች እና የአካባቢ አስተዳደር አካላት የተናገሩት*

## *2.13. ጉና ወረዳ ነገሌ ከተማ*

በአርሲ ዞን ጉና ወረዳ ስር በምትገኘው ነጌሌ ከተማ የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. ከጠዋት ጀምሮ ሐዘናቸውን ለመግለጽ ነዋሪዎች ወደ ጎዳና/አደባባይ ወጥተዋል። ሁኔታው በሂደት ወደ አመፅ ተቀይሮ እስከ ቀኑ 8፡30 ሰዓት ድረስ መንገድ የመዝጋት፣ የአነግ ባንዲራ ቀለማትን በመንግስት ንብረቶች ላይ የመቀባትና ጥቃት የመፈፀም አዝማሚያዎች ታይተዋል። ሆኖም ግን ጉዳት ሳይደርስ ሽማግሌዎች እና የመንግስት አካላት ሁኔታውን አረጋግተውት ለተቃውሞ የተሰማራው ሰው ተበትኗል።

ይሁንና ሰልፉ ከተበተነ በኋላ በግምት ወደ 8፡30 ሰዓት አከባቢ በኦሮሚያ ፖሊስ ልዩ ኃይል በተወሰደ እርምጃ የ5 ሰዎች ሕይወት ማለፉን፣ በትንሹ በ8 ሰዎች ላይ አካላዊ ጉዳት መድረሱን (ሰባቱ በጥይት፣ አንዱ በድብደባ) ከተጎጂ ቤተሰቦች፣ ከጤና ጣቢያ እና ከአካባቢው የአስተዳደር አካላት በተገኘ ማስረጃ ማረጋገጥ ተችሏል። ጉዳቱም ሊደርስ የቻለው በአገር ሽማግሌዎች እና የመንግስት አካላት ጥረት ሰልፉ ተበትኖ ከገጠር አካባቢዎች የመጣው ሕዝብ ወደቤቱ በመመለስ ላይ ሳለ የተዘጋ መንገድ እያስከፈተ ወደ ከተማው በመምጣት ላይ ከነበረ የኦሮሚያ ፖሊስ ልዩ ኃይል ጋር መንገድ ላይ ተገናኝተው ፍጥጫ በመፈጠሩ ነው። ፍጥጫውን ተከትሎ ፖሊሶች ወደ ላይ መተኮስ የጀመሩ በመሆኑ ችግሩን ለመፍታት የአከባቢው ሽማግሌዎች መሃል ቢገቡም ልዩ ኃይሉ "እርምጃ እንወስዳለን ከመሃል ውጡ" በማለት በቀጥታ ወደ ሕዝቡ በመተኮሱ ወደ ቤቱ ይመለስ በነበረ ሰልፈኛና ተኩስ ሰምቶ ሁኔታውን ለማየት ከቤታቸው በወጡ ሰዎች ላይ የሞትና የአካል ጉዳት መድረሱን በቦታው የነበሩ ምስክሮችና ተጎጂዎች አስረድተዋል።

> *"ፍጥጫውን ተከትሎ ፖሊሶች ወደ ላይ መተኮስ በመጀመራቸው ችግሩን ለመፍታት የአከባቢው ሽማግሌዎች መሃል ቢገቡም ልዩ ኃይሉ 'እርምጃ እንወስዳለን፥ ከመሃል ውጡ' በማለት በቀጥታ ወደ ሕዝቡ በመተኮሱ ወደ ቤቱ ይመለስ በነበረ ሰልፈኛና ተኩስ ሰምቶ ሁኔታውን ለማየት ከቤታቸው በወጡ ሰዎች ላይ የሞትና የአካል ጉዳት ደርሷል። በፖሊሶች በተወሰደ እርምጃ ከሞቱት ሰዎች መካከል ጉዳት እንዳይደርስ የልዩ ኃይል አባላትን ለማግባባት ሲሞክሩ የነበሩ የአገር ሽማግሌዎች እና ከነዚህም መሃከል አንደኛው ፖሊሶች ተኩስ ሲከፍቱ በመሸሽ ላይ እያሉ ማጅራታቸው ላይ ተመትተው ተገለዋል።"*
>
> *ተጎጅዎች እና ምስክሮች የተናገሩት*

በፖሊሶች በተወሰደ እርምጃ ከሞቱት ሰዎች መካከል ከፍተኛ ጉዳት እንዳይደርስ የልዩ ኃይል አባላትን ለማግባባት ሲሞክሩ የነበሩ የአገር ሽማግሌዎች እንደሚገኙበት እና ከነዚህም መሃከል አንዳቸው ፖሊሶች ተኩስ ሲከፍቱ በመሸሽ

ላይ እያሉ ማጅራታቸው ላይ ተመትተው የተገደሉ መሆኑን ቤተሰቦቻቸው ገልጸዋል። በተመሳሳይ ሌላ የአገር ሽማግሌ ሁኔታውን ለማረጋጋት ሲጥሩ በተከፈተው ተኩስ እንደተመቱ በስፍራው የነበሩ ምስክሮች አረጋግጠዋል። ሌሎች ምስክሮችም ፖሊስ አውቶማቲክ እሩምታ ተኩስ መክፈቱን እና ሁኔታውን ለማየት ከቤት የወጣ እና በሰልፉ ላይ ያልነበረ ሌላ ግለሰብ በጥይት ተመትቶ መሞቱን ለኮሚሽኑ ገልጸዋል። ለዚህ ሪፖርት መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት በጥይት ተመትተው በህክምና ላይ ከነበሩ ተጎጂዎች መካከል የ15 ዓመት ሴት ልጅ እና ከሁለት ጊዜ በላይ በጥይት የተመቱ ሰዎች እንደሚገኙበት የኮሚሽኑ መርማሪዎች ተመልክተዋል።

የኦሮሚያ ልዩ ፖሊስ የኃይል እርምጃውን ሲወስድ ሰልፈኞቹ የጦር መሳሪያ ያልያዙና ሰላማዊ እንደነበሩ፤ በንብረትም ሆነ በሰው ላይ ጉዳት አለማድረሳቸውን ተጎጂዎች እና ምስክሮች ለኢሰመኮ አስረድተዋል። የአካባቢው የአስተዳደር አካላትም ይህንኑ በማረጋገጥ በከተማው በሰልፈኞቹ ጉዳት አለመድረሱን እና በልዩ ኃይሉ የተወሰደው እርምጃ ተመጣጣኝ ያልነበረ መሆኑን መስክረዋል።




ተጎጂዎች እና ምስክሮች ግድያውን የፈፀሙ አባላትን በመለየት ተጠያቂነትን ለማስፈን የተደረገ ጥረት አለመኖሩን ገልፀው በተቃራኒው ታስረው የሚገኙ የሟቾች ቤተሰቦች እንዳሉ እና በፖሊሶች "ሀገሪቱ በወታደር ነው የምትተዳደረው፥ ፀጥ ብላችሁ ተቀመጡ" መባላቸውን፤ ኢሰመኮ ለዚህ ሪፖረት ምርመራ ባደረገበት ጊዜም ጭምር በከተማው የሚገኙ የልዩ ኃይል አባላት ወጣቶችን ይደበድቡ እንደነበር ለኮሚሽኑ አስረድተዋል። የአካባቢው የአስተዳደር አካላትም ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ምርመራ አለመደረጉን አምነው ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችም ፍርሃት ስላለባቸው ቅሬታ አለማቅረባቸውን ጠቅሰዋል።

የሟች ቤተሰቦች እና የቆሰሉ ሰዎች ምንም አይነት ድጋፍ አለማግኘታቸውን፤ በተለይም አካላዊ ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች የህክምና ድጋፍ እንኳን አለመደረጉን ገልጸዋል። እንዲያውም የልዩ ኃይል አባላት የተገደሉ ሰዎች የቀብር

ሥነ-ሥርዓት ላይ በመገኘት ሃዘንተኛውን ማንገላታታቸውን እና የከተማው ጤና ጣቢያ ድረስ በመሄድ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎችን ወደ ጤና ጣቢያ ያደረሱ ሰዎችን እና የጤና ባለሙያዎችን “ለምን እርዳታ ትሰጣላችሁ” ብለው መደብደባቸውን ድብደባ የተፈፀመባቸው የህክምና ባለሙያዎች እና ምስክሮች ለኢሰመኮ ገልጸዋል።

## 2.14. ዶዶላ ከተማ

የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ በዶዶላ ከተማ ሰኔ 23 እና 24 ቀን 2012 ዓ.ም. የተካሄዱ የተቃውሞ ሰልፎች ጋር ተያይዞ በተፈጠረ ሁከት በሰዎች ህይወት እና ንብረት ላይ ጉዳት ደርሷል። በከተማው ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. በግምት ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12፡00 ሰዓት በተፈጸመ ጥቃት የ9 ግለሰቦች መኖርያ ቤቶች፣ ሱቆች፣ ንግድ ቤቶች፣ ተሸከርካሪዎች፣ የቤት ቁሳቁሶች፣ ገንዘብ ወ.ዘ.ተ. በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ወድመዋል ወይም ተዘርፈዋል።

ይህንንም ተከትሎ የፀጥታ ኃይሉ በወሰደው እርምጃ እድሜያቸው ከ10-25 ዓመት የሆኑ 7 ሰዎች በጥይት ተመትተው የተገደሉ ሲሆን በ35 ሰዎች ላይ አካላዊ ጉዳት ደርሶባቸዋል። ጉዳት ከደረሰባቸው ሰዎች መካከል በደረሰው ጥቃት ውስጥ ተሳትፎ ያልነበራቸው ትንሽ ልጆች ይገኙበታል። ከዚህም በተጨማሪ ፖሊሶች በከተማው በሚገኘው መደወላቡ ሆስፒታል ውስጥ በመግባት በህክምና ላይ የነበሩ ተጎጂዎችን እና የህክምና ባለሙያዎችን መደብደባቸውን በቦታው የነበሩ ምስክሮች እና ተጎጂዎች ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

አብዛኞቹ ንብረታቸው የወደመባቸው ሰዎች የከተማው አስተዳደርም ሆነ የፀጥታ ኃይሉ ጉዳቱን ለመከላከል ያደረጉት ጥረት አለመኖሩን ገልጸዋል። አብዛኞቹ ተጎጂዎች ጥቃቱ ብሔራቸውን ወይም ኃይማኖታቸውን መሰረት በማድረግ እንደተፈፀመባቸው ያምናሉ።

ኢሰመኮ ለዚህ ሪፖረት መረጃ በሚሰበስብበት ወቅት በጥቃቱ ተሳታፊ ነበሩ ተብለው የተጠረጠሩ ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ ግለሰቦች በቁጥጥር ስር የዋሉ ሲሆን በፀጥታ ኃይሉ የተፈጸሙ ግድያ እና አካል ጉዳት በማጣራት ተጠያቂነትን ለማስፈን የተወሰደ እርምጃ አልነበረም። በሌላ በኩል በተፈጸመው ጥቃት ምክንያት ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው በቤተክርስትያን ውስጥ የተጠለሉ ሰዎች በመንግስት ድጋፍ አልተደረገላቸውም ነበር።

ኢሰመኮ የመረጃ ሚዛናዊነትን ለመጠበቅ እና በግለሰቦችና በመንግስት የፀጥታ ኃይሎች ጉዳት ከደረሰባቸው ሰዎች በተነሱት ቅሬታዎች ላይ የከተማው አስተዳደር እና የፀጥታ ቢሮ ኃላፊ አስተያየት እንዲሰጡ ቢጠየቁም ምርመራው በሚደረግበት ወቅት የኦሮሚያ ክልል መንግስት እና የኦሮሚያ ፖሊስ ኮሚሽን በቀጥታ በደብዳቤ ካላሳወቁን በስተቀር አስተያየት መስጠት አንችልም በማለታቸው አስተያየታቸውን ማካተት አልተቻለም።

## 2.15. ቡራዩ ከተማ

በቡራዩ ከተማ ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. ከለሊቱ 9፡00 ሰዓት ጀምሮ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ ወደ መንገድ/አደባባይ በመውጣት የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ አስክሬን ወዳለበት ቦታ ለመሄድ ሲንቀሳቀስ ነበር። በማግስቱ ጠዋት ላይ አስክሬኑን ወደ አምቦ ለመሸኘት ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ በቦታው ተገኝቶ የነበረ ሲሆን ቡራዩ ኬላ በሚባለው አካባቢ “አስክሬኑ ወደ አዲስ አበባ ይመለስ ወይስ አይመለስ” በሚል በሕዝቡና በፀጥታ ኃይሎች መካከል በተፈጠረ አለመግባባት በሰው ሕይወት እና አካል ላይ ጉዳት ደርሷል። በተጨማሪም ሰኔ 24 ቀን 2012 ዓ.ም.

ሰልፍ በወጡ ሰዎች እና በፀጥታ ኃይሎች መካከል በተፈጠረ ግጭት የሰው ህይወት መጥፋቱን የከተማው አስተዳደር አካላት ገልጸዋል።

በአጠቃላይ ሰኔ 22 እና 23 በቡራዩ ከተማ በፀጥታ ኃይሎች በተወሰደ እርምጃ 2 ሰዎች በጥይት ተገድለዋል። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የ33 ዓመት ወጣት ሲሆን ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. የሃጫሉን አስክሬን በመሸኘት ላይ እያለ ቡራዩ ከተማ ልዩ ስሙ ሳንሱሲ በሚባል ቦታ ላይ ከፖሊስ በተተኮሰ ጥይት ጭንቅላቱ ላይ ተመቶ ባጋጠመው ከፍተኛ የደም መፍሰስ ምክንያት ከቀኑ 6፡30 ሰዓት ላይ ህይወቱ አላፏል። በተመሳሳይ ሌላ ወጣት ሰኔ 24 ቀን 2012 ዓ.ም. ከፀጥታ ኃይሎች በተተኮሰ ጥይት ደረቱ ላይ ተመትቶ መሞቱን ከአይን እማኞች፣ ከቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ እና ከቡራዩ ከተማ ጤና ጣቢያ ከተገኙ መረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል። ከተገደሉ ሰዎች በተጨማሪ በሁለቱ ቀናት በቡራዩ ከተማ በተለያዩ ቦታዎች በፀጥታ ኃይሎች በተተኮሱ ጥይቶች 15 ሰዎች ቀላል እና ከባድ አካላዊ ጉዳት ደርሶባቸዋል።




አንድ የዘይት ፋብሪካ፣ በፋብሪካዉ ግቢ የነበሩ አንድ ቦቴ መኪና እና አንድ የሕዝብ ማመላለሻ ቅጥቅጥ መኪና በግለሰቦች ተቃጥለዋል። በተጨማሪም በፋብሪካው ግቢ ውስጥ የነበሩ ተሽከርካሪዎች መስታወታቸው ተሰባብሯል፤ እንዲሁም የፋብሪካው የጥበቃ ሰራተኛ በወጣቶቹ አካላዊ ጉዳት ደርሶባቸዋል። የአቢሲንያ ባንክ ሳንሱሲ ቅርንጫፍ እና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከታ ቅርንጫፎችም መጠነኛ ጉዳት ደርሶባቸዋል።

የንብረት ጉዳት ሲደርስ እና ፋብሪካው ሲቃጠል የፀጥታ ኃይሉ በቂ ጥበቃ አላደረገም በሚል ተጎጂዎች ቅሬታ አቅርበዋል። በሌላ በኩል ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. ጠዋት ከአስክሬን ሽኝት ጋር በተያያዘ በሰልፈኞች በኩል ምንም ዓይነት ጥቃት ሳይሰነዘር ፖሊሶች ጥይት መተኮስ በመጀመራቸው ጉዳት እንዲደርስ እና ረብሻ እንዲፈጠር ምክንያት መሆናቸውን በቦታው የነበሩ ምስክሮች ለኮሚሽኑ አስረድተዋል። የተወሰኑ ከአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ በተተኮሰ

ጥይት የተመቱ መሆኑን የተናገሩ ተጎጂዎች ምንም ችግር ሳይፈጠር "ኦሮሞ ስለሆንን" ነው በቀጥታ ጥይት የተተኮሰብን የሚል ቅሬታ ለኮሚሽኑ አቅርበዋል። የንብረት ጉዳት አድርሰዋል ተብለው የተጠረጠሩ በርካታ ሰዎች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የመንግስት አካላት የገለጹ ሲሆን፤ የፀጥታ አካላት ያደረሱትን ሞት እና የአካል ጉዳት ለማጣራት የተጀመረ ምርመራም ሆነ የተወሰደ እርምጃ መኖሩን አልገለፁም። ለዚህ ሪፖርት መረጃ እስከተሰበሰበበት ጊዜ ድረስ ለተጎጂዎች በመንግስት ምንም አይነት ድጋፍ አልተደረገም።

## 2.16. አርሲ ነጌሌ ከተማ

የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ ከሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. ምሽት ጀምሮ በነጌሌ ከተማ ጩኸት ነበር። በማግስቱ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. ከጠዋት ጀምሮ በተደረገው የተቃውሞ ሰልፍና ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተፈጠረ ሁከት የሰዎች ሞት፣ የአካል እና የንብረት ጉዳት ደርሷል።

በከተማው በግለሰቦች በተፈጸመ ጥቃት 5 ሰዎች ተገድለዋል። በፀጥታ ኃይሎች እና በሁከት ፈጣሪዎች በተፈጸመ ጥቃት 44 ሰዎች የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። የአካል ጉዳት ከደረሰባቸው ሰዎች ውስጥ 19 ሰዎች በጥይት የተመቱ ሲሆን 25 ሰዎች ደግሞ በዱላ፣ በድንጋይ፣ በእሳት እና በኤሌክትሪክ ጉዳት ደርሶባቸዋል። ከነዚህ ውስጥ 27 ሰዎች ቀላል ጉዳት የደረሰባቸው ናቸው። በተጨማሪም በ16 የግል ንብረቶች ላይ ዘረፋ እና የቃጠሎ አደጋ ደርሷል።

በከተማው የኦሮሚያ ልዩ ኃይል እና የከተማው ፖሊስ የነበሩ ቢሆንም የከተማ አስተዳደሩ እና የከተማው ፓሊስ ጥበቃ እንዲያደርግ በተደጋጋሚ ሲጠየቅ ኃይል የለንም፤ ትእዛዝ አልተሰጠንም ወይም የግለሰብ ንብረት ጠብቁ አልተባልንም የሚል መልስ ይሰጡ እንደነበር ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች አስረድተዋል። አንዳንድ ቦታ ላይ ደግሞ ፖሊስ ጥቃቱን እያዩ በዝምታ ማለፉን ጥቃቱ የደረሰባቸው ነዋሪዎች ገልጸዋል። በጥቃቱ የተሳተፉ አንዳንድ ግለሰቦች ጥቃት በተፈጸመበት ወቅት "ፖሊሶቹ ከኃይማኖት ተቋማትና ከመንግስት መስሪያቤት ውጪ ያሉትን አቃጥሉ" ይሉን ነበር ብለው ሲናገሩ መስማታቸውን አንድ ምስክር ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

> " በከተማው የኦሮሚያ ልዩ ኃይል እና የከተማው ፖሊስ የነበሩ ቢሆንም የከተማ አስተዳደሩ እና የከተማው ፓሊስ ጥበቃ እንዲያደርግ በተደጋጋሚ ሲጠየቅ ኃይል የለንም፤ ትእዛዝ አልተሰጠንም ወይም የግለሰብ ንብረት ጠብቁ አልተባልንም የሚል መልስ ይሰጡ ነበር። አንዳንድ ቦታ ላይ ደግሞ ፖሊስ ጥቃቱን እያዩ በዝምታ ተመልክቷል። "
>
> *ተጎጅዎች እና ምስክሮች የተናገሩት*

በሌላ በኩል የኢሰመኮ መርማሪ ቡድን ያነጋገራቸው አንዳንድ የጤና ባለሙያዎች በእለቱ አምቡላንሶች አገልግሎት እንዳይሰጡ መደረጋቸውንና የደም እጥረት አጋጥሞ ከሻሸመኔ ለማምጣት አጃቢ ቢጠይቁም በፀጥታ አካላት መከልከላቸውን ገልጸዋል።

የጥቃቱ ሰለባዎች ጥቃቱ የተፈጸመባቸው በብሔራቸው፣ በኃማኖታቸው ወይም በፖለቲካ አመለካከታቸው ምክንያት ነው ብለው እንደሚያምኑ ለኮሚሽኑ ተናግረዋል።

በጥቃቱ በመሳተፍ ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር የዋሉ ሰዎች መኖራቸውን ኮሚሽኑ የተረዳ ቢሆንም ጥቃቱ በአመፅ መልክ የተፈፀመ እና ብዙ ሰዎች የተሳተፉበት በመሆኑ አጥፊውን ለይቶ ለማስቀጣት ስለሚያስቸግር ፍትህ ሳያገኙ እንዳይቀሩ ስጋት እንዳላቸው ተጎጂዎች ገልጸዋል።

ንብረታቸው የወደመባቸውና በፖሊስም ይሁን በግለሰቦች የሞትና የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ኢሰመኮ ለዚህ ሪፖረት መረጃ ባሰባሰበበት ወቅት በመንግስት የተደረገላቸው ድጋፍ እንደሌለ ተጎጂዎች ገልጸዋል። የከተማው አስተረዳደር በከተማው የደረሰውን የንብረት ውድመት ግምት ሰርቷል።

የመረጃ ሚዛናዊነትን ለመጠበቅ እና ከተጎጂዎች በተነሱ ቅሬታዎች ላይ አስተያየት እንዲሰጡ በኮሚሽኑ የተጠየቁት የከተማው የአስተዳደር አካላት ከኦሮሚያ ክልላዊ መንግሰት ትእዛዝ ሳይሰጠን መረጃ መስጠት አንችልም በማለታቸው ሃሳባቸውን ማካተት አልተቻለም።

## 2.17. ባቱ ከተማ

የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ በባቱ በከተማ ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. ከለሊቱ 7፡00 ሰዓት ጀምሮ ሰዎች ተሰብስበው ሐዘናቸውን ሲገልጹ እንደነበርና በሂደት ሁኔታው ወደ መንገድ መዝጋት፣ ንብረት ማውደም እና ሰዎችን ማጥቃት መቀየሩን ኢሰመኮ ከተጎጂዎች፣ ከምስክሮች፣ ከአስተዳደር አካላት እና ከህክምና ተቋማት ከተገኙ መረጃዎች ተረድቷል።

በከተማው ከ27 በላይ የተለያዩ ንብረቶች (የንግድ ቤቶች፣ ተሽከርካሪዎች እና መኖሪያ ቤቶች) ሙሉ በሙሉ እና በከፊል የመቃጠል እና የመዘረፍ አደጋ ደርሶባቸዋል። በከተማው የሚገኘው ኃይሌ ሪዞርት ከፍተኛ ሊባል የሚችል ጉዳት የደረሰበት ሲሆን በሪዞርቱ ውስጥ የነበሩ የእንግዶች እና የድርጅቱ ተሽከርካሪዎችም ተቃጥለዋል።

የመንግስት አካላት እንደገለፁት ለጊዜው "ማንነቱ ባልታወቀ ግለሰብ" በተወረወረ ቦንብ አንዲት የ17 ዓመት ሴትልጅ ህይወቷ ያለፈ ሲሆን አንድ ወጣት ደግሞ አካላዊ ጉዳት ደርሶበታል። በተጨማሪም ከባቱ ሆስፒታል በተገኘ መረጃ መሰረት የባቱ ከተማ አጎራባች በሆነችው ቡልቡላ ከተማ ውስጥ 5 ሰዎች በፀጥታ ኃይል ባልደረቦች በተተኮሰ ጥይት ተመትተው ሞተዋል፤ እንዲሁም ሌሎች 7 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል።

የመንግስት አካላት ጥቃቱን ለመቆጣጠር ምንም አይነት ሚና እንዳልነበራቸው አብዛኛዎቹ ተጎጂዎች የገለጹ ሲሆን አንዳንዶች ደግሞ የከተማው ፖሊስ በነበረው አቅም ጉዳቱን ለመከላከል ጥረት ሲያደርግ እንደነበር አስረድተዋል። በተነሳው ቅሬታ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ የተጠየቁት የአካባቢው አስተዳደር አካላት በነበራቸው ውስን ኃይል አደጋውን ለመቆጣጠር ጥረት ሲያደርጉ እንደነበር ገልፀው በሁከቱ ከተሳተፈው የሰው ብዛት አንጻር ጉዳቱን ሙሉ በሙሉ ማስቆም ባይቻልም በነበራቸው የፖሊስ ኃይል የመንግስት መስሪያ ቤቶች እና ባንኮች ላይ ትኩረት በማድረግ ጥበቃ መደረጉን አስረድተዋል። በተጨማሪም ችግሩ መፈጠር እንደጀመረ ተጨማሪ ኃይል እንዲላክ የተጠየቀ ቢሆንም መንገዶች ተዘግተው ስለነበር ቶሎ መድረስ አለመቻላቸውን የአስተዳደር አካላቱ አክለው ጠቅሰዋል።

አብዛኞቹ ንብረታቸው የወደመባቸው ሰዎች ጥቃቱ ብሔርን መሰረት ያደረገ ነው ብለው እንደሚያምኑ የገለፁ ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ በፖለቲካ አመለካከታቸው ምክንያት መጠቃታቸውን አስረድተዋል። የከተማው የአስተዳደር አካላት ተወካዮች በበኩላቸው ጥቃቱ የደረሰባቸው ሰዎችን የብሔር ስብጥር በማጣቀስ ጥቃቱ አንድን ብሔር ኢላማ ያደረገ ነው ብሎ ለመደምደም እንደሚያስቸግር ገልጸዋል።

ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ቁጥራቸው በርከት ያለ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የከተማው አስተዳደር ገልጿል። ኢሰመኮ ለዚህ ሪፖረት መረጃ ሲሰበስብ የወደመውን ንብረት ከመመዝገብ ባለፈ ንብረታቸው ለወደመባቸው ግለሰቦች የተደረገላቸው ድጋፍ እንደሌለ የገለፁ ቢሆንም ኮሚሽኑ አስቸኳይ መፍትሄ የሚፈልጉ ጉዳዮች[2] በተመለከተ ያወጣውን መግለጫ ተከትሎ የክልሉ መንግስት ተጎጂዎችን አግኝቶ በማነጋገር በቀጣይ መልሶ ማቋቋም የሚቻልበት ሁኔታ ላይ መምከራቸውን ለመረዳት ተችሏል።

## 2.18. ሻሸመኔ ከተማ

የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ በሻሸመኔ ከተማ ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. ከሌሊቱ 7፡00 ሰዓት ጀምሮ በተለያዩ አከባቢዎች ጩኸት እና ለቅሶ የነበረ ሲሆን ቀስ በቀስ ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ሰዎች ከከተማ ውስጥ እና ከአጎራባች ቀበሌዎች በመውጣጣት መንገዶችን የመዝጋት እና የግለሰቦችን ንብረት የማጥቃት ተግባራት መፈጸማቸውን ተጎጂዎች እና ምስክሮች ለኢሰመኮ አስረድተዋል።



ሻሸመኔ

ከሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. ከለሊቱ 7፡00 ሰዓት እስከ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. 9፡00 ሰዓት ድረስ በቡድን በቡድን የተደራጁ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች በሻሸመኔ ከተማ በፈፀሙት መጠነ ሰፊ ጥቃት የአንድ ሰው ህይወት የጠፋ ሲሆን ከፍተኛ የንብረት ውድመትም ደርሷል። አንዲት የዘጠኝ ወር ነፍሰ ጡር ጥቃት ፈጻሚዎቹ ቤቷ ድረስ በመሄድ በፈፀሙት የንብረት ጉዳት፣ ዛቻ፣ እና ማስፈራሪያ ለከፍተኛ ጭንቀት በመጋለጧ ሆስፒታል ተኝታ ክትትል ሲደረግላት ቆይታ ሐምሌ 13 ቀን 2012 ዓ.ም. በኦፕራሲዮን እንድትገላገል ከሚከታተላት ሐኪም ጋር ቀጠሮ ቢያዝላትም በድንገት ሐምሌ 12 ቀን 2012 ዓ.ም. ምሽት ሃዋሳ በሚገኘው ታቦር የእናቶች እና ህፃናት ሆስፒታል ሕይወቷ አልፏል። ቀደም ሲል ክትትል ሲያደርግላት የነበረ ሐኪም ተጎጂዋ የስኳር ታማሚ የነበረችና የወሊድ ጊዜዋ የደረሰ

[2] ኢሰመኮ ጋዜጣዊ መግለጫ፥ “አፋጣኝ ምላሽ የሚሹ የሰብዓዊ መብት ጉዳዮች” ነሐሴ 8 ቀን 2012 ዓ.ም. https://www.facebook.com/permalink.php?story_fbid=928329717643929&id=202584253551816

ቢሆንም የስኳር ህመሟን መቆጣጠር ተችሎ ስለነበር ሞቷ ቅጽበታዊ በመሆኑ ከነበረባት ጭንቀት የመጣ የልብ ችግር (heart attack) ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አስቀምጧል።

በተጨማሪም ከሻሸመኔ አጠቃላይ ሆስፒታል እና ሻሸመኔ አጠቃላይ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በተገኘው መረጃ መሰረት በሻሸመኔ ከተማ እና አካባቢው 7 ሰዎች በጥይት ተመትተው የተገደሉ ሲሆን፤ 25 ሰዎች በጥይት መመታትን ጨምሮ በተለያዩ ምክንቶች ከባድ እና ቀላል የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። ሌሎች ሶስት ሰዎች ደግሞ አካላቸው ላይ በእሳት የመቃጠል አደጋ ደርሶባቸዋል።

በሻሸመኔ ከተማ ከፍተኛ የንብረት ማውደም እና የመዝረፍ ተግባር ተፈፅሟል። የከተማ አስተዳደሩ ባጠናቀረው መረጃ መሰረት 20 ህንፃዎች፣ 35 የመኖሪያ ቤቶች፣ 78 መኪናዎች፣ 79 ሆቴሎች፣ 36 ባለ ሶስት እግር ተሽከርካሪዎች (ባጃጆች)፣ 17 ሞተር ሳይክሎች፣ 28 ሱቆች እና 2 ትምህርት ቤቶች ተቃጥለዋል። በተጨማሪም 15 ህንፃዎች፣ 195 መኖርያ ቤቶች፣ 6 ግሮሰሪዎች እና 63 ሱቆች የመሰባበር አደጋ ደርሶባቸዋል።

በከተማው የነበሩ የፀጥታ ኃይሎች ንብረት ሲቃጠልና ሲዘረፍ እያዩ እንዳልተከላከሉ፤ የፌዴራል ፖሊስም ችግሩን ለማስቆም ቶሎ አለመድረሱን፤ ከደረሰ በኋላም ትዕዛዝ አልተሰጠንም በሚል ምክንያት ጥቃቱን ባለማስቆሙ በከተማው ከፍተኛ የንብረት ውድመት እንደደረሰ የንብረት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ለኢሰመኮ አስረድተዋል።




የከተማው የአስተዳደር አካላት በበኩላቸው በከተማው የነበረው የፖሊስ ኃይል ከ300 ያልበለጠ እንደነበር እና ችግሩ እንደተፈጠረ ተጨማሪ የፌደራል ፖሊስ እንዲላክ የጠየቁ ቢሆንም ዘግይተው መድረሳቸውን እና ከደረሱም በኋላ እርምጃ ውሰዱ አልተባልንም በሚል ሁከቱን ለማስቆም አለመሰማራታቸውን ለኮሚሽኑ ገልጸዋል።

ኢሰመኮ ያነጋገራቸው አብዛኞዎቹ ተጎጂዎች ጥቃቱ ብሔርና ኃይማኖትን መሰረት አድርጎ የተፈጸመባቸው እንደሆነ አስረድተዋል። በጥቃቱ መጀመሪያ አከባቢ የአንድ ብሔር አባላትን ንብረት ኢላማ የማድረግ አዝማሚያ የነበረ

ቢሆንም እየሰፋ ሲመጣ ግን የሁሉንም ብሔር ተወላጆች እና ኃይማኖት ተከታዮች ንብረትን የማውደም እና የመዝረፍ ተግባር ተፈጽሟል።

ኢሰመኮ ለዚህ ሪፖርት መረጃ በሰበሰበበት ወቅት የከተማውን ከንቲባ ጨምሮ ከ584 በላይ ሰዎች በሻሸመኔ ከተማ በደረሰው ጉዳት ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር ውለው ምርመራ እየተደረገባቸው ነበር።

ጥቃቱን ተከትሎ ከ287 በላይ አባወራዎች ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ ሲሆን አስቸኳይ የእለት አርዳታ ከማቅረብ አንፃር ሰፊ ቅሬታ ነበር። የከተማ አስተዳደሩ ባለው አቅም ለተፈናቃዮች እርዳታ እያቀረበ እንዲሁም የተጎዱ መኖሪያ ቤቶችን መልሶ እየጠገነ መሆኑን ገልፆ፤ ሙሉ በሙሉ የወደሙ ንብረቶችን መተካት ከአቅሙ በላይ በመሆኑ ለኦሮሚያ ክልል እና ለፌደራል መንግስት ማሳወቁን ለኮሚሽኑ አስረድቷል።

## 2.19. ጅማ ዞን (ጅማ፣ የቡ እና ሰቃ ከተማዎችን ያጠቃልላል)

የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. በጅማ ዞን የተለያዩ ወረዳዎች ሰልፎች የተደረጉ ሲሆን በአብዛኛዎቹ ቦታዎች ሕዝቡ በአርቲስቱ ግድያ የተሰማውን ሃዘን በሰላማዊ መንገድ በመግለጽ ወደየቤቱ ተመልሷል። ነገር ግን በጅማ ከተማ፣ በመና ወረዳ የቡ ከተማ እና በሰቃ ጨቆርሳ ወረዳ ሰቃ ከተማ ሰልፎቹ ከ4፡ 00 ሰዓት ጀምሮ ወደ ሁከት በመቀየራቸው በሰዎች እና በንብረት ላይ ጉዳት ደርሷል።

አብዛኞቹ በጅማ ዞን የደረሱ ጉዳቶች የንብረት ውድመት ሲሆኑ በጅማ ከተማ የሚገኘው ዶሎሎ ሆቴል ከፍተኛ ቃጠሎና ዝርፍያ ደርሶበታል። በሆቴሉ ላይ በተፈጸመው ጥቃት 1 በሆቴሉ ውስጥ የነበረ እንግዳ በእሳት ተቃጥሎ የሞተ ሲሆን በ2 የሆቴሉ ሰራተኞች ላይ አካላዊ ጥቃት ተፈጽሟል። ኢሰመኮ በሆቴሉ ላይ የደረሰውን ጉዳት ለመመልከት በተገኘበት ጊዜ በቦታው የነበሩ የሆቴሉ ተረኛ የጥበቃ ሰራተኛ በፊትም “ሆቴሉን እናቃጥላለን እያሉ የሚዝቱ ግለሰቦች ነበሩ” በማለት የገለጹ ሲሆን ሌላዋ የእለቱ የሆቴሉ ተረኛ ተቆጣጣሪ የነበረች ሰራተኛ ደግሞ ሆቴሉን ያቃጠሉት ግለሰቦች ከሆቴሉ ከስራ በተባረረች የቀድሞ የሆቴሉ ሰራተኛ እየተመሩ መምጣታቸውን ለኮሚሽኑ ገልፃለች። በተጨማሪም በከተማው ውስጥ የ7 ግለሰቦች የንግድ እና የመኖርያ ቤቶች ተቃጥለዋል።

በመና ወረዳ የቡ ከተማ 2 የግለሰብ መኖሪያ ቤቶች፣ 2 የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ፅ/ቤቶች፣ የወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት እና 2 ተሽከርካሪዎች ተቃጥለዋል። በተመሳሳይ በሰቃ ወረዳ ተሽከርካሪዎች እና የመኖርያ ቤቶችን ጨምሮ በ 8 ንብረቶች ላይ ጉዳት መድረሱን የጅማ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት ገልጿል።

ጥቃቱን ያደረሱት ሰዎች ከከተማ እና ከገጠር የተውጣጡ መሆናቸውን ተጎጂዎች እና ምስክሮች የገለጹ ሲሆን፤ የዞኑ አሰተዳደር አካላት ግን ጥቃቱን የፈጸሙት “በኦነግ ሸኔና የተደራጁ ግለሰቦች ናቸው” ብለዋል።

ከአንድ የከተማው የፖሊስ አባል ከሆነ ተጎጂ በስተቀር ሁሉም ንብረታቸው የወደመባቸው ሰዎች ንብረታቸው ሲቃጠል ለከተማው ፖሊስም ሆነ የኦሮሚያ ልዩ ኃይል በተደጋጋሚ የድረሱልን ጥያቄ ቢያቀርቡም ደርሰው ችግሩን አለማስቆማቸውን፤ አንዳንድ የንብረት ቃጠሎ በደረሰባቸው አካባቢዎች አቅራቢያ የመከላከያ ሰራዊት ካምፕ ቢኖርም ወታደሮቹ ትዕዛዝ አልተሰጠንም በሚል ጥቃቱን ለመከላከል ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ጥቃቱን የማስቆም እርምጃው የተጓተተ እንደነበረ አስረድተዋል።

በጅማ ከተማ በዶሎሎ ሆቴል ላይ ቃጠሎ ሲፈፀም የፀጥታ ኃይሉ እርዳታ ተጠይቆ ባይደርስም ሆቴሉ ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰበት በኋላ "ተጨማሪ ጥቃት እንዳይፈፀምበት ለመጠበቅ የመጡ አምስት የከተማው የፖሊስ አባላት 1,000 ብር (አንድ ሺህ ብር) ካልተከፈለን አንጠብቅም በማለታቸው በድርድር 700 ብር (ሰባት መቶ ብር) ተከፍሏቸው ለመጠበቅ መስማማታቸውን" አንዷት የሆቴሉ ሰራተኛ ለኮሚሽኑ መርማሪዎች ገልጻለች።

በዞኑ ስለነበረው አጠቃላይ ሁኔታ የተጠየቁት የዞኑ የአስተዳደር አካላት መጀመሪያ አካባቢ ሰላማዊ ሰልፍ ስለነበር ችግሩ በዚህ ልክ ይፈጠራል የሚል ግምት ስላልነበራቸው የቅድመ መከላከል ስራ አለመሰራቱን አምነው፤ ችግሩ ከተፈጠረ በኋላ ለማስቆም ያለውን ውስን የሰው ኃይል ማሰማራታቸውን እና የኦሮሚያ ልዩ ኃይልም ድጋፍ በተጠየቀበት ጊዜ ምላሽ በመስጠት ችግሩን በማስቆም ሂደት ላይ መሳተፉን ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

ተጎጂዎች ጥቃቱ ብሔራቸውን ወይም ኃይማኖታቸውን መሰረት ያደረገ መሆኑን ሲገልጹ፤ የዞኑ አስተዳደርና የፖሊስ መምሪያ "በተጨባጭ የተከሰተው ነገር ይህንን አያመለክትም፤ ጥቃቱ የሃይማኖትና የብሔር ሽፋን ቢሰጠውም ጉዳዩ የፖለቲካ አላማ ያለው ነው" ብለዋል።

ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በጥቃቱ ተሳትፈዋል ተብለው የተጠረጠሩ 72 አመራሮችን ጨምሮ 306 ሰዎች በቁጥጥር ስር ውለው ምርመራ እየተደረገባቸው መሆኑን፣ 68 የወረዳ አመራሮች ደግሞ ከኃላፊነታቸው እንዲነሱ መደረጉን የዞኑ የአስተዳደር አካላት ገልጸዋል።

ለዚህ ሪፖረት መረጃ በሚሰበሰብበት ጊዜ ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች የአካባቢው ህብረተሰብ ከሚያደርግላቸው ድጋፍ ውጪ በመንግስት በኩል መልሶ ለማቋቋም ቃል የተገባላቸው ቢሆንም በተጨባጭ የተጀመረ ነገር አለመኖሩን ገልጸዋል። የዞኑ አስተዳደር አካላት በበኩላቸው ተጎጂዎችን መልሶ ለማቋቋም ጥረት በማድረግ ላይ መሆናቸውን ተናግረዋል።

## 2.20. አሰላ ከተማ

በአሰላ ከተማ ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. በአርቲስት ሃጫሉ ግድያ ሐዘናቸውን ለመግለጽ በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ወደ አደባባይ የወጡ ሲሆን ሁኔታውን ወደ ሁከት ለመለወጥ በመሞከሩ በአካባቢው የነበረውን የመከላከያ ሰራዊት ድጋፍ በመጠየቅ ሁኔታውን ለመቆጣጠር መቻሉን የአካባቢው አስተዳደር አካላት ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

በተፈጠረው ሁኔታ በከተማው 4 ሰዎች በፀጥታ ኃይሎች በጥይት ተመተው ሕይወታቸው ሲያልፍ፤ 9 ሰዎች የአካል ጉዳት እንደደረሰባቸው የአካባቢው አስተዳደር አካላት ገልጸዋል። ከዚህ በተጨማሪም 2 የግል እና 3 የመንግስት መኪናዎች ሲቃጠሉ፤ 1 ሱቅ፣ 3 የሞባይል ስልክ መለዋወጫ ሱቆች፣ 1 እንጨት መሰንጠቂያ ማሽን፣ 8 የንግድ እና 8 የግል ቤቶች ላይ በደረሰ ጥቃት በአጠቃላይ 7,105,855 ብር (ሰባት ሚሊዮን አንድ መቶ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ አምስት ብር) የሚገመት የንብረት ጉዳት ደርሷል።

የከተማው አስተዳደር አካላት ጥቃቱ ብልፅግና ፓርቲን የማጥቃት እና በአካባቢው ያሉ ባለሃብቶችን የማሸማቀቅ ይዘት የነበረው መሆኑን እና ታቅዶበት በከተማው በነበሩ እና ከገጠር ወደ ከተማ በገቡ ወጣቶች የተከናወነ እንደነበር አስረድተዋል።

የከተማ አስተዳደሩ መጀመሪያ አከባቢ ሰልፈኞቹ ወደ ጎዳና የወጡት ሐዘናቸውን ለመግለጽ ነው በሚል ዝምታን መምረጡንና ዋና ዋና የሚባሉ የንግድ ተቋማትን፣ ባንኮችን እና የመንግስት ተቋማትን የመጠበቅ ስራ ላይ ያተኮረ መሆኑን፤ ነገር ግን በግርግሩ በተሳተፉት ሰዎች ሰፊ ጥቃት ማድረስ ሲጀመር ከከተማው ፖሊስ አቅም በላይ በመሆኑ የመከላከያ ሰራዊት እና የክልሉን ልዩ ኃይል ድጋፍ ተጠይቆ ችግሩን መቆጣጠር መቻሉን ገልጿል።

በከተማው ጥቃቱን በመፈፀም የተጠረጠሩ 23 ሰዎች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን እና ሕዝቡን በማስተባበር ተጎጂዎችን ለመደገፍ እንዲቻል የጉዳቱን መጠን እየለየ መሆኑን የከተማ አስተዳደሩ ለኮሚሽኑ ገልጿል።

### *2.21. ጎባ ከተማ*

በጎባ ከተማ ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. የከተማው እና ከገጠር አካባቢዎች የመጡ ሰዎች ሰልፍ ማድረግ ጀምረው በኋላ ሁኔታው ወደ ሁከት ተቀይሯል። በተፈጠረው ሁከት 1 የፖሊስ አባል እና 1 ግለሰብ በጥይት ተመትተው ሞተዋል፣ 5 ቤቶች ሙሉ ለሙሉ ሲቃጠሉሌሎች 39 ቤቶች ላይ ጉዳት ደርሷል።

የፀጥታ አካላት በተለይም መከላከያ ሰራዊት "ከበላይ አልታዘዝንም" በማለት ጥቃቱን ለማስቆም እርምጃ አለመውሰዳቸውን፤ ከቀኑ 9፡00 ሰዓት በኋላ ግን ትእዛዝ ደርሶናል በሚል ሰላም የማስፈን እርምጃ መውሰድ መጀመራቸውን ተጎጂዎች እና ምስክሮች አስረድተዋል። በከተማው የተፈጠረውን ሁከት ለማረጋጋት የአገር ሽማግሌዎች ከፍተኛ አስተዋጽዎ ማድረጋቸውን ኢሰመኮ ተገንዝቧል።

> በከተማው የተፈጠረውን ሁከት ለማረጋጋት የአገር ሽማግሌዎች ከፍተኛ አስተዋጽዎ ማድረጋቸውን ኢሰመኮ ተገንዝቧል።

በጎባ ከተማ የተፈጸመው ጥቃት በዋነኝነት ኃይማኖትን መሰረት ያደረገ እንደነበር ተጎጂዎች የገለፁ ሲሆን፤ ለዚህም ማሳያ ተጎጂዎች ክርስቲያን የሆኑ የአማራ እና የኦሮሞ ብሔርተወላጆች መሆናቸው እንደሆነ ተጎጂዎች ለኮሚሽኑ ገልጸዋል። የአካባቢው አስተዳደር አካላት ጥቃቱ የፖለቲካ አንድምታ እንደነበረው እና ጥቃት ፈጻሚዎቹ "ብልጽግናን አንፈልግም" በማለት መፈክር ያሰሙ እንደነበር ገልጸዋል።

ሶስት የመንግስት ሰራተኞችን ጨምሮ 56 ሰዎች በጎባ ከተማ ከተፈጸመው ጥቃት ጋር በተያያዘ ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር ውለዋል። ከእነዚህ መካከል ያለበቂ መረጃ ተጠርጣሪዎችን ለቋል በሚል የታሰረ የፖሊስ አዛዥ ይገኝበታል።

የአካባቢው አስተዳደር አካላት በራሳቸው ተነሳሽነት ቀላል የንብረት ጉዳት የደረሰባቸው ተጎጂዎችን ማገዛቸውን እና ሙሉ በሙሉ ንብረታቸው ለወደመባቸው 5 ተጎጂዎች ድጋፍ ለማድረግ እየሰሩ መሆኑን፤ ነገር ግን የከተማው አቅም ውስን ስለሆነ ተጨማሪ ድጋፍ እንደሚያስፈልግ ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

### *2.22. ኢተያ ከተማ*

ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. የኢተያ ከተማ ወጣቶች የአርቲስት ሃጫሉ መገደልን ምክንያት በማድረግ ሐዘናቸውን ለመግለጽ ሰልፍ እንደጀመሩ ሁኔታው ወደ ሁከት ተቀይሯል። ጥቃት ፈፃሚዎች 2 ሰዎችን መግደላቸውን፣ 31 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ማድረሳቸውን እና ከፍተኛ ግምት ያለው ንብረት ማቃጠላቸውን የአካባቢው አስተዳደር አካላት ገልጸዋል።

የመንግስት አካላት ጉዳዩን ለመቆጣጠር ጥረት ቢያደርጉም አባገዳዎች፣ የአገር ሽማግሌዎች እና ሃደ ሲቄዎች ሰልፈኞቹን በማረጋጋት ሁኔታው እንዳይባባስ ከፍተኛ ሚና እንደነበራቸው ምስክሮች እና የአካባቢው የአስተዳደር አካላት ገልጸዋል።

የአካባቢው አስተዳደር አካላት ጥቃቱ ግለሰቦችን ለማጥቃት ያለመ፣ ኃይማኖትን መሰረት ያደረገ፤ ፖለቲካዊ ይዘት የነበረው፤ በተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እና አመራሮች አሰተባባሪነት የተፈጸመ እና ብልጽግና ፓርቲን ለማሽማቀቅ ያለመ እንደነበር ገልጸዋል። ለጥቃቱ ተጠያቂ የሆኑ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን እና ለተጎጂዎች ድጋፍ ለማድረግ ኮሚቴ በማቋቋም ስራ መጀመሩን የአካባቢው አስተዳደር አካላት ለኮሚሽኑ አስረድተዋል።

## 2.23. ጀጁ ወረዳ አርቦዬ ከተማ

ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. የአርቲስት ሃጫሉ መገደልን ምክንያት በማድረግ የአርቦዬ ከተማ እና የአካባቢው ነዋሪዎች ሐዘናቸውን ለመግለጽ የጀመሩት ሰልፍ ወደ ሁከት ተቀይሯል። በእለቱ የከተማው እና ከአጎራባች የገጠር ቀበሌዎች የተውጣጡ ሰዎች በብዛት ወደ ጎዳና በመውጣት ዱላ፣ ቆንጨራ እና ድንጋይ ይዘው በወረዳው አመራሮች እና የብልጽግና ፓርቲ አባላት ላይ ድብደባ ለመፈጸም መሞከራቸውን እና በፖሊስ ጣቢያም ላይ ድንጋይ ሲወራወሩ የነበረ መሆኑን የከተማው አስተዳደር አካላት ገልጸዋል። በተጨማሪም የኦሮሞ ተወላጅ ያልሆኑ ያካባቢው ነዋሪዎች ላይ የአካል እና የንብረት ጥቃት ተፈጽሟል።

በከተማው ከተከሰተው ሁከት ጋር በተያያዘ 2 ሰዎች በሚሊሻ አባላት በተተኮሰ ጥይት ተመትተው የተገደሉ ሲሆን ሌላ አንድ ግለሰብ ደግሞ በሁከቱ ተሳታፊዎች ተደብድቦ ሞቷል። ከዚህ በተጨማሪም 1 ሆቴል፣ 3 መኖሪያ ቤቶች እና የወርልድ ቪዥን መስሪያ ቤት ሙሉ በሙሉ መዘረፋቸውን እንዲሁም 16 መኖሪያ ቤቶች በድንጋይ መሰባበራቸውን የአካባቢው አስተዳደር አካላት ገልጸዋል።

በከተማዋ ከተፈጠረው ሁከት ጋር በተያያዘ 6 አመራሮችን ጨምሮ 120 ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር የዋሉ ሲሆን ከተዘረፉት ንብረቶች ውስጥ የተወሰነውን ለባለቤቶቹ ማስመለስ መቻሉን ለማወቅ ተችሏል።

## 2.24. አርሲ ሮቤ ከተማ

ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. ጠዋት ከ 2፡00 ሰዓት ጀምሮ በአርሲ ሮቤ ከተማ ከገጠር እና ከከተማው የተውጣጡ ወጣቶች በአርቲስት ሃጫሉ መገደል የተሰማቸውን ሃዘን ለመግለጽ በሚመስል መልኩ ሰልፍ የተጀመረ ሲሆን ሁኔታው ወዲያው ሁከት እና ጥቃት ወደ ማድረስ ተቀይሯል።

በከተማው በተፈጸመው ጥቃት በ2 ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት እና በ15 የንግድ ቤቶች ላይ የመሰባበርና ዝርፊያ ተግባር ተፈፅሟል። የከተማው ፖሊስ ችግሩን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ቢሞክርም ጥቃት ፈጻሚዎቹ በቁጥር ብዙ በመሆናቸው ለመቆጣጠር እንደተቸገረ እና በአካባቢው የነበረው ልዩ ኃይልም በፍጥነት ድጋፍ ባለማድረጉ ጉዳት መድረሱን የአካባቢው የአስተዳደር አካላት ገልጸዋል።

ጥቃቱ ብሔር እና ኃይማኖት መሰረት ያደረገ እንደነበር እና ጥቃት ፈጻሚዎቹ ጥቃት ሲፈፅሙ “የአማራ፣ የክርስቲያን፣ የነፍጠኛ ቤት ነው” ይሉ እንደነበረ ተጎጂዎች ለኢሰመኮ አስረድተዋል። በከተማዋ ከተፈጠረው ሁከት እና ጥፋት ጋር በተያያዘ 26 ሰዎች ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር እንደዋሉ የአስተዳደር አካላት ለኮሚሽኑ ገልጸዋል።

## 2.25. መርቲ ወረዳ (አቦምሳ እና በሌ ከተሞች)

ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. የአርቲስት ሃጫሉ መገደልን ምክንያት በማድረግ በመርቲ ወረዳ የሚኖር በርካታ ሕዝብ ለሰልፍ የወጣ ሲሆን፤ መጀመሪያ ሰላማዊ የነበረው ሰልፍ ከሰዓት በኋላ ወደ ሁከት እና ብጥብጥ ተቀይሮ በሰዎችና በንብረት ላይ ጉዳት ደርሷል።

በወረዳው በተፈጠረው ሁከት በአጠቃላይ የ3 ሰዎች ህይወት አልፏል። በአቦምሳ ከተማ የነበረው ሰልፍ ወደ ሁከት ሲያመራ የከተማው ፖሊስ እና የኦሮሚያ ልዩ ኃይል ተቆጣጥረውት የነበረ ቢሆንም ሰልፉ ተበትኖ ከገጠር የመጡ ሰልፈኞች ሲመለሱ በከተማው መውጫ ላይ 1 መምህር በዱላ ደብድበው ገድለዋል። በበሌ ከተማ ደግሞ 2 ወጣቶች ግለሰብ ቤት በመግባት ንብረት ለመዝረፍ ሲሞክሩ በባለቤቱ በተተኮሰ ጥይት ተገድለዋል። ሁለቱን ወጣቶች ተኩሶ በመግደል የተጠረጠረውን ግለሰብ ጨምሮ ከ20 በላይ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የወረዳው አስተዳደር አካላት ገልጸዋል።

## 2.26. ጊንጪ ከተማ

የአርቲስት ሃጫሉ ግድያን ምክንያት በማድረግ በጊንጪ ከተማ በተከሰተው ሁከት 2 ሰዎች ሲገደሉ በ8 ሰዎች ላይ አካላዊ ጉዳት ደርሷል። በተጨማሪም በግለሰቦች መኖርያ ቤት፣ ንግድ ቤት እና ተሽከርካሪ ላይ በተፈጸመ ጥቃት ግምቱ 694,960 ብር (ስድስት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ብር) የሆነ ጉዳት፣ የዳንዲ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት ላይ 200,000 ብር (ሁለት መቶ ሺህ ብር) የሚገመት ጉዳት፣ የፖሊስ አባል የሆነ አንድ ግለሰብ ቤት ደግሞ 50,000 ብር (ሃምሳ ሺህ ብር) የሚገመት የቤት ቁሳቁስ እና አልባሳት ላይ ጉዳት የደረሰ ሲሆን የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን መ/ቤት ላይ በተፈጸመ ጥቃት 3 ክላሽኒኮቭ እና 2 "ኋላቀር" የጦር መሳሪያዎች ተዘርፈዋል።

ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. ምሽት የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያ ከመሰማቱ በፊት መንግስትን የሚያወግዙ በራሪ ጽሁፎች ባልታወቁ ሰዎች በጊንጪ ከተማ ሲበተን እንደነበር፤ ግድያው ከተሰማ በኋላ ምሽቱን በነበረው አመጽ ከሌሊቱ 8፡00 ሰዓት ላይ በግለሰብ ቤት ላይ ቦምብ ተወርውሮ በቤቱ ላይ ጉዳት መድረሱን የአካባቢው የአስተዳደር አካላት ገልጸዋል። ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ በዋና መንገዶች ላይ የተሰበሰቡ ሰዎች ጎማ የማቃጠል፤ የወረዳውን ፖሊስ ጽ/ቤት ከበው በቁጥጥር ስር የነበሩ ሰዎችን ስም እየጠሩ የፖለቲካ እስረኞች ስለሆኑ ይፈቱልን በማለት ድንጋይ መወራወር እና የግለሰብ ንብረት የማውደም ተግባራት ተፈጽመዋል።

ሁኔታውን ለማረጋጋት ፖሊስ ከአገር ሽማግሌዎች ጋር ተወያይቶ ይፈቱ የተባሉት 6 ሰዎች ከፖሊስ ጣቢያው እንዲለቀቁ መደረጉን፤ ያም ሆኖ አመጹ እየተጋጋለ በጦር መሳሪያዎች ጭምር በመጠቀም እስከ ሰኔ 25 ቀን 2012 ዓ.ም. ድረስ ብሔርን እና ፖለቲካ አመለካከትን መሰረት ያደረገ ጥቃት መፈጸሙን የአካባቢው አስተዳደር አካላት አስረድተዋል። በተፈጠረው ሁኔታ ውስጥ የፀጥታ ኃይሎች በወሰዱት እርምጃ ሞትና የአካል ጉዳት ደርሷል።

## 2.27. ሱሉልታ ከተማ

የአርቲስት ሃጫሉ ግድያን ምክንያት በማድረግ በሱሉልታ ከተማ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. በተቀሰቀሰው ሁከት በ31 ቤቶች እና 1 የፖሊስ መኪናን ጨምሮ 4 ተሽከርካሪዎች መስታወታቸውን የመሰባበር ጉዳት ደርሷል። የመፈንከት ጉዳት ከደረሰበት አንድ ሰው ውጪ በሰዎች ላይ ጉዳት አለመድረሱን የአካባቢው አስተዳደር አካላት ገልጸዋል።

በከተማው ብሔርን ለይቶ ለማጥቃት የመጣ ሃይል እንደነበረ እና እንደ ሩዋንዳ በብሔሮች መካከል የእርስ በእርስ ግጭት/እልቂት ለመፍጠር ታስቦ እንደነበር እንዲሁም ብዛት ያለው የጦር መሳሪያ መያዛቸውን የከተማው አስተዳደር አካላት ገልጸዋል።

በጥቃቱ ተሳትፈዋል ተብለው የተጠረጠሩ 53 ሰዎች በቁጥጥር ስር ውለው በተደረገው ማጣራት 42ቱ መለቀቃቸውን የከተማው አስተዳደር አካላት አስረድተዋል።

## 2.28. ገርበ ጉራቻ (ኩዩ ወረዳ)

ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. በገርበ ጉራቻ ከተማ በርካታ ሕዝብ ሃዘኑን ለመግለጽ ሰልፍ ተካሂዷል። በዚህ መሃል በመንግስት ላይ ተቃውሞ ለማሰማት እና ሁከት ለመፍጠር የሞከሩ ሰዎች ቢኖሩም የንግድ እንቅስቃሴ ከመቆሙ በቀር በወረዳው በሰውም ሆነ በንብረት ላይ ጉዳት አልደረሰም። መኪና ለማቃጠል ሙከራ ያደረገ ሰው መያዙን እና የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን ጨምሮ 8 ሰዎች ተጠርጥረው ተይዘው በዋስ መለቀቃቸውን ለማወቅ ተችሏል።

## 2.29. ሀሳሳ

የአርቲስት ሃጫሉ ግድያን ምክንያት በማድረግ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. በሀሳሳ ከተማ በተፈጠረው ሁከት በአጠቃላይ 4 ሰዎች የሞቱ ሲሆን ከእነዚህም መካከል ሁለቱ በፀጥታ ኃይሎች በተተኮሰ ጥይት የተገደሉ ሲሆኑ ሁለቱ ደግሞ በግለሰቦች በተፈጸመባቸው ድብደባ ሕይወታቸው አልፏል። በተጨማሪም በእለቱ የ5 ግለሰቦች ንብረት ላይ የማቃጠል እና የመዝረፍ ጥቃት ተፈጽሟል።

## 2.30. ነጌሌ ስጋሎ

ከአርቲስት ሃጫሉ ግድያ ጋር በተያየዘ ከመጠነኛ ተቃውሞና መንገድ ከመዝጋት ውጪ በነጌሌ ከተማ የከፋ የፀጥታ ችግር አልነበረም። ሆኖም ግን ሰኔ 25 ቀን 2012 ዓ.ም. ቅኝት ያደርጉ የነበሩ የኦሮሚያ ፖሊስ ልዩ ኃይል አባላት አልፎ አልፎ ጥይት ይተኩሱ ስለ ነበር አንድ መንገድ ላይ ተኝቶ የነበረ የአዕምሮ ህመምተኛ በተኛበት በተባራሪ ጥይት ተመትቶ መገደሉን በቦታው የነበሩ ምስክሮች ለኢሰመኮ ገልጸዋል።

## 2.31. በቆጂ

የአርቲስት ሃጫሉ ግድያን ምክንያት በማድረግ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. በበቆጂ ከተማ በተፈጠረው ሁከት 3 የንግድ ድርጅቶች ላይ መጠነኛ ጥቃት ደርሶባቸዋል። የከተማው አስተዳደርና የአገር ሽማግሌዎች በሰሩት የማረጋጋት ስራ የከፋ ጉዳት ሳይደርስ የከተማውን የፀጥታ ሁኔታ መቆጣጠር ተችሏል።

## 2.32. ቢሾፍቱ

የአርቲስት ሃጫሉ ግድያን ተከትሎ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. በቢሾፍቱ ከተማ ሕዝቡ የተሰማውን ሃዘን ለመግለጽ አደባባይ የወጣ ሲሆን ከቆይታ በኋላ ሰልፉ ወደ ሁከት በመቀየሩ ንብረት የማቃጠል እና የዝርፊያ ተግባራት ተፈጽሟል።

ሁኔታውን ለመቆጣጠር በፀጥታ ኃይሎች በተወሰደ እርምጃ 3 ሰዎች በጥይት ተመትተው የተገደሉ መሆኑን እና ሌላ 1 ሰው ከግለሰብ ቤት ውስጥ በተተኮሰ ጥይት መሞቱን የአካባቢው አስተዳደር አካላት ለኢሰመኮ ገልጸዋል። በከተማው

ቁጥራቸው ከ40 በላይ የሚሆኑ ሰዎች በቢሾፍቱ ከተማ ከደረሰው ሁከት ጋር በተያያዘ ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር ውለው ምርመራ እየተደረገባቸው ነበር። ሆኖም ግን በፀጥታ ኃይሎች የተፈፀሙ ግድያዎችን በሚመለከት የተደረገ ምርመራ ስለመኖሩ አልታወቀም።

## 2.33. ሞጆ

ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. በሞጆ ከተማ ሕዝቡ በአርቲስት ሃጫሉ መገደል የተሰማውን ሃዘን ለመግለጽ አደባባይ የወጣ ሲሆን በሂደት ረብሻ ለማሥነሳት ተሞክሮ በፀጥታ ኃይሎች በተወሰደ እርምጃ 1 ሰው በጥይት ተገድሏል። ሆኖም ግን በተከናወነው የተቀናጀ የሰላም ማስከበር ስራ በግለሰቦች እና በመንግስት ንብረት ላይ ጉዳት አለመድረሱን የአካባቢው አስተዳደር አካላት ለኢሰመኮ አስረድተዋል።

## 2.34. መቂ

ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. የአርቲስት ሃጫሉ ግድያን ምክንያት በማድረግ በመቂ ከተማ በተፈጠረው የፀጥታ ችግር 3 ሰዎች በጥይት የተገደሉ ሲሆን 3 የግለሰብ የእህል ወፍጮዎች ደግሞ በከፊል ጉዳት ደርሶባቸዋል።

## 2.35. ዱከም

ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. በዱከም ከተማ የአርቲስት ሃጫሉ ግድያን ምክንያት በማድረግ ሕዝብ ወደ ጎዳና ወጥቶ ሃዘኑን በተቃውሞ እንቅስቃሴ በታጀበ ሁኔታ ገልጿል። ሆኖም ግን ከህብረተሰቡ ጋር በቅንጅት በተሰራ የማረጋጋት ስራ ምንም ጉዳት ሳይደርስ መጠናቀቁን የከተማው አስተዳደር ለኢሰመኮ ገልጿል።

## 2.36. ለገጣፎ ለገዳዲ

የአርቲስት ሃጫሉ ግድያን ተከትሎ በለገጣፎ ለገዳዲ ከተማ በሰውም ሆነ በንብረት ላይ የደረሰ ጉዳት የለም። ነገር ግን ሰኔ 25 ቀን 2012 ዓ.ም. ወጣቶች "ግጭት ቀስቃሽ ቲሸርት" ለብሰው ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ በመሞከራቸው 8 ወጣቶች በፖሊስ በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የከተማው አስተዳደር ለኮሚሽኑ አስረድቷል።

## 2.37. ገላን ከተማ

ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. በገላን ከተማ በርካታ ሰዎች በአርቲስት ሃጫሉ ግድያ የተሰማቸውን ሃዘን ለመግለጽ አደባባይ የወጡ ሲሆን ጉዳት ሳይደርስ ሰልፉ መጠናቀቁን እና ሁከት ለማነሳሳት የሞከሩ 10 ሰዎች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን የከተማው አስተዳደር አካላት ለኢሰመኮ ገልጸዋል።

## 2.38. ሲሬ ከተማ

ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. በሲሬ ከተማ የአርቲስት ሃጫሉን መገደል ምክንያት በማድረግ ሰልፍ የነበረ ቢሆንም የከተማው አስተዳደር፣ ታጣቂዎች እና ፖሊስ አካባቢውን በመጠበቅ፣ ጥንቃቄ በማድረግ እና ሕዝቡን ማረጋጋት በመቻላቸው እንዲሁም ከዚህ በፊት በከተማዋ ጥቃት በደረሰ ጊዜ ሕዝቡ እና ሽማግሌዎች ተመሳሳይ ችግር እንዳይደገም ለመስራት ተስማምተው ስለነበረ ምንም አይነት ጉዳት ሳይከሰት ሰልፍ በሰላም መጠናቀቁን የከተማው አስተዳደር አካላት ለኮሚሽኑ ገልጸዋል።

# 3. በምርመራው የተለዩ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት

## *3.1. ግድያ እና አካላዊና ሥነ-ልቦናዊ ጉዳት*

የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ድንገተኛ ግድያ ከተሰማበት ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. ምሽት አንስቶ ጩኸት መሰማት እንደተጀመረ፤ የተወሰኑ ወጣቶች በሰልፍ መልክና በቡድን ወደ ጎዳና በመውጣት ጎማ በማቃጠልና ድንጋይ በመደርደር መንገድ መዝጋት እንዲሁም ሰዎችን ማጥቃት እና ንብረት ማውደም እንደጀመሩና በማግስቱ ሁኔታው ተባብሶ መቀጠሉ ምርመራዊ በተካሄደባቸው 40 አካባቢዎች በሁሉም የነበረ ሂደት ነው። ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት አካባቢ ጀምሮ ብዙ ሰዎች ሐዘናቸውን ለመግለጽ በሚመስል መልኩ ወደ ጎዳና/አደባባይ መውጣት የጀመሩ ሲሆን በመጀመሪያ ሁኔታው ሰላማዊ ሰልፍ ቢመስልም ወደ ከፍተኛ ሁከትና ጥቃት ማድረስ ተቀይሮ በሁከት ፈጣሪ ሰዎችና ቡድኖች በየከተሞቹና በየመንደሩ በሰላም የሚኖሩ ሰዎች በቤታቸውና በየጎዳናው በግፍና በጭካኔ ተገድለዋል፤ ተደብድበው የአካልና የሥነ-ልቦና ጉዳት ደርሶባቸዋል፤ ቤትና ንብረታቸው በከፊል ተዘርፏል፤ በአብዛኛው ግን ሆነ ተብሎ በእሳት ተቃጥሏል። በዚህም የተነሳ ብዙ ሰዎች ከመኖሪያቸው ተፈናቅለዋል። በጥቃቱ የተወሰኑ የየከተሞቹ ነዋሪዎችና ከአካባቢ የገጠር ቀበሌዎች በመኪና ተጭነው የመጡ ሰዎችም ተሳታፊዎች ነበሩ።

በተለይም በባቱ፣ ሻሸመኔ፣ ጭሮ፣ ሀሮማያ፣ ወሊሶ፣ አዳማ፣ ጎባ፣ አርሲ ነጌሌ፣ አርሲ ሮቤ፣ ዴራ፣ አዳባ፣ ኮፈሌ፣ ጀጁ፣ አጋርፋ፣ ኢተያ፣ መርቲ ወረዳ እና ሌሎች አካባቢዎች የፀጥታ አካላት በወሰዱት እርምጃ በጥይት የተገደሉትንና የቆሰሉትን ሳይጨምር ቢያንስ 35 ሰዎች በሁከት ፈጣሪ ቡድኖች ሲገደሉ፤ 306 ሰዎች ደግሞ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። ከተገደሉት ሰዎች ውስጥ አዛውንቶች፣ ካህናት፣ ሴቶች እና ሕጻናት ይገኙበታል።

በአጠቃላይ በመላው ኦሮሚያ በነበረው ብጥብጥ በሁከት ፈጣሪ ቡድኖች ብቻ ቢያንስ 35 ሰዎች ሲገደሉ፤ 306 ሰዎች ደግሞ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። ከተገደሉት ሰዎች ውስጥ አዛውንቶች፣ ካህናት፣ ሴቶች እና ሕጻናት ይገኙበታል።

በዚህ መጠነ ሰፊ ጥቃት የተሳተፉት ብዙ ቁጥር ያላቸው ከቦታ ቦታ በቡድን ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ሰዎች ሲሆኑ፤ በጩቤ፣ በድንጋይ፣ በእሳት፣ በኤሌክትሪክ ገመድ፣ በዱላ፣ በዶማ፣ በገጀራ እና በመጥረቢያ ተጠቅመው ሰዎችን ደብድበዋል፣ የአካል ጉዳት አድርሰዋል፣ ፍጹም ግፍና ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ በማሰቃየት ወይም በማረድ ጭምር ሰዎችን ገድለዋል። አጥቂዎቹ ሰዎችና ቡድኖች የነዋሪዎችን ቤት በመስበርና በመግባት ከፊሎቹን በየቤታቸው፤ ከፊሎቹን ከቤታቸው አስገድዶ መንገድ ላይ በማስወጣት ገድለዋል፤ ሬሳቸውን መሬት ላይ በመጎተትና በጎዳና ላይ በመጣል አስከሬናቸው ለሰዓታት ሳይነሳ እንዲቆይ አድርገዋል።

የአካል ጉዳት ከደረሰባቸው ሰዎች ውስጥ መላው አካላቸው በመሰባበሩ ስቃይ በተሞላበት ሁኔታ በሕክምና ላይ ያሉ ሰዎች ነበሩ። ከፍተኛ ድብደባ ደርሶባቸው ከሞት የተረፉት አብዛኞቹ ሰዎች አጥቂዎቹ ገለናቸዋል ብለው ጥለዋቸው የሄዱ ሰዎች ናቸው። አጥቂዎቹ ከፈጸሙት ድብደባ፣ ግድያና ንብረት ማውደም በተጨማሪ ተጎጂዎችንና የተጎጂ ቤተሰቦችን ብሔርን መሰረት ያደረጉ ስድቦች ሲሳደቡ፣ ሲያንቋሽሹ፣ ሲያስፈራሩና ሲዝቱባቸው እነደነበርና ይህም ሰላማዊ ነዋሪዎች በብሔር ወይም በኃይማኖታቸው ምክንያት ለጥቃት የመጋለጥ ከፍተኛ ስጋትና የሥነ-ልቦና ጭንቀት እንደፈጠረባቸው ኢሰመኮ ተገንዝቧል።

በሰዎችና በንብረት ላይ ጥቃት ከመድረሱ አስቀድሞ ለመከላከከል እና ጥቃቱን ለማስቆም የፀጥታ አካላት የነበራቸው ሚና ከቦታ ቦታ የተለያየ እንደነበር የመንግስት ኃላፊዎች፣ ተጎጂዎች፣ የተጎጂ ቤተሰቦችና የአይን ምስክሮች አስረድተዋል። ጥቃት በተሞከረባቸው የተወሰኑ አካባቢዎች የፀጥታ ኃይሉ ቅድመ ዝግጅት በማድረጉ ጉዳቱን ለመከላከል፤ ለማስቆም ወይም ለመቀነስ ተችሏል። በአንጻሩ የፀጥታ አካሉ የወንጀል መከላከል ወይም የማስቆም አቅም፣ ዝግጁነት እና ፍላጎት ዝቅተኛ በነበረባቸው አካባቢዎች፤ በተለይ በባቱ፣ ሻሸመኔ፣ ጭሮ፣ ሀሮማያ፣ ወሊሶ፣ አዳማ፣ ጎባ፣ አርሲ ነጌሌ፣ አርሲ ሮቤ፣ ዴራ፣ አዳባ፣ አጋርፋ፣ ኮፈሌ፣ ጀጁ፣ እና ኢተያ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል።

ተጎጂዎችና የተጎጂ ቤተሰቦች ለኢሰመኮ እንዳስረዱት ከዚህ አደጋ በፊት ጥቃቶች ሊፈጸሙ እንደሚችሉ ምልክቶች ቢኖሩም፤ መንግስት አፋጣኝ የእርምት እርምጃ ባለመውሰዱ ለዚህ የከፋ ችግር ተዳርገናል ብለዋል። በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች በተለይ በክርስቲያን እምነት ተከታዮች ላይ ከ1998 ዓ.ም. ጀምሮ በተለያየ ጊዜ ጉዳት ሲደርስ መቆየቱን የመንግስት አካላት ቢያውቁም ምንም የማስተካከያ እርምጃ እንዳልተወሰደ አስረድተዋል።

> “ ሌላው ቀርቶ ጥቃት ከደረሰ ከብዙ ሰዓታት በኋላ እንኳን አምቡላንስ እንዳይገባ አጥቂዎች ሲያግዱ የደረሰ አልነበረም፤ ጥቃት አድራሾች አጥፍተው ሲበቃቸው ነው ጥለው የሄዱት፤ በአንዳንድ ቦታዎች የፀጥታ ኃይሎች የደረሱት ጥቃቱ ከተፈጸመ በኋላ ነው፤ በብዙ ቦታዎች ከፀጥታ አካላት ይልቅ ጎረቤቶች፣ የኃይማኖት አባቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች እና አባገዳዎች ባደረጉት ጥረት አደጋውን ለመቀነስ ተችሏል። ”

ጥቃት በተፈጸመባቸው ብዙዎቹ ቦታዎች ነዋሪዎችና ተጎጂዎች ጥቃቱ በተፈጸመበት ወቅት “ለክልሉ ልዩ ኃይል እና ለከተማ ፖሊስ በተደጋጋሚ ስልክ ብንደውልም የሚደርስልን ኃይል አልነበረም፤ አንዳንድ ስልኮች በጭራሽ አይሰሩም ነበር፤ በስልክ አግኝተን ያነጋገርናቸው የተወሰኑ ኃላፊዎች ደግሞ ‘ትእዛዝ አልተሰጠንም’፤ ‘ኃይል የለንም’፤ ‘የግለሰብ ንብረት ጠብቁ አልተባልንም’ የሚል ምላሽ ሰጥተውናል” በማለት ገልጸዋል። ጥቃት ፈጻሚዎቹ በብዙ ቦታዎች በተደራጀ መልኩ እየተመላለሱ ጥፋት ሲፈጽሙ እንኳን አንድም የሚከላከል የፀጥታ አካል አልነበረም በማለት አስረድተዋል። አንድ ተጎጂ ሁኔታውን ለኮሚሽኑ በምሬት ሲገልጹ “መንግስት ያለ አይመስልም ነበር” ብለዋል። ነዋሪዎች ለኮሚሽኑ ጨምረው እንዳስረዱት፤ “ሌላው ቀርቶ ጥቃት ከደረሰ ከብዙ ሰዓታት በኋላ እንኳን አምቡላንስ እንዳይገባ አጥቂዎች ሲያግዱ የደረሰ አልነበረም፤ ጥቃት አድራሾች አጥፍተው ሲበቃቸው ነው ጥለው የሄዱት፤ በአንዳንድ ቦታዎች የፀጥታ ኃይሎች የደረሱት ጥቃቱ ከተፈጸመ በኋላ ነው፤ በብዙ ቦታዎች ከፀጥታ አካላት ይልቅ ጎረቤቶች፣ የኃይማኖት አባቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች እና አባገዳዎች ባደረጉት ጥረት አደጋውን ለመቀነስ ተችሏል”።

በተወሰኑ አካባቢዎች ደግሞ ፖሊስ ጥቃቱን እያየ በዝምታ ማለፉን ጥቃቱ የደረሰባቸው ነዋሪዎችና ምስክሮች በከፍተኛ ቅሬታ ለኮሚሽኑ ገልጸዋል። እንደ ተጎጂዎች ገለጻ “ፖሊስ አጥቂዎችን ለመበተን ጥረት አላደረገም፤ ጥይት ወደ ላይ እንኳን አልተኮሰም፤ ይልቁንም የተወሰኑ የፀጥታ ኃይሉ አባላት ለጥቃት አድርሾቹ እንደ ደጀን ሆነው ጥቃት ሲፈፅሙ ጥበቃ ያደርጉላቸው ነበር”።

ኢ.ሰመኮ ያነጋገራቸው የአካባቢ መስተዳድር እና የፀጥታ ኃላፊዎች ጉዳቱን ለማስቆም አለመቻላቸውን አምነው፤ ለዚህም ምክንያቱ ጥቃቱ በድንገት መድረሱና አስቀድሞ የሚታወቅ አለመሆኑ፤ የደህንነት ጥበቃ ስራቸው ቅድሚያ የሰጠው ለመንግስትና ከፍተኛ የልማት ተቋማት፣ ባንኮችና የኃይማኖት ተቋማት የነበረ መሆኑን፤ ጥቃቱን ለመከላከል እና ጥበቃ ለማድረግ ቢሞከርም ከፀጥታ ኃይሉ አቅም በላይ መሆኑን፤ ተጨማሪ የፀጥታ ኃይል ቢጠየቅም ቶሎ ምላሽ ባለመሰጠቱ እና መንገድም በመዘጋቱ ምክንያት ተጨማሪው የፀጥታ ኃይል በጊዜ ለመድረስ ባለመቻሉ መሆኑን ገልጸዋል።

> ኮሚሽኑ ባካሄደው ምርመራ ለመረዳት እንደተቻለው የጥቃቱ የቅርብ መነሻ ምክንያት (trigger factor) የአርቲስት ሃጫሉ መገደል ቢሆንም፤ በብዙ ቦታዎች ኃይማኖት እና ብሔር በመለየት የማጥቃት አዝማሚያ ነበር። ጥቃት ፈፃሚዎቹ ተጠቂዎችን በዋነኝነት በኃይማኖታቸው ወይም በብሔራቸው ሆነ ብለው እየለዩና እየመረጡ ያጠቁ ነበር።

ኮሚሽኑ ባካሄደው ምርመራ ለመረዳት እንደተቻለው የጥቃቱ የቅርብ መነሻ ምክንያት (trigger factor) የአርቲስት ሃጫሉ መገደል ቢሆንም፤ በብዙ ቦታዎች ኃይማኖት እና ብሔር በመለየት የማጥቃት አዝማሚያ ነበር። አጥቂዎቹ ቡድኖችና ሰዎች ተጠቂዎችን በዋነኝነት በኃይማኖታቸው ወይም በብሔራቸው ሆነ ብለው እየለዩና እየመረጡ ያጠቁ ነበር።

የጥቃቱ ባህሪና መጠን እንደየአካባቢው ሁኔታ የሚለያይ ቢሆንም በአመዛኙ፤ የክርስቲያን እምነት ተከታዮች በብዛት በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ጥቃቱ በአማራ ብሔር ተወላጆች ላይ ያነጣጠረ ሲሆን፤ የእስልምና እምነት ተከታዮች በብዛት በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ደግሞ በኦሮቶዶክስ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ነበር። አጥቂዎቹ ቡድኖችና ሰዎች ከቦታ ቦታ በሰልፍ ሲንቀሳቀሱና ጥቃት በሚፈጽሙበት ወቅት ሲያሰሙት የነበሩት መፈክርና የቅስቀሳ ንግግሮች ውስጥ፤ “ነፍጠኛ ውጣ”፣ “ይህ የኦሮሞ ነው አትንካ”፤ “እሱ/እሷ አማራ ነው/ናት”፣ “ክርስቲያን አጥፉ”፣ “እናንተ የሚኒሊክ ርዝራዦች ከዚህ ትወጣላችሁ”፣ “አማራ ውጣ”፣ “ነፍጠኛ ውጣ”፣ “ክርስቲያን ውጣ”፣ “መንዜ ውጣ” ይሉ እንደነበር ምስክሮች አስረድተዋል።

በሌላ በኩል ጥቃቱ በተፈጸመበት ወቅት በሚድያ ይተላለፉ የነበሩ መልእክቶች የወንጀል ድርጊቱ ስልታዊና የተቀናጀ እንደነበርም የሚያመለክቱ ናቸው።

በተለይ የኦሮሚያ ሚዲያ ኔትዎርክ (OMN) ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. ከጠዋቱ 12፡00 ሰዓት ጀምሮ በአፋን ኦሮሞ ፕሮግራም የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ ሐዘናቸውን ለመግለጽ የወጡ ወጣቶች ስለሁኔታው አስመልክቶ የሰጧቸውን አስተያየቶች በቀጥታ ስርጭት ሲያስተላልፍላቸው ከነበሩት መልእክቶች መካከል፡-

***“ሃጫሉን የገደለው ነፍጠኛ ነው፣ ሃጫሉን ከመቅበራችን በፊት ጠላታችን የሆነውን ይህን ሥርዓት ከፊንፊኔ (አዲስ አበባ) ነቅለን መቅበር አለብን፣ ሕዝባችን ይህን ሥርዓት መቅበር አለብህ”*** የሚል፤

በዚሁ ቀንና ፕሮግራም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት እስከ 5፡00 ሰዓት በሁለት ግለሰቦች መካከል ሲደረግ በነበረና በቀጥታ በተላለፈ ውይይት ላይ ***“መንግስት በኦሮሞ ላይ ጥላቻ አለው፣ ኦሮሞን ለማጥፋት ተነስቷል … እየገደሉን ገዳያችንን መለመን አቁመን ሥርዓትቱን መንቀል አለብን፣ ይህ ሥርዓት ካልፈረሰ ግድያ በሕዝባችን ላይ አይቆምም … ከሃጫሉ ሞት የሚጠቀሙ ነፍጠኞች ናቸው”*** የሚል፤

ሰኔ 26 ቀን 2012 ዓ.ም. ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ላይ በአፋን ኦሮሞ ፕሮግራም የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን አስመልክቶ አሜሪካ አገር ሚኒሶታ ከተማ በተካሄደው ሰልፍ ላይ አንድ የሰልፉ ተሳታፊ የተናገሩትና የተላለፈው ***"ከአሁን በኋላ ኢትዮጵያ ሰላም አታገኝም፣ ሰላም አይኖርም፣ መፍረሷ አይቀሬ ነው። ነፍጠኛ ወይም አማራ ከዚህ በኋላ በኦሮሚያ ምድር ላይ እንዳይኖር በየቀኑ ለማስወጣት ዝግጅት ላይ ነው"*** የሚል፤

ሰኔ 26 ቀን 2012 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 11፡00 ሰዓት፤ እንዲሁም ሰኔ 28 ቀን 2012 ዓ.ም. ከ11፡00 ሰዓት እስከ 12፡00 ሰዓት በአፋን ኦሮሞ ፕሮግራም የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን አስመልክቶ በአሜሪካ ሚኖሲታ፣ በጀርመን፣ በእንግሊዝ እና በካናዳ ቶሮንቶ በተደረጉ የተቃውሞ ሰልፎች ላይ የተነገሩና የተላለፈ ***"ነፍጠኛ ከኦሮሚያ መወገድ አለበት፣ አብይ ገዳይ ነው፣ አራጅ ነው፣ የኛ ኮሮና አብይ ነው፥ ኮሮና የለም፣ የሃጫሉ ገዳይ አብይ ነው፣ መንግስት ገዳይ / አራጅ ነው"*** የሚሉ በቀጥታ ስርጭት በጽሁፍና በቃል የተላለፉ መልዕክቶች ይገኙበታል።

ኢሰመኮ ያነጋገራቸው ምስክሮች አክለው እንዳስረዱት ጥቃቱ ማንነትን መሰረት ያደረገ ስለመሆኑ ሌላው አመላካች ማስረጃ፤ ጥቃት አድራሾች በአንዳንድ ከተሞች ጥቃት ለመፈጸም በቀጥታ ያመሩት እና ጥቃቱን የፈጸሙት በአብዛኛው የአማራ ብሔርተወላጆች ወይም የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች በአንድነት በሚኖሩበት አካባቢና መንደሮች መሆኑ ነው። ለአብነት ያህል በጭሮ አባ ኮራን ሰፈር እና በወሊሶ ገሊላ የሚባለው ሰፈር በዚህ አይነት ጥቃት ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል።




መንግስት በየፀጥታ ኃይሉ እና በመዋቅሩ አማካኝነት የሚፈጸሙ ወንጀሎችና ተገቢ ያልሆኑ አያያዞች ከመከላከል በተጨማሪ፤ ከመንግስት መዋቅር ውጪ ባሉ ግለሰቦችና ቡድኖችም የማንኛውም ሰው ሕይወት እንዳይጠፋና አካላዊ ጥቃት እንዳይደርስ እንዲሁም ንብረት እንዳይወድም የመጠበቅና የመከላከል ኃላፊነት አለበት። ይሁን እንጂ የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ድንገተኛ ግድያን ተከትሎ በተቀሰቀሰው ሁከት፤ ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. ከሌሊት ጀምሮ እና ሰኔ

23 ቀን 2012 ዓ.ም. ቀኑን ሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ልዩ ልዩ የኦሮሚያ አካባቢዎች፤ በየአካባቢዎቹ በተሰባሰቡ ሰዎችና ከአጎራባች የገጠር ቀበሌዎች በብዛት በመኪና ተጭነው በመጡ ሰዎች ጭምር አሰቃቂ ግድያና አካላዊ ጥቃት ተፈጽሟል፣ ንብረት ወድሟል፣ ሰዎች ከመኖሪያቸው ተፈናቅለዋል። ከእነዚህ ሁሉ ጉዳቶች በተጨማሪ ጥቃት በተፈጸመባቸው አካባቢዎች ነዋሪዎች ላይ ከፍተኛ የሥነ ልቦና ስብራት ደርሷል። በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች ነዋሪዎችን ከዚህ ጥቃት አስቀድሞ ለመከላከል በክልሉ መንግስት የተደረገ በቂ የጥንቃቄ ዝግጅት አልነበረም።




ስለጉዳዩ ለኢሰመኮ ማብራሪያ የሰጡት የፀጥታ አካላትና የመንግስት ኃላፊዎች ጥቃቱ ያልታሰበና ብዙ ቁጥር ያላቸው ሰዎች የተሳተፉበት ስለነበር በሚፈለገው መጠንና ፍጥነት ለማስቆም አለመቻሉን ገልጸዋል። በእርግጥ የጥቃቱ ድንገተኝነት፣ የብዙ ሰዎች በብዙ ስፍራዎች በጥቃቱ መሳተፍ፣ በአጋጣሚ በእለቱ የክልሉ የዞን እና ከተማ አመራሮች ለስብሰባ አዳማ ከተማ የነበሩ መሆኑ በየአካባቢው ለነበሩት የፀጥታ አካላት ፈታኝ የነበረ መሆኑን ለመገንዘብ ቢቻልም፤ በተለይ ከዚህ በፊትም ብሔርንና ሃይማኖትን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች የተፈጸሙባቸው ቦታዎች ላይ ጭምር አንዳችም ዝግጁነት አለመኖሩ ዜጎችን በአሳዛኝ ሁኔታ ለተደጋገመ ጥቃትና በደል አጋልጧል። እንዲሁም በአንዳንዶቹ ጥቃት የተፈጸመባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች ቀድሞውንም ብሔርእና ሃይማኖትን መሰረት ያደረገ ወከባ፣ ዛቻና ማስፈራሪያ ይደርስባቸው እንደነበር በተደጋጋሚ አቤቱታ ሲያቀርቡ የነበረና ከአካባቢው ነባራዊ ሁኔታም የሚታወቅ ሆኖ ሳለ፤ ተገቢው ትኩረት አለመሰጠቱን ያመለክታል።

ከዚህ በተጨማሪም በተወሰኑ ቦታዎች ጥቃቱ የተፈጸመው የፀጥታ አካላት በየአካባቢዎቹ ባሉበትና አንዳንድ ቦታዎች ላይም በቀጥታ እይታቸው ስር ሆኖ ጥቃቱን ለማስቆም ሙከራ እንኳን እንዳላደረጉና፤ ሰዎች እርዳታ ሲጠይቁ "አልታዘዝንም"፣ "የግለሰብ ንብረት ጠብቁ አልተባልንም"፣ "የምንጠብቀው የመንግስትና የልማት ተቋማትን፣ ባንኮችንና የኃይማኖት ተቋማትን ነው" የሚል ምላሽ ይሰጡ እንደነበር ምስክሮች አስረድተዋል።

## *3.2. በንብረት ላይ የደረሰ ጉዳትና የዜጎች መፈናቀል*

የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ በተከሰተው ሁከት በግለሰቦች፣ በድርጅቶች፣ በመንግስትና በፖለቲካ ፓርቲዎች ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል። በተለይም በአጋርፋ፣ በአዳባ፣ በዶዶላ፣ በሻሸመኔ፣ በአርሲ ነጌሌ፣ በባቱ፣ በአሳሳ፣ በበቆጂ፣ በአሰላ፣ በጭሮ፣ በአምቦ፣ በወሊሶ፣ በቡራዩ፣ በፍቼ፣ በሱሉልታ፣ በአዳማ፣ በዴራ፣ በኮፈሌ፣ በቢሾፍቱ እና አርቦዬ የብዙ ግለሰቦች መኖሪያ ቤቶች፣ የንግድ ተቋማት፣ የብልጽግና ፓርቲ ጽ/ቤቶች፣ የመንግስት ቢሮዎች እንዲሁም የተለያዩ ተሽከርካሪዎች በሁከት ፈጣሪ ሰዎችና ቡድኖች በእሳት በማቃጠል፣ በማፈራረስና በመሰባበር ወድመዋል፤ በከፊልም ተዘርፈዋል።

ከዚህ በላይ ስለግድያ እና የአካል ጉዳት ጥቃት እንደተመለከተው በንብረትም ላይ የደረሰው ጥቃት በተወሰኑ ቦታዎች የብሔርና የሃይማኖት ማንነትን መሰረት አድርጎ የተፈጸመ ነው። ለምሳሌ በአንዳንድ ቦታዎች የአማራ ቤት ተከራይተው ይኖሩ የነበሩ ኦሮሞዎችን ንብረታቸውን አስቀድሞ በማስወጣት ቤቶቹን ለይቶ በማቃጠል፤ እንዲሁም የኦሮሞዎች ቤት ተከራይ የሆኑ አማራዎችን ንብረታቸውን ለይቶ ከቤት ውጪ በማውጣት የመሰባበርና እና የማቃጠል ተግባር ተፈጽሟል።

ከንብረት ውድመት በተጨማሪ በርካታ ሰዎች ከመኖሪያ አካባቢያቸው፣ ተወልደው ካደጉበትና ከነቤተሰባቸው ለረጅም ዓመታት ከኖሩበት አካባቢ በግፍ ተፈናቅለዋል። ለምሳሌ ከመንግስት በተገኘ መረጃ መሰረት በአጋርፋ 227፣ በኮፈሌ 15፣ በሻላ 27፣ በሻሸመኔ 356፣ በሄበን አርሲ 25፣ በቆሬ 136፣ በገደብ አሳሳ 119 ቤተሰቦች፤ በአጠቃላይ 6468 ሰዎች በቤትና ንብረታቸው ላይ በተፈጸመ ጥቃት ወይም ለደህንነታቸው በመስጋት ከመኖሪያቸው ተፈናቅለው በቤተ ክርስትያን እና መንግስት በለያቸው ጊዜያዊ የመጠለያ ጣቢያወዎች ይገኙ ነበር።[3]

## *3.3. የሕክምና አገልግሎት ክልከላ*

ኢሰመኮ ምርመራ ባካሄደባቸው የተወሰኑ ስፍራዎች ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ህክምና እንዳያገኙ የመከላከል ድርጊቶች ነበሩ። በጉና ወረዳ ነገሌ ከተማ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. የመንግስት የፀጥታ አካላት በከተማው የሚገኘው ጤና ጣቢያ በመግባት ጉዳተኞች ይዘው ወደ ጤና ጣቢያው የወሰዱ ሰልፈኞችን እና የጤና ባለሙያዎችን “ለምን እርዳታ ትሰጣላችሁ” ብለው መደብደባቸውን፤ በዶዶላ ከተማ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. የፀጥታ ኃይሎች መደወላቡ ሆስፒታል ውስጥ በመግባት በሕክምና ላይ የነበሩ ተጎጂዎችን መደብደባቸውን፤ በአርሲ ነጌሌ ከተማ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. አምቡላንሶች አገልግሎት እንዳይሰጡ ማደናቀፎች እንደነበሩና በከተማው ጤና ጣቢያ በእለቱ የደም እጥረት ሲያጋጥም ከሻሸመኔ ከተማ ሆስፒታል ለማምጣት እንዲቻል የፀጥታ አካላት አጀብ እንዲያደርጉ ቢጠየቁም ፈቃደኛ እንዳልነበሩ በስፍራዎቹ የነበሩ የጤና ባለሙያዎች እና ምስክሮች ለኢሰመኮ አስረድተዋል።

በተጨማሪም በወሊሶ ከተማ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. በተከሰተው ሁከት ምክንያት ጉዳት ደርሶባቸው ወሊሶ ቅዱስ ሉቃስ ሆስፒታል የደረሱ ሰዎችን፣ የተወሰኑ የተቋሙ የሕክምና ባለሙያዎች “እርዳታ አናደርግም፤ አናክምም” በማለታቸው ተጎጂዎች የሕክምና እርዳታ በጊዜው ማግኘት አልቻሉም። በተለይም አንዳንድ የህክምና ባለሙያዎች

[3] ከብሔራዊ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን በቀን 25/12/12 በቁጥር H2501/143 ለኢሰመኮ የተፃፈ ደብዳቤ።

ፈጽሞ ከሕክምና ሥነ-ምግባር ውጪ በሆነ መልኩ "ሃዘን ታውጇል፣ ስራ አንሰራም" በማለትና ለተወሰኑ ተጎጂዎች ብቻ ስማቸውን በማየት በአድልዎ አገልግሎት ይሰጡ እንደነበር ምስክሮች ለኢሰመኮ አስረድተዋል።

## 3.4. የፀጥታ አካላት የኃይል አጠቃቀም

ምንም እንኳን የፀጥታ ኃይሉን በየቦታው የገጠመው መጠነ ሰፊ የሰላም መደፍረስ እና የፀጥታ ኃይል አባሎቹ የተሰማሩበት ኃላፊነት እጅግ ፈታኝ የነበረ መሆኑን መገንዘብ ቢቻልም፤ በተወሰኑ ቦታዎች የኃይል አጠቃቀም ተመጣጣኝነት ጥያቄ ያሥነሳ ስለነበር ኮሚሽኑ የፀጥታ አካሎችን የኃይል አጠቃቀም በሚመለከት ማጣራት አድርጓል።

በዚሁ መሰረት፣ በአምቦ ከተማ የጎዳና ላይ ሰልፈኞችን በአስለቃሽ ጭስ ለመበተን ከተደረገው ጥረት በስተቀር፤ በሌሎች ሁሉም አካባቢዎች የፀጥታ ኃይሎች የጎዳና ላይ ሰልፈኞችን ለመበተንም ሆነ አጠቃላይ ሁኔታውን ለመቆጣጠር የተጠቀሙት የሚያቃጥል/የሚያስለቅስ ንጥረ ነገር (chemical irritants /እንደ አስለቃሽ ጭስ/)፣ ውሃ፣ ወይም የፖሊስ ዱላ የመሰሉ መለስተኛ ጉዳት የሚያደርሱ መሳሪያዎችን (less-lethal weapon) ሳይሆን፤ ሕይወት ሊያጠፋ የሚችል መሳሪያ (lethal weapons, like firearms) ነበር።

> በአጠቃላይ አርቲስት ሃጫሉ ከተገደለ በኋላ ባሉት ሶስት ተከታታይ ቀናት በኦሮሚያ በመንግስት የፀጥታ ኃይሎች በተወሰደ እርምጃ ቢያንስ 76 ሰዎች ሲገደሉ፣ 190 ሰዎች የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል።

ኮሚሽኑ ለዚህ ሪፖርት ምርመራ ባደረገባቸው አካባቢዎች ከተጎጂ ቤተሰቦች፣ ከሕክምና ተቋማት፣ ከአይን ምስክሮች እና ከአካባቢው መስተዳደር አካላት በተሰበሰበ መረጃ መሰረት፤ በመንግስት የፀጥታ ኃይሎች በተወሰደ እርምጃ ቢያንስ 76 ሰዎች ሲገደሉ፣ 190 ሰዎች የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል።

ለምሳሌ በጉና ወረዳ ነገሌ ከተማ ሰኔ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. በአርቲስት ሃጫሉ ሞት ሐዘናቸውን በሰልፍ ገልጸው ወደ አከባቢያቸው ሲመለሱ የነበሩ ወጣቶችን ከሌላ ቦታ ወደ ነገሌ ከተማ እየገባ የነበረ የኦሮሚያ ልዩ ኃይል የተዘጉ መንገዶችን እንዲከፍቱ ትዕዛዝ በመስጠቱ ከወጣቶቹ ጋር ፍጥጫ ተፈጥሮ ለማረጋጋት ሽማግሌዎች ጥረት እያደረጉ ሳለ፤ ልዩ ኃይሉ በድንገት ተኩስ በመክፈቱ ሁኔታውን ለማረጋጋት ሲሞክሩ የነበሩት ሽማግሌዎችን ጨምሮ 5 ሰዎች በጥይት ተገድለዋል። የአካባቢው የአስተዳደር አካላትም በእለቱ በፖሊስ የተወሰደው እርምጃ እና ያስከተለው ጉዳት ከባድ እንደነበር ለኢሰመኮ ገልጸዋል።

በተጨማሪም የፀጥታ ኃይሎች የጎዳና ላይ ሰልፈኞችን ለመበተን ወይም የተዘጋ መንገድ ለማስከፈት በከፈቱት የእሩምታ ተኩስ በተለያየ የሰውነት ክፍላቸው ላይ በጥይት ተመትተው የቆሰሉ ወይም የሞቱ ሰዎችን ሁኔታ ኮሚሽኑ ከአይን ምስክሮችና ከሕክምና ማስረጃዎች አጣርቷል። ከፊሎቹ እግራቸውንና ታፋቸውን በጥይት የተመቱ ሲሆኑ፤ ከፊሎቹ ደግሞ ከጀርባቸው፣ ከፊት ለፊት ደረትና ጭንቅላታቸውን በጥይት ተመተዋል።

በተወሰኑ አካባቢዎች (ለምሳሌ በአምቦ እና ጊንጪ ከተሞች) በተፈጠረው ሁከት ከሰልፈኞችና በቡድን ተደራጅተው ከቦታ ቦታ ይንቀሳቀሱ የነበሩ ሰዎች መካከል መሳሪያ የያዙ፣ ጥይት የተኮሱ፣ ቦምብ ጭምር በመወርወር የፀጥታ ኃየል አባላቱን ያቆሰሉና የገደሉ ነበሩ። በመሆኑም በተወሰኑ ሁኔታዎች የፀጥታ አባላት ከነገሩ ሁኔታ አንጻር ጠመንጃ እንዲጠቀሙ ያስገደደ ሁኔታ እንደነበር ለመረዳት ቢቻልም፤ በአመዛኙ የፀጥታ ኃይል አባሎቹ መለስተኛ ጉዳት በሚያስከትሉ መሳሪያዎች (less-lethal weapons) ሳይሆን ሕይወት ሊያጠፋ የሚችል (lethal weapon) ጠመንጃና

የመሳሰሉ መሳሪያዎች የታጠቁ በመሆኑ ለሰልፈኞቹ፣ በአካባቢው ለነበሩ ሰዎችና ለየፀጥታ አባላቱ ጭምር የሕይወትና የአካል ደሕንነት ተጋላጭነት ፈጥሯል።

የመንግስት የፀጥታ ኃይሎች ጠመንጃ ለመጠቀም በሚያስገድዳቸው ሁኔታዎች ውስጥም ቢሆን፤ የተወሰኑ ሰዎች አሟሟት (ለምሳሌ በአዳማ ከተማ በቤቱ በር ላይ የተገደለ ግለሰብ፤ በዶዶላ ከተማ የ10 ዓመት ሕፃንን ጨምሮ እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች መገደላቸው፤ በነጌሌ ስጋሎ ከተማ በመንገድ ዳር ተኝቶ የነበረ የአእምሮ ሕመምተኛ የሆነ ሰው መገደሉ) ስለ አጠቃላይ ኃይል አጠቃቀምና ተመጣጣኝነት ከፍተኛ ጥያቄ የሚያሥነሳ ነው።

ኢሰመኮ ምርመራ ባደረገባቸውና የፀጥታ ኃይሎች በወሰዱት እርምጃ የሰው ሕይወት በጠፋባቸው በየትኛውም አካባቢዎች በፌዴራል ወይም በክልሉ መንግስት አካል የደረሰውን የሕይወት መጥፋት ለማጣራት የተጀመረ ስራ መኖሩን ለማረጋገጥ አልቻለም። ይህም ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት አካባቢዎች በተጨማሪ በአወዳይ፣ በአሰላ፣ በዶዶላ፣ በቡልቡላ፣ በቢሾፍቱ፣ በአሳሳ እና በሻሸመኔ ከተሞች የደረሰውን ጉዳት ይጨምራል። በአንዳንድ ቦታዎች (ለምሳሌ በአወዳይ እና በወሊሶ ከተሞች) የተወሰኑ ሰዎች አጠራጣሪ የአሟሟት ሁኔታን በተመለከተ ተገቢው የአስክሬን ምርመራ ሳይደረግ የተቀበሩ መሆኑን ኮሚሽኑ ተረድቷል።

## 3.5. ጠቅላላ ድርጊቱና ውጤቱ በሰብአዊነት ላይ የተፈጸመ (crime against humanity) የግፍና ጭካኔ ወንጀል (atrocity crime) ስለመሆኑ

በዓለም አቀፍ ደረጃ እጅግ ከተወገዙ ከባድ የግፍና ጭካኔ ወንጀሎች (atrocity crimes) መካከል አንዱ በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸም ወንጀል (crime against humanity) ነው።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባል አገራት እ.አ.አ. በ2005 ባደረጉት ዓለም አቀፍ ስብሰባ የሰው ልጆችን ከዘርማጥፋት ወንጀል (genocide)፣ ከጦር ወንጀል (war crime) እና በሰብአዊነት ላይ ከሚፈጸሙ ወንጀሎች (crimes against humanity) ለመከላከል እና ለመጠበቅ ቃል ገብተዋል።[4] ከዚህ በተጨማሪም እነዚህን ከባድ ዓለም አቀፍ ወንጀሎች የመከላከል እና ተፈጽመውም ሲገኙ ወንጀለኞችን የመቅጣት ሕጋዊ ግዴታ በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች[5] የሚመነጭ እና በዓለም አቀፍ የልማድ ሕግ ጭምር የታወቀ ነው።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ-መንግስት እንዲሁም በ1997 በወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ በሰዎች ላይ እንደዚህ አይነት ወንጀሎች እንዳይፈፀምባቸው ይከለክላል። በተለይ በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች (crimes against humanity) ላይ የሚቀርብ ክስ በይርጋ እንደማይታገድና በይቅርታ ወይም በምሕረት እንደማይታለፍ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ-መንግሥት (አንቀፅ 28) በግልጽ ተደንግጓል።

በዓለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤቶች በዳበረው ሥነ-ሕግ (jurisprudence of international criminal tribunals)[6] እና ዓለም አቀፍ የልማድ ሕግ (international customary law) መሰረት፤ በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸም ወንጀል (crimes against humanity) ማለት፤ ስልታዊ የሆነ ወይም ተስፋፍቶ በብዛት የተከሰተና ሆነ ተብሎ በሲቪል ሰዎች ላይ ያነጣጠረ ግድያን፣ የሰዎች ደብዛ ማጥፋትን፣ ማሰርን፣ አስገድዶ መሰወርን፣ ከአካባቢ

[4] The 2005 World Summit Outcome Document, paragraphs 138 and 139.
[5] The statutes of Nuremberg, Tokyo, ICTY, ICTR, and ICC.
[6] Nuremberg, Tokyo, ICTY and ICTR, cases.

ማስወጣትን፣ ጾታዊ ጥቃት መፈጸምን፣ አንድ ተለይቶ የሚታወቅ ቡድን ወይም የማሕበረሰብ ክፍልን ለይቶ ማሳደድና ማጥቃትን፣ ማሰቃየትንና ይህን የመሰሉ በአካል ደህንነት ወይም ሥነ-ልቦና ላይ ከፍተኛ ጉዳትና ስቃይ የሚያመጡ ኢ-ሰብአዊ ድርጊቶችን የሚጨምር የግፍና የጭካኔ ወንጀል ነው።

በተለይ በግድያ አማካኝነት በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸም ወንጀልን (crime against humanity of murder) ከሚያቋቁሙት መስፈርቶች ውስጥ ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. አጥፊዎቹ ሆነ ብለው አንድ ወይም ከዚያ በላይ ሰዎች መግደላቸው፤
2. ድርጊቱ በስፋት ወይም በስልታዊና በተቀናጀ መንገድ በሲቪል ሰዎች ላይ ያነጣጠረ ጥቃት አካል ሆኖ ሲፈጸም (the conduct was committed as part of a widespread or systematic attack directed against a civilian population)፣
3. አጥፊዎቹ ድርጊታቸው በዚህ በስፋት ወይም በስልታዊና በተቀናጀ መንገድ በሲቪል ሰዎች ላይ ያነጣጠረ ጥቃት አካል መሆኑን እያወቁ ወይም ድርጊታቸው የዚሁ አካል እንዲሆን አስበው ተሳታፊ ሲሆኑ (the perpetrator knew that the conduct was part of or intended the conduct to be part of a widespread or systematic attack directed against a civilian population) ናቸው።[7]

በዚህ ሪፖርት በዝርዝር እንደተመለከተው፤ የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ በተነሳው ሁከት የተፈጸሙ ድርጊቶች እነዚህን መስፈርቶች ያሟላሉ።

- በአብዛኛው በቡድን የተደራጁ ሰዎች ከቦታ ቦታ እየተንቀሳቀሱ ብዙ ሰዎችን በድንጋይ፣ በዱላ፣ በገጀራ፣ በመጥረቢያ፣ በዶማ፣ በስለት እና በእሳት በማቃጠል በአሰቃቂ ሁኔታ ገድለዋል፤ የአካልና የሥነ-ልቦና ጉዳት አድርሰዋል፤ ንብረት አውድመዋል፤ ነዋሪዎችን ከመኖሪያቸው አፈናቅለዋል፤

- ከላይ የተጠቀሱት ጥቃቶች ሰኔ 22 ቀን 2012 ዓ.ም. ሌሊት ጀምሮ እስከ ሰኔ 24 ቀን 2012 ዓ.ም. ድረስ ቢያንስ በ40 የተለያዩ ቦታዎች በስፋት ተፈጽመዋል፤

- ጥቃቱ ያነጣጠረው በከፊል በብሔር እና ኃይማኖታቸው ተለይተው የተመረጡ ሰዎችን ከየቤታቸው ለይቶ በማሳደድና በማጥቃት፤ በከፊል ደግሞ ብሔርና ሃይማኖት ሳይለይ ሰላማዊ ነዋሪዎችን ወይም ሲቪል ሰዎችን ሆነ ብሎ በማጥቃት ነበር፤

- ጥቃቱ የተፈጸመው የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ በተፈጠረው ሁከት እንደመሆኑ መጠንና በወቅቱ በማኅበራዊ ሚዲያና የተወሰኑ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ይተላለፍ ከነበሩት መልዕክቶችና እንዲሁም በወንጀል ድርጊቱ ይሳተፉ የነበሩ ሰዎችና ቡድኖች ያሰሟቸው ከነበረው መፈክሮች አንጻር፤ ጥቃቱን በመፈጸም ይሳተፉ የነበሩት ሰዎች፤ ተግባራቸው ስልታዊና የተቀናጀ ወይም የሰፊ ጥቃት አካል መሆኑን በማወቅ የተሳተፉበት እንደነበር ከነገሩ ሁኔታ ለመረዳት ይቻላል።

[7] Elements of the Crime of Genocide, Crimes against Humanity and War Crimes: International Criminal Court.

ስለሆነም አጠቃላይ የነገሩ ሁኔታና የድርጊቱ አፈጻጸም ስልታዊ በሆነ መንገድ ወይም በስፋት በሲቪል ሰዎች ላይ ያነጣጠረና በሰብአዊነት ላይ የተፈጸመ (Crime Against Humanity) የግፍና የጭካኔ ወንጀል (Atrocity Crime) መሆኑን ያመለክታል።

በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸም ወንጀልን (crime against humanity) ከሚያቋቁሙት መስፈርቶች ውስጥ በተለይ "ስልታዊና በተቀናጀ መንገድ የተፈጸመ" የሚለው ነጥብ፤ በዓለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤቶች የዳበረ ሥነ-ሕግ ተብራርቶ ተተርጉሟል። በስልታዊና በተቀናጀ መንገድ በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸም ወንጀል በመንግስት አካላት ወይም መንግስታዊ ባልሆኑና በተደራጁ ቡድኖችም ሊፈፀም እንደሚችል በዓለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ውሳኔዎች ያመለክታሉ።[8] ከዚህ በተጨማሪም የወንጀሉ ድርጊት በተቋማዊ አደረጃጀት፣ አመራር እና/ወይም የተወሰነ አካባቢን በሚቆጣጠር ቡድን ሊፈፀም ይችላል።

> የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከትሎ በተነሳው ሁከት የተፈጸሙ ድርጊቶች፥ አጠቃላይ የነገሩ ሁኔታና የድርጊቶቹ አፈጻጸም ስልታዊ በሆነ መንገድ ወይም በስፋት በሲቪል ሰዎች ላይ ያነጣጠረና በሰብአዊነት ላይ የተፈጸመ (Crime Against Humanity) የግፍና የጭካኔ ወንጀል (Atrocity Crime) መሆኑን ያመለክታል።

ከዚህ በላይ የተገለጹት በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸም ወንጀልን (crimes against humanity) ከሚያቋቁሙት ሶስት መስፈርቶች ውስጥ 2ኛ እና 3ኛ መስፈርቶች የወንጀሉ ድርጊት ስለተፈጸመበት አውድ ወይም ከባቢያዊ ሁኔታና የአጥፊዎቹ የተሳትፎ ሁኔታ የሚመለከቱ ሲሆን፤ በዓለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤቶች በዳበረው ሥነ-ሕግ መሰረት በወንጀሉ ድርጊት ተሳታፊ የሆኑት አጥፊዎች ስለ ወንጀሉ ዝርዝር አፈጻጸም ዝግጅትና ዕቅድ የግድ ሊያውቁ ይገባል ማለት እንዳልሆነ፤ ይልቁንም በድንገት በተከሰተ የተስፋፋ ወይም ስልታዊ የሆነ በሲቪል ሰዎች ላይ ያነጣጠረን ጥቃት ለማገዝ ወይም ለማራመድ አስበው መሳተፋቸው፤ መስፈርቱን ለማሟላት በቂ እንደሆነ ተመልክቷል።

"The [two elements of crime against humanity] describe the context in which the conduct must take place. These elements clarify the requisite participation in and knowledge of a widespread or systematic attack against a civilian population. However, the last element should not be interpreted as requiring proof that the perpetrator had knowledge of all characteristics of the attack or the precise details of the plan or policy of the State or organization. In the case of an emerging widespread or systematic attack against acivilian population, the intent clause of the last element indicates that this mental element is satisfied if the perpetrator intended to further such an attack."[9]

በዚህ ሪፖርት በዝርዝር በተገለጹት ጥቃቶች የተሳተፉት ሰዎችና ቡድኖች አንድ ተለይቶ የታወቀ አደረጃጀትና አንድ ወጥ አመራር ነበራቸው ባይባልም፤ ብዙ ሰዎች ከተለያዩ አካባቢዎች በመኪና ጭምር ተጉዘውና ተሰባስበው፣ መፈክር እያሰሙ፣ ከቦታ ቦታ በቡድን እየተንቀሳቀሱና የሚያጠቁትን ሰው በከፊል በብሔርና በኃይማኖት እየመረጡ በአጠቃላይ

[8] *Tadic*, *Kupreškić* case the ICTY.

[9] Elements of the Crime of Genocide, Crimes against Humanity and War Crimes: Guide Material of the International Criminal Court, p. 3.

ግን በሲቪል ሰዎች ላይ አነጣጥረው ሲፈጽሙ የነበረው ጥቃት፤ ስልታዊ ወይም ሰፊ የሆነ የጥቃት አላማን ለማገዝ ወይም ለማራመድ ታስቦ የተፈጸመ መሆኑን በበቂ ሁኔታ ያሳያል።

በዚህ አይነት የወንጀል ድርጊት አፈጻጸም የወንጀሉ እቅድ ወይም ፖሊሲ ማለት የግድ በጽሁፍ የተቀመጠ ወይም በይፋ የታወጀ እቅድ/ፖሊሲ ማለት ሳይሆን፤ ይልቁንም ከነገሩ ሁኔታዎችና ከወንጀሉ ድርጊት፣ ከፖለቲካ መድረኮች ንግግሮች፣ ጽሁፎች፣ ፕሮፖጋንዳ መልዕክቶች፣ የሚዲያ ቅስቀሳዎችና በአጠቃላይ ከወንጀሉ አፈጻጸም እና ከባቢያዊ ሁኔታ መገንዘብ እንደሚቻል በዓለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤቶች የዳበረ ሥነ-ሕግ ተመልክቷል።[10]

የወንጀል ድርጊቱ በዋነኛነት በተለያዩ ሰዎችና ቡድኖች ቢፈጸምም፤ የመንግስት አካላት በዝምታ በማለፍ፣ በመታገስ፣ በማበረታታት፣ በግልጽ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በመደገፍና በመሳሰሉ ድርጊቶች ወይም ተገቢውን የመከላከል ድርጊት ባለመፈጸም በወንጀል ድርጊቱ ተሳትፎ ሊኖራቸው እንደሚችልና ይህም ተጠያቂነት እንደሚያስከትል ይታመናል።[11] በዚህ ሪፖርት እንደተመለከተው በአንዳንድ ቦታዎች የመንግስት የፀጥታና አስተዳደር አካላት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ተሳትፎ የነበራቸው መሆኑ ስለታወቀ፤ በተለይ የኦሮሚያ ክልል መንግስት ሰላማዊ ነዋሪዎችን ወይም ሲቪል ሰዎችን ይህን ከመሰለ ጥቃት ሊከላከል ሳይችል በመቅረቱ፤ የበኩሉን ኃላፊነት ተቀብሎ ጥፋተኛ የመንግስት ኃላፊዎችን ተጠያቂነት ማረጋገጥ አለበት።

### *የግፍና ጭካኔ ወንጀሎች (atrocity crimes) ወደፊት እንዳይከሰቱ ስለመከላከል*

ከዚህ በላይ እንደተመለከተው በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸም ወንጀል (crime against humanity) በመከሰቱና ከሌሎች የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር ተዳምሮ ሲታይ፤ የዘር ማጥፋት ወንጀልን (Genocide) ጨምሮ የዚህ አይነት የግፍና ጭካኔ ወንጀሎች (atrocity crimes) ስጋት መኖሩን የሚያመላክት ስለሆነ፤ የአጥፊዎችን ተጠያቂነት ከማረጋገጥና የተጎዱ ሰዎችን መልሶ ከማቋቋም በተጨማሪ፤ መንግስት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር፤ የተሟላ የግፍና ጭካኔ ወንጀል መከላከያ ስትራቴጂ (Comprehensive Strategy for the Prevention of Atrocity Crimes) ነድፎ በአፋጣኝ በስራ ላይ ሊያውል ይገባል።

> በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸም ወንጀል (crime against humanity) በመከሰቱና ከሌሎች የኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር ተዳምሮ ሲታይ፤ የዘር ማጥፋት ወንጀልን (Genocide) ጨምሮ የዚህ አይነት የግፍና ጭካኔ ወንጀሎች (atrocity crimes) ስጋት መኖሩን የሚያመላክት ስለሆነ፤ የአጥፊዎችን ተጠያቂነት ከማረጋገጥና የተጎዱ ሰዎችን መልሶ ከማቋቋም በተጨማሪ፤ መንግስት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር፤ የተሟላ የግፍና ጭካኔ ወንጀል መከላከያ ስትራቴጂ (Comprehensive Strategy for the Prevention of Atrocity Crimes) ነድፎ በአፋጣኝ በስራ ላይ ሊያውል ይገባል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እነዚህ እጅግ በጣም ከባድ የሆኑ የግፍና ጭካኔ ወንጀሎች ከመፈጸማቸው በፊት አስቀድሞ ለመለየትና ለመከላከል የሚረዳ ዝርዝር የስጋት ምንጮችንና አመላካቾችን ለመተንተን የሚያግዝ የትንተና መርጃ ማእቀፍ[12] አዘጋጅቷል። ይህ ማእቀፍ እንደሚያመለክተው፤ የግፍና ጭካኔ ወንጀሎች (atrocity crimes) በድንገት የሚከሰቱ ሳይሆኑ፤ የረዥም

[10] Prosecutor vs Tadić, *ICTY, (trial chamber)* Judgment of 7 May 1997, para. 653.
[11] *Kupreškić*case, ICTY.
[12] United Nations, Framework of Analysis for ATROCITY CRIMES A tool for prevention, 2014 (reprinted in 2018)

ጊዜ ሂደት ውጤቶች በመሆናቸው፤ በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ የወንጀሉ ስጋት ስለመኖሩ አመላካች ሁኔታዎችንና ቁልፍ ምክንያቶቻቸውን አስቀድሞ በመለየት፤ አስፈላጊውን የጥንቃቄና የመከላከል እርምጃዎችን ለመውሰድ ይቻላል።

ስለሆነም በዚህ የተባበሩት መንግስታት የትንተና ማዕቀፍ መሰረት በአፋጣኝ የልዩ ባለሙያዎች ቡድን በማቋቋም፤ ስለ ስጋት ምንጮች የተሟላ ማስረጃ በማሰባሰብ የግፍና የጭካኔ ወንጀሎች መከላከያ ስትራቴጂ ቀርጾ በአስቸኳይ ስራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል።

***

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን

Ethiopian Human Rights Commission